# ሪቻርድ ፓንክረስት የታሪካችን ጎልጉል

በአገራችን ታሪክ ላይ ብዙ መጽሃፍት የተጻፉ ቢሆንም በዘመናዊ ጥናትና ምርምር ከቀረቡት ውስጥ በ1927 ዓም እአአ በእንግሊዝ አገር ውድፎርድ በተባለው ቦታ የተወለዱት የፕሮፌሶር ሪቻርድ ፓንክረስት ስራዎች ትልቁን ድርሻ ይይዛሉ።እኚህ የታሪክ ምሁር ለኢትዮጵያ ታሪክ ትኩረት የሰጡት ገና በወጣትነት ሳሉ ከወላጅ እናታቸው ከወረሱት አፍቅሮ ኢትዮጵያ በመነሳት ነው።እናታቸው ወ/ሮ ሲልቪያ ፓንክረስት ኢትዮጵያ በጣልያኖች በተወረረችበት ጊዜ ከአጼ ሃይለስላሴ ጎን በመሆን የኢትዮጵያን ጉዳይ በእንግሊዞች አእምሮ ውስጥ ሰርጾ እንዲገባና ለነጻነት ትግሉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ የቁርጥ ቀን የኢትዮጵያ ወዳጅ ናቸው።በዚህ የኢትዮጵያ ፍቅር የተጠመቀው ልጃቸው ሪቻርድም የእናቱን ፈለግ ተከትሎ ለኢትዮጵያ ያለውን ፍቅር እስከመጨረሻው ባለው የብእር መሳሪያ ታሪኳን እየጎለጎለ/እያወደሰ ሲከላከልና ለተተኪው ትውልድ ሲያስተምር ፣ልጆቹንም ሄለንና አሉላ በማለት በስምና በግብር ከኢትዮጵያ ጋር አስተሳስሮ እንደሱ በአፍቅሮ ኢትዮጵያ የተራቸውን እንዲወጡ ያደረገ ትልቅ ምሁርና የኢትዮጵያ ባለውለታ ነው።ይህ ታላቅ የታሪክ ሰው በተወለደ በሰማንያ ዘጠኝ ዓመቱ በሚወዳት አገር በኢትዮጵያ ውስጥ በፌብሩዋሪ 16 2017 በሞት ተለዬ። የዚህን ታላቅ የታሪክ ምሁር ውለታ በምስጋና ብቻ ሳይሆን ሲምስክርለት የኖረውን የኢትዮጵያን ታሪክ ተቀብሎ ለተተኪው ትውልድ ማሳለፍ ተገቢና አስፈላጊ ነው።ስለሆነም እኔም በበኩሌ ከጻፋቸው መጽሃፍት ውስጥ በአንዱ ያገኘሁትን ላለንበት ወቅት ተገቢ ስለመሰለኝ ባለኝ መለስተኛ የእንግሊዝኛ ችሎታ አንብቤ የተረዳሁትን ብዙሃኑ ኢትዮጵያዊ በሚረዳው ቋንቋ በአማርኛ ተርጉሜ **ለአርባ ቀኑ መታሰቢያ** ይሆን ዘንድ አቅርቤያለሁ።የትርጉም ስህተትና ግድፈት ቢኖር ይቅርታ እየጠየኩ ከአላማው አንጻር እንዲታይልኝ አሳስባለሁ። በምሁሩ የቀረበውን ጽሁፍ ከመተርጎሙ ጋር ታሪኩ በአሁኑ ጊዜ ያለውን ዝምድናና ውጤት በሚመለከት የግል አስተያየቴንም የተረጓሚው አስተያየት በሚል አመላካች አያይዤ ማቅረቤን ከወዲሁ ለመግለጽ እውዳለሁ።

ትርጉሙ ያተኮረው «መንግስትና መሬት በኢትዮጵያታሪክ "STATE AND LAND IN ETHIOPIAN History" በሚል እርእስ በፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት የተጻፈው መጽሀፍ ነው።እንዲህ ሲል በክርስትናው እምነት ይጀምራል-

የክርስትና ሃይማኖት የመንግስትና የሃገሪቱ ሃይማኖት የሆነው በአራተኛው መቶ ዓመት ከክርስቶስ በኋላ ኤዛና በተባለው ዘመነ መንግስት ነው። ፈሬምናጦስ የተባለው ወጣት ሶሪያዊ ለክርስትና መስፋፋት የመጀመሪያ ጳጳስ በመሆን ብዙ ሰርቷል።በጊዜው በዘውድ ላይ ተቀምጣ የነበረችውን ንግስት እናት የሆነችውን ሶፊያን በማሳመን ለንግድ ከቦታ ወደ ቦታ የሚንቀሳቀሱት ነጋዴዎች በዬቦታው ቤተክርስቲያን /የጸሎት ቦታ /እንዲያሰሩ በማዘዝ ሃይማኖቱ ሊስፋፋ ቻለ።

በስድስተኛው መቶኛ ዓ.ም ማለቂያ ላይ በንጉስ አሜዳ ዘመነመንግስት የመጡት የሶርያ ዘጠኝ መነኮሳት ቅዱስ መጽሃፍትን በመተርጎምና በልዩ ልዩ ቦታዎች አድባራትንና ገዳማትን መሰረቱ።

አባ አሌፍ የባህዛን፣አባ አረጋዊ የደብረ ዳሞን፣አባ አፍሴ ዬሃን፣አባ ገሪማ የማዳራን፣አባ ማታ የእንዳን በሰሜን ኤርትራ ውስጥ፣የግብጹ አባ ዩሃንስም የደብረሲናን ደብር መሰረቱ።የየአንዳንዱ ደብርና ገዳም ምስረታ ከትላልቅ መሬት ስጦታ ጋር የተቆራኘ ነበር።

በተጨማሪም ስለ ዝነኛው የሃይቅ ገዳም (ወሎ፣ከደሴ ሃያ ኪሎሜትር ወደሰሜን የሚገኝ) ስለ ቅዱስ እስጢፋኖስ ገዳም ምስረታ የሚከተለውን ተጽፏል።

በሰባተኛው መቶ ዓ. ም.አባ ሰላማ አዜብ የሚባል ጳጳስ ከደሴ ከተማ ወጣ ብሎ የሚገኘውን የሃይቅን ደሴት ጎብኝቶ ለመውሰድ ተመኘ።የደሴቱ ነዋሪ በትልቅ ዛፍ ላይ በሚኖር ዘንዶ ያመልክ ነበር። በየቀኑ ለዘንዶው ወተትና ስጋ ይገብር ነበር። ይህ ጳጳስ ደሴቱን በመስቀሉ በመባረክ ዘንዶውን አሶገደው።ይህንን ተአምር

መስራቱን ለንጉሱ ነግሮ በደሴቱ ላይ ቤተክርስቲያን ለመስራት ፈቃድ ጠይቆ ተፈቅዶለት የገቢ ምንጭም እንዲሆነው ብዙ ሰፊ መሬት ተሰጠው ይባላል።እሱም አሁን እስጢፋኖስ ገዳም ተብሎ የሚጠራው መሰረተ።

በዚህ ታሪክ ላይ የተረጓሚው አስተያየት«የዚህ ዘንዶ ታሪክ በአውሮፓውያኑም ዘንድ የተለመደ ስለሆነ እውነተኛ ታሪክ ነው ከማለት ይልቅ ልብ ወለድና አፈታሪክ ነው ብሎ ማሰቡ ሳይቀል አይቀርም። በአውሮፓውያኑ የሚነገርለት የዘንዶ ታሪክ ጋር ይመሳሰላል።በዱሮ ጊዜ ነዋሪውን ያስጨነቀና ያስቸገረ አንድ ዘንዶ ነበር ይባላል። ከሚያደርሰው ጥፋት ለመዳን በየጊዜው የከባቢው ኑዋሪ በተራ ለዘንዶው አንዳንድ ቆንጆ ሴት ልጃገረድ መገበር ግዴታው ነበር። ከብዙ ዘመን በኋላ የንጉሱ ተራ ሆነ።ንጉሱ የሚወዳትን አንድ ሴት ልጁን ለዘንዶ ከመስጠት ይልቅ ዘንዶውን ለገደለ ጎበዝ ልጁን እንደሚድርና የመንግስቱን ግማሽ እንደ ሚሸልመውና አሳልፎ እንደሚሰጠው በአዋጅ አስነገረ።በዚያ መሰረት አንድ ደፋር የደሃ ልጅ በፈረስ ዘንዶው ከሚገኝበት ጫካ ድረስ በመሄድ ዘንዶውን ገድሎ ሕዝቡንና ንጉሱን ከጭንቅ በማዳኑ የተባለውን እንዳገኘ የሚያትት፣ እስከ አሁን ድረስ ለልጆች የሚነገር ልብ ወለድ መዝናኛ ተረት ሆኖ ቆይቷል።ታዲያ አባሰላማ አዜብም ይህን ያገራቸውን ታሪክ አምጥተው ይሆናል በሕዝባችንና በመሪዎቹ ላይ የነሰነሱት።»

እዚህ ላይ ግራ የሚያጋባው ነገር ከላይ ከፍ ብሎ በተገለጸው የክርስትና ሃይማኖት ዜና ቀደም ሲል በመጀመሪያዎቹ አስርታት ዓመታት ውስጥ (በ30-42 ዓ.ም) በንግስት ህንደኬ(ገርሳሞት) ጃንደረባ እንደ ደረሰና እሱም በክርስትና ሃይማኖት ተጠምቆ እንደመጣ ሲነገር በሌላው የታሪክ አገላለጽ ደግሞ የክርስትና ሃይማኖትና ትምህርቱ ከአራት መቶ ዓመት በኋላ በፍሬምናጦስ በኩል ለመግባት ቻለ ይላል።የአገሩ ቅርበትና የንግስቲቱ የግዛት ክልል ጋዛ ሲደርስ የሃይማኖቱ ዜናና ትምህርቱ ከእየሩሳሌም አክሱም ለመድረስ እንዴት አራት መቶ ዓመት ፈጀበት የሚል ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀርም።

በዚህም ሆነ በዚያ ይህ የክርስትና ሃይማኖት በኢትዮጵያና ከዚያም በፊት በባይዘንታይን( በግሪኮች)የከባቢ ትልቅ መንግስት ግዛት በመስፋፋቱ ቀሪውን ያልተጠመቀ አገር ሕዝብ በሃይል በማስገደድ ክርስቲያን የማድረጉ ሂደት ተስፋፍቶ ነበር ፤የክርስቲያኑ መንግስታት የጋራ ግንባር ነበራቸው።

ሃይማኖቱን በመጀመሪያ የተቀበሉት በስልጣን ላይ የነበሩት በመሆናቸው ሃይማኖቱና መንግስታቱ የማይነጣጠሉ ሆኑ፤ መንግስታት ሃይሞኖቱን ሲያስፋፉ ሃይማኖቱም ለነገስታቱ ሕዝቡ በሰላም ሰጥ ለጥ ብሎ ተገዝቶ እንዲኖር ያስተምርና ይሰብክ ነበር።ክብረ ነገስት በተባለው ያገራችን ጥንታዊ መጽሀፍ የተጻፈውን ብንመለከት በይበልጥ ልንረዳ እንችላለን።

በአምላክ ምርጫ ንጉስ ይነግሳል፤ከወንድሞች መካከል ይመረጣል፤በነሱም ላይ ይነግሳል፤እንግዳና ባዳ ወንድም ያልሆነ በትረመንግስቱን ይረከባል፤ዙፋን ላይ ይወጣል፤ዘውድ ይጭናል፤ይህም በቁሶች ጸድቆ ህግ ይሆናል።

ሁሉም ፍጥረት /ነፍስ/ ለላይኛው ሃይል ይገዛ፤ከፈጣሪም ሌላ ሃይል የለም፤ሁሉም ሃይል የፈጣሪ ስጦታ ነው፤ የንጉስን ሃይል የማይቀበል ፣የሚቃወም፣ፈጣሪውን የሚቃወም ነው። እሱም የተረገመ ይሆናል። ስለዚህ የሚከበረውን ማክበር፣የሚከፈለውን መክፈል፣ መፍራት ተገቢ ነው።

ክብረ ነገስት ስለአመጽና ተቃውሞ በማንሳት እንዲህ ይላል፤በንጉሱ ላይ ለመፍረድና እርምጃ ሊወስድ /ሊቀጣ/ የሚችለው አምላክ ብቻ ነው።(የተርጓሚው አስተያየት አምላክ እስኪፈርድበት ድረስ ሕዝብ በትዕግስት ድምጹን አጥፍቶ፣ሰጥ ለጥ ብሎ መገዛት አለበት ማለት ነው።)

በ1588-1679 የነበረው እንግሊዛዊ ፈላስፋ ቶማስ ሆብስ እንደጻፈው፣ ጥሩ መሪዎች ሲኖሩ ጊዜውም ጥሩ ይሆናል፣መሪው መጥፎ ሲሆን ጊዜውም እንደዚያው መጥፎ ይሆናል።ቀጥሎም የከተማ መጥፋትም ሆነ መልማት በመሪዎች ጸባይና እጅ ነው ይላል።አገር እንደመሪው ነው የሚለውን አባባል መጽሀፍ ቅዱስም ገልጾታል።ክብረ ነገስትም እንዲህ በማለት ስለመልካምና መጥፎ መሪዎች እጣ ፈንታ በተጨማሪም ከአምላክ ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት እንደሚከተለው ገልጾታል።

ፈጣሪ ሁል ጊዜ ጥሩ ነገርን ይደግፋል፤ይረዳል፣ከጥሩ ጎን ይቆማል።ንጉስ ጥሩ ከሆነ፣አምላክ በሶስት ጎኑ ይጠብቀዋል።

በመጀመሪያ ጠላቶቹን ያሶግድለታል፣እንዳይማረክና እጃቸው ውስጥ እንዳይገባ ይጠብቀዋል።

ሁለተኛ ቀናና ትክክለኛ ስራ እንዲሰራ አምላኩ በቀኝ ጎኑ ይቆማል።

ሶስተኛ ዓለም፣ደስታና ጸጋ የሰፈነበት አገዛዝ እንዲቀዳጅና ሁሉም አገርና ሕዝብ በስሩ እንዲያድር ይረዳዋል ይላል።

የተርጓሚው አስተያየት« ሃይማኖት ለስርዓት አገልጋይና መከታ፣ለስልጣንም መወጣጫ መሰላል መሆኑን በታሪክ አይተናል፣እያየንም ነው።በተለያየ ጊዜ የተነሱትን ስርዓቶችና የተጠቀሙበትን ሃይማኖት ለመመልከት ይረዳ ዘንድ ከዚህ በታች በታሪክ መዝገብ ውስጥ ሰፍሮ ያገኘሁትን ለማካፈል እወዳለሁ።

በውጭ ሃይሎች ግፊትና ወረራ፣ የመደብም ሆነ የሃይማኖት፣ ወይም የስልጣን ንትርክና ግጭት በኢትዮጵያ ምድር ውስጥ ሲካሄድ ቆይቷል።በጊዜው ገነው የነበሩ መንግስታት አቅማቸው እየዛለ፣በምትካቸው ሌሎች እየተነሱ ሲመጡ ለባለተራው የመልቀቅ ግዴታ ውስጥ ገቡ።የእስልምና ሃይማኖት ተነስቶ በክርስቲያን መንግስታት ላይ አመጽ ቀሰቀሰ፤በስራቸው የነበሩትን ግዛቶች እየነጠቀ ስልጣንና ሃይላቸውን ተፈታተነ፤በድል ላይ ድል እየተቀዳጀ ብዙ አገሮችን በመውረር በስሩ አደረገ፤ሕዝቡንም የወደደውን በሰላም ያልወደደውን በሃይልና በማስገደድ አሰለመው።እምቢ ያለውንም አጠፋው።

የክርስትናን ሃይማኖት ለማስፋፋት የክርስቲያን መንግስታት እንደተባበሩ ሁሉ የእስልምና ሃይማኖትንም ለማስፋፋት የእስላም አገሮችና መንግስታት ተባብረዋል።በዚህ ዓለም አቀፍ የእስላም ዘመቻ ብዙ ጠንካራ የነበሩ አገሮችና መንግስታት እየተጠቁ ሲሸነፉና ሲገረሰሱ የኢትዮጵያም ክርስቲያን መንግስታት ከመጣው ጦስና መከራ አላመለጡም።

የዚህ ከባድና ፈታኝ ጊዜ ቀማሽ የሆነው ንጉስ አጼ ካሌብ ነበር።አጼ ካሌብ የፋርስና የአረብ እስላሞችን መስፋፋት ለማቆም መርከቦቹን ከቀይ ባህር አንቀሳቅሶ ወደ የመን በማምራት ድል አድርጎ በቦታው አብርሃ የሚባል መኮንኑን የየመን አገረ ገዥ አድርጎ ብዙ ጦር አስቀምጦ ወደ አክሱም ተመለሰ።ብዙ መንፈሳዊና ፖለቲካዊ ስራዎችን ከሰራ በኋላ ይህን ዓለምና መንግስቱን በመናቅ መንኖ ገዳም ገብቶ ሞተ።

በቦታው ልጁ አጼ ገ/መስቀል ተተክቶ እንደ አባቱ የአረብና የፋርስ እስላሞቹን ተዋግቶ በተደጋጋሚ ድል ማድረጉ እሱም እንደ አባቱ መንኖ መሞቱን ታሪክ ይገልጻል።ከሱ በኋላ በአክሱም ሃያ ስምንት /28 ነገስታት ተከታትለው ነግሰዋል፤የመጨረሻው የአንበሳ ውድም መንግስት በስምንት መቶ አርባ አምስት /845 ዓ.ም. ዮዲት በምትባል የአይሁድ ሀይማኖት አማኝ የሆነች ኢትዮጵያዊት/ ፈላሻ የተባለውን የሰሜንን ማህበረሰብ አስተባብራ በግፍ የተገደለባትን ጌዴዎን የተባለውን የጎሳ መሪ አባቷን ደም ለመበቀልና ሃይማኖቷን ተከላክላ ለማስከበርና ለማስፋፋት በመነሳት የአክሱምን መንግስት ገለበጠች። በጊዜው የነበረው ንጉስ አንበሳ ውድም ሊቋቋማት ስላልቻለ ከአክሱም አምልጦ ሸዋ መንዝ ገባ።ዮዲት ተከታትላ ለመያዝ ሞክራ ነበር ግን ሸሽቶ ወደ መራቤቴ ስለገባ ፊቷን ወደ አክሱም አዞረች።ዮዲት አርባ ዓመት ገዝታ ስለ ሞተች አንበሳ ውድም ከሸዋ ወደ አክሱም ተመልሶ ሃያ /20/ዓመት ነገሰ።ልጁም ድል ነአድ ተተክቶ አስር ዓመት ገዛ።

የአክሱም ነገስታት በዘር እየተቀባበሉ አያሌ ዘመናት ከገዙ በኋላ እንደቀሩት በጊዜው ተነስተውና ገነው እንደ ወደቁት የግሪክ፣የሮማና የፐርሺያ ስርወ መንግስታት ከተነሳው ነውጥ ሊያመልጡ አልቻሉም።የመንግስታት ስልጣን በውስጥና በውጭ ግፊትና ትብብር ባለተራ የሚቀማው የቡድኖች ጨዋታ ሆነ።

ነገር ግን በተከታታዮቹ የአክሱም ነገስታት በሁለት በኩል ባላጋራ ተቀሰቀሰባቸው። የእስልምና ዘመቻው ሌላውን የእስያንና የሰሜን አፍሪካ በቁጥጥሩ እያደረገ በኤርትራም ባሕር ዳር ለዳር ያለውን በዳህላቅና በአዶሊስ ደሴቶች

ያለውን የአክሱምን ግዛት መጫንና ማወክ ጀመረ።ሁለተኛው ደግሞ ከአክሱም በደቡብ በኩል ያለው የላስታ ሕዝብ የዛጉዌን ዘር አንግሶ ርእሰ ብሄሩን ወደ ላስታ አዛወረ።በዚህ በሁለት አጣብቂኝ ማለትም በሃይማኖትና በክልል/በዘር/ጥርስ ውስጥ የገባው የሳባ ዘር ንብረት ሆኖ የቆየው የአክሱማይት ወርሃ መንግስት ሰንሰለት ለተከታዮቹ መቶ ዓመታት ተበጥሶ ኖረ።

የመጀመሪያው  የላስታ ንጉስ ክርስቲያኑ ተክለ ሃይማኖት ነበር። የታወቀውና የዚህ ዘር ተወላጅ  የሆነው ላሊበላም ዘጠነኛው ንጉስ ነው።ንጉስ ላሊበላ ከማስተዳደር በላይ የሃይማኖት ሰው ስለነበረ በአሁኑ ጊዜ የሚደነቁትን አብያተክርስቲያናት አሰርቷል። እንዲሁም ግብጻውያንን ለማንበርከክ የአባይን ወንዝ አቅጣጫ በመለወጥና ወደ ግብጽ እንዳይፈስ አደርጋለሁ በማለት ሕዝቡንና ንጉሱን አስጨንቆ እንደነበር ይነገራል። የዛጉዌ መንግስት ከዘጠኝ መቶ እስከ ሽህ ሁለት መቶ ዓመት (900-1200 ዓ.ም) ሶስት መቶ ዓመት ከቆየ በኋላ የመጨረሻው ንጉስ የነበረው ነኵቶ ለአብ በሚገዛበት ዘመን በሃዋርያነትና በብቃት የታወቁት የቡልጋው ተወላጅ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከሸዋ ላስታ ሄደው የዛጉዌ ዘር የመንግስትን ስልጣን ከሰለሞናዊ ከቀዳማዊ ምኒሊክ ዘር የወሰደው በሃይልና በማይገባ መንገድ መሆኑን አስረድተው በጊዜው ሸዋ ውስጥ ለሚገኘው ለድል ነዓድ ስምንተኛው ልጅ ለይኩኖ አምላክ እንዲለቅለት ባባትነት ስለመከሩት እሱም ፍጹም ክርስቲያንና የመምህር ቃል ሰሚ ነበርና ምክራቸውን ተቀበለ። ስልጣኑን፣ዙፋኑንና ዘውዱን ለመልቀቅ ግን የሚከተሉትን ውሎች ተዋውሎ ነበር። በዚህም ውል መሰረት

1ኛ-የላስታ ከባቢ አስተዳደር ከዛጉዌ ዘር መዳፍ እንዳይወጣ

2ኛ-ላስታን የሚገዛው መስፍን የዛጉዌ ዘር ለመሆኑ ለምልክት ሁለት የብር ነጋሪት እንዲያስጭን

3ኛ-የቀዳማዊ ምኒልክ ዘር በወርቅ ዙፋን ሲቀመጥ የላስታው መስፍን በትንሽ የብር ወንበር እንዲቀመጥ የሚደነግግ ውል ነበር።

በጊዜው በሸዋ  የተቀባ ጳጳስ ባለመኖሩ በኘሁ በአቡነ ተክለሃይማኖት እጅ ይኩኖ አምላክ ዘውድ ጭኖ ነገሰ። ለውለታቸውም የመንግስቱን ሲሶ ለአቡኑ በመስጠቱ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የነበረው የቤተ ክህነት ድርሻ በዚህ መሰረት እንደ ተጀመረ ይነገራል።ሆኖም ግን ቀደም ብሎ እንደተመለከተው ከብዙ ዘመን በፊት ለዘጠኙ መነኮሳት አገልግሎት ነገስታቱ መሬት ይሰጡ እንደነበር አይተናል።የጊዜው ዋና የምርትና የሃብት ምንጭ መሬት ስለነበር ያንን በብዛት በጁ ያስገባ የሚኖረው ተደማጭነትና ቦታ ከፍተኛ ነበር።

የተርጓሚው አስተያየት«አሁንም ቢሆን የኤኮኖሚ ቁልፉን ወይም ምንጩን የጨበጠ የስልጣን ባለቤትና የፈለገውን ለማድረግ እንደሚችል የምናየውና የምናውቀው ነው።ይህም ነው ላለፉትና በዘመናችን ለተቀሰቀሱት ግጭቶችና ጦርነቶች ምክንያትና መንስኤ የሆነው።ለወደፊቱም ቢሆን ይህ አሰራርና ልማድ ከቀጠለ፣ገደብና ድንበር ካልተበጀለት አገራት ከአገራት ከመጋጨትና ሕዝብ ለሕዝብ ከመተላለቅ አያመልጡም።»

የአክሱማይት/ሰሎሞናዊ  ሃረግ በይኩኖ አምላክ በኩል አቆጥቁጦ ቦታ እየቀያየረ ተደላድሎ እስከ ሽህ አምስት መቶ ዓ.ም. ድረስ እስከ አጼ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግስት ቆዬ።አጼ ልብነ ድንግል በነገሱበት ዘመን ቀደም ሲል የተጠቀሰው የግብጾችና የቱርኮች ወረራና የመስፋፋት ሙከራ በአገር በቀሉ በግራኝ አህመድ እየታገዘ ብዙ ከባቢዎች በቁጥጥር ስር ዋሉ፤ብዙ ህዝብም ሃይማኖቱን እንዲለውጥና እንዲሰልም ተገደደ።ቤተክርስቲያናትና ደብሮች ተቃጠሉ፣ገዳማትና ንብረቶች ወደሙ።መነኮሳት በጭካኔ ታረዱ።

አህመድ ጉሬይ የአዳል/አፋር/ ሱልጣን/ገዥ የነበረ ሰው እንጂ ተራ ሽፍታ እዳልነበረ ታሪኩ ይነግረናል።ችግሩ ብዙ ጊዜ የታሪክ ጸሃፊዎች የሚወዱትን ሲክቡ የሚጠሉትን ሲንዱና ሲያወግዙ መጻፍ የተለመደ ድክመት በመሆኑ ነው።አህመድ ጉሬይ/ግራኝ/ከሃይማኖትም ባሻገር የአዳል ባለስልጣን ለኢትዮጵያ መንግስት የሚከፍለው ግብር አስመርሮት እንደተነሳ ፣ከገባርነት ለመላቀቅ ያደረገው የእምቢ ባይነት እርምጃ ነበር።

አዳል/አፋር/፣አውሳ፣ሃረር፣ባሌ፣እየተባለ የሚጠራው ኑዋሪ ሕዝብ እርስ በራሱ እየተዋጋና እየታረቀ በጠቅላላው የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ግዛት ሆኖ ይኖር ነበር።እንደተቀረው  የከባቢ አስተዳደር ለአገሪቱ የበላይ ንጉሰ ነገስት ግብርና አስራት ይከፍል ነበር።በዚህም መሰረት አንድ የአዳል/አፋር/ ባላባት/ሱልጣን/ሰባት መቶ(700) ነጭ በቅሎ፣አምሳ(50) የወርቅ ቡችላ፣ሶስት(3) ኮዜ ምንጣፍ (ኮዜ ምን እንደሆነ ላውቀው አልቻልኩም)፣አንድ ሽህ ሶስት መቶ (1300)ሽማ፣ሁለት ሽህ(2000)ሰንጋ( ፍሪዳ)፣ሶስት ሽህ (3000)የበግና የፍየል ሙክት፣ ለንጉሱ ፣ለአጼ ልብነ ድንግል ይገብር ነበር።ይኸንን ግብር ሲገብር ሱልጣኑ ለራሱ ከሕዝቡ ከሰበሰበው ቀንሶ መሆኑን ልብ ማድረግ ያሻል።የሚከፍለው የግብር ግብር መሆኑ ነው።በዚያን ጊዜ ጥሬ ገንዘብ ስላልተለመደ መለዋወጫው ሁሉ ዕቃ በቃ ነበር። በዚህ ዓይነት ስርዓት መኖርና መገበር ያስመረረው የአገሪቱ ዜጋ የሆነው የአፋርና ኢሳ ሱልጣን ሕዝቡን ቀስቅሶ በንጉሱ ላይ አመጸ።በአመጸበት ጊዜ በተለያየ ጊዜ ወደ አገሪቱ የገቡት የአረብ እስላሞች የተባበሩት ሲሆን በተለይም በቱርኮች የሃይማኖትና የግዛት መስፋፋት ፍላጎት ኢትዮጵያን ለመያዝ ብዙ ጥረት እንዳደረጉ ሁሉ ይህ እምቢ ባይነት ጥሩ አጋጣሚ ስለሆነላቸው ትግሉ የሃይማኖት ሽፋን እንዲይዝ በማድረግ የመሳሪያና የወታደር እርዳታ በመስጠታቸው መሪው አህመድ ግራር ድፍረት አግኝቶ ለመዋጋት ተነሳ። ብዙ ጊዜ ድል ሲያደርግ አልፎ አልፎም ድል ሲመታ ለመጨረሻ ጊዜ እስከ ወደቀበት ጊዜ ድረስ ለክርስቲያኑ መሪዎች ውጋት ሆኖባቸው ቆይቷል።

የአጼ ልብነ ድንግል የእህት ባል /አማች /የነበረው ራስ ደጋልሃን/ዴገል/ዋና የጦር አለቃና የባሌም አውራጃ አስተዳዳሪ ነበር።እሱም ብዙ ወታደር አስከትሎ በ1519 ዓ ም.በአዳል መሬት ላይ ከግራኝ አህመድ ጋር ተዋግቶ ብዙ ጉዳት አድርሷል።

የተርጓሚው አስተያየት«ይህ እራሱ በአሁኑ ጊዜ ታሪክን አጣመው ኢትዮጵያ ከተመሰረተች መቶ ዓመት ብቻ ነው፣ ድንበሯም ከአማራ መሬትና ክልል አያልፍም የሚሉትን ለማረምና ትክክል እንዳልሆኑ ለማጋለጥ ይረዳል።»

የኢትዮጵያ ነገስታትና መሪዎች ለአገዛዛቸው የሚጠቀሙት ሃይልን ብቻ አልነበረም፤ብልሃትንና ሰላማዊ መንገድንም ተጠቅመዋል። በጋብቻ  እየተሳሰሩ ቤተ ሰብነትንና ዝምድናን እየፈጠሩ ግጭትንና አለመግባባትና ያሶግዱ ነበር።

በዚህ መንገድ አጼ ዘርዓያዕቆብ ከሃድያ ባላባት የምትወለደውን ጽዮን ሞገሳ የምትባለዋን አግብተው ነበር። እንደዚሁም ልጃቸው በእደ ማርያም እሌኒንና ሮማነ ወርቅን ሁለቱም ከአዳል ባላባት የሚወለዱትን አግብተው ነበር።እቴጌ ሮማነ ወርቅ የአጼ እስክንድር እናት መሆናቸው ነው።እቴጌ እሌኒም ከአጼ በእደ ማርያም እስከ አጼ ልብነ ድንግል ድረስ ባለስልጣን ሆነው የሰሩ ናቸው።

በአስራ አንደኛው መቶ ዓመት  በቱርክ የኦትማን መሪነት የተጀመረው የሙስሊም ሃይል እየተስፋፋ እስከ ቀይ ባህር ዳርቻ መጥቶ በ1510 ዓ ም. የምጥዋን ወደብ ያዘ። የኢትዮጵያ መንግስታት መቀመጫ አክሱምና ላስታ በነበረበት ወቅት ዳር ድንበሩን በተለይም ግዛታቸው በሆነው በሃረርና በአዳል በአውሳም አውራጃ ቁጥጥሩና ግንኙነቱ የላላ ስለነበር፣ቤተ ክህነቱም በትጋት ክርስትናን ባለማስተማሩ፣ከየመንና ከሌላውም የአረብ አገር በንግድ ስም እየገቡ ቁርአንን ለሚያስተምሩ ሰርጎ ገቦች አመቺ ሆነላቸው። ከተወላጇ ሴት ጋር እየተጋቡ ሃይማኖታቸውን አስፋፉ።የሐረርና ከባቢው መሬት በቱርኮች ከዚያም በግብጾች ቁጥጥር ስር አደረ።አሁን በሕዝቡ እምነትና፣ አለባበስ የሚገለጸው ባህል ከዚያው የመጣና የፈለሰ ነው።

ይህ ዘሩ አንድ የሆነው የሴምና የካም ወገን የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነቱን እየዘነጋና እየተወ ሃይማኖትን እንደቁም ነገር እየቆጠረ እርስ በርሱ እየተዋጋ ወደ ሚኖርበት ወቅት ተሻገረ።

በመጀመሪያው ዘመን ላይ የሰው ዘር እንደ እንስሳ/አውሬ/በሚኖርበት ወቅት እምነትና ሃይማኖት አልነበረውም። አሁን ኢትዮጵያ በምትባለዋም አገር መሬት ላይ ይኖር የነበረው የመጀመሪያው የሰው ዘር ከዚህ የተለዬ ኑሮ አልኖረም።ከጊዜ በኋላና በእድገት ሳቢያ በጣኦትና ከዚያም በኋላ በኦሪት ሕግ የአይሁድ እምነት መሠረት ከማምለክ ደረጃ ላይ ደረሰ።

ጊዜ ቆጥሮ የክርስትና ሃይማኖት ወደ አገሪቱ ሲገባና ሲስፋፋ፣በአዲስ መጡና በቆየው የኦሪትና የጣኦት ሃይማኖት ተከታዮች መካከል ግጭትና ጦርነት ቀሰቀሰ።የመጀመሪያ የሆነውን የሃይማኖት ጦርነት በክርስቲያን የአክሱም ነገስታትና በኦሪት እምነት ተከታይ በሆኑት በአገሪቱ ዜጎች መካከል ለተነሳው የርስ በርስ እልቂት ምክንያት ሆነ። በዚህ ሳቢያ የኦሪት እምነትን ይከተሉ የነበሩት ከሺህ ዓመት ከክርስቶስ በፊት በቀዳማዊ ምንሊክ ጊዜ ገብተው ከኑዋሪው ሕዝብ ጋር ተቀላቅለው፣ተዋልደው የተባዙት ኢትዮጵያውያን ከአክሱማዊ ነገስታት እምነት ውጭ መኖር እንደማይገባቸው ተጽእኖው እያየለ ሄደባቸው።በተመሳሳይ ደረጃም በጥንታዊ ፍልስጥኤም በአሁኒቷ እስራኤል ውስጥ የክርስቲያኑ መነሳት ለኦሪት አማንያኑ ስቃይና በደል ስላስከተለ እግራቸው ወደ አደረሳቸው ለመሰደድ ተገደው ነበር።ብዙዎችም ከብዙ ዘመን በፊት በሰላም ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ከተዋለዱትና ከተከለሱት በጊዜ ብዛትም ሙሉ ለሙሉ ኢትዮጵያውያን ከሆኑት የእምነት አጋሮቻቸው ጋር ለመቀላቀል መጥተው ከኑዋሪው ሕዝብ ጋር ተጋብተውና ተዋልደው ቁጥራቸው ለማብዛትና የሚደርስባቸውን በደል ለመቋቋም ከሚችሉበት ደረጃ ላይ ደረሱ ።ከራሳቸው መካከል ጌዴዎን የተባለውን በማንገስ ለአክሱም መንግስት የእምቢ ባይነትን እርምጃ ወሰዱ።አንድ ጊዜ ሲበረቱ ሌላ ጊዜ ሲዳከሙ ከቆዩ በኋላ ንጉሳቸው ጌዴዎን ሲሞት ዮዲት የተባለችውን ሴት ልጁን አንግሰው ትግላቸውን ቀጠሉ።በጊዜው የነበረው የአክሱም ንጉስ አንበሳ ውድም የሚባለው አቅሙ ተዳክሞ አገዛዙ በተልፈሰፈሰ ጊዜ በመሆኑ በዮዲት ተሸንፎ አገሩን ለቆ ወደ ሌላው ግዛቱ ወደ ሆነው ወደ ሸዋ ለመሰደድ ተገደደ።በዚህ ወቅት የክርስትና ሃይማኖት ትልቅ ዱላ አረፈበት፤የመስፋፋቱ ሂደት ተቀጨ።ቤተክርስቲያናትና ገዳማት ተቃጠሉ፤ቀሳውስት ተጨፈጨፉ፣ ተሰደዱ። የአይሁድ እምነት እየገነነ መጣ።ከአርባ ዓመታት አገዛዝ በኋላ ዮዲት ስትሞት ተሰዶ የነበረው ንጉስ ወደ መንበሩ ወደ አክሱም ተመለሰ።

ከሃይማኖቱ ውዝግብና ጦርነት ጎን ለጎን ደግሞ የክልል ጥቅምና ስልጣን ያስከተለው ጦርነት ሌላው ህዝብ አበሳና ስቃይ የሚያይበት ምክንያት ነበር።የአክሱሙን መንግስት የሚፈታተን የዛጉዌ ዘር ነኝ የሚል ሌላ ሃይል በላስታ ተነስቶ ለሶስት መቶ ዓመታት ስልጣኑንና ጥቅሙን ከአስከበረ በኋላ ጊዜና ብልሃት ላነሳው ተረኛ አስረክቦ ሄዷል።( ዝርዝሩ ከላይ የተገለጸ ስለሆነ መድገሙ አስፈላጊ አይደለም።)

በየጊዜው የሚነሳው ሃይማኖት የለዬ ጦርነት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሃይማኖት አሰላለፍን አስከተለ።ከ1300 ዓመታት ወዲህ ለተካሄደው የሃይማኖት ጦርነት ክርስቲያኑ የክርሰቲያኑን እስላሙም የእስላሙን እርዳታና ድጋፍ ያሳድድ ጀመር።

የሃይማኖት መሪዎች በሚያደርጉት ስብከት ሕዝብ በየጊዜው ለሚነሱ ነገስታት ታማኝና ተገዥ ሆኖ ኖሯል። በተለይም የኢትዮጵያ ሕዝብ ለነገስታቱ የነበረው ክብርና ታዛዥነት በጣም ከፍተኛ ነበር። ከመሪነት አሳልፎ ያመልክባቸው ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም። (ከላይ በክብረነገስቱ የተገለጸውን ልብ ይሏል)

የተርጓሚው የጨማሪ ማብራሪያ ነገስታቱ «የአገሪቱ በጠቅላላ የመሬቱም የተፈጥሮ ሀብቱም ባለቤቶች ናቸው። በእያንዳንዱም ዜጋ ላይ የመሰላቸውን የመፍረድ፣ለሚፈልጉት የመስጠትና የመሸለም፣ከማይፈልጉት የመቀማትና የመንሳት ሃይልና ሙብት ነበራቸው። የፈለጉትን ቢያደርጉ "ሰማይ አይታረስ ንጉስ አይከሰስ" በሚለው ሃረግ የተደነገገ ስልጣንና ጉልበት ነበራቸው። ብዙሃኑ በመልካቸው ሳያውቃቸው በስማቸው ፈርቶ ያድር ነበር። ሁሉም ሕይወቱና ኑሮው በንጉሱ መኖር፣ ፈቃድና ፍላጎት ላይ የተንጠለጠለ መስሎ ይታየው ነበር።ንጉሱ ካልኖረ የሚኖር አይመስለውም።አገሪቱም ካለንጉሱ አንድ ቀን እንደማታድር ተደርጎ ነበር የሚታመነው።ሌላው ቀርቶ በአጠቃላይ ንጉስ የተፈጥሮ ባላ እንደሆነ ነበር የሚገመተው፤ያ ባላ ተደርጎ የሚቆጠረው ንጉስ ባይኖር ዓለም እንደሚደረመስ በማዬት ሁሉም ንጉሱን ፈርቶና አክብሮ ማደር ነበረበት።»

በፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት ስለ ክብረነገስት የተገለጸውንየነገስታት ሙብትና ግዴታቸውን ወደሚያሳየው የታሪክ ትንታኔ አመራለሁ።

መጥፎ ንጉስን በሚመለከት ክብረመንግስት እንዲህ ይላል፤-

ንጉሱ ጥሩና የአምላክን ቃል የማያከብር ከሆነ አምላክ ይቀጣዋል።በዓለም ላይ የሚኖርበት ቀን ያጥራል፤ በሰማይም ሲኦል ከሰይጣን ጋር ይጠብቀዋል፣በመሬትም ላይ ጤናና ደስታ አይኖረውም።በፍርሃትና በጭንቀት፣ በሽብር ሰላም የሌለው ኑሮ ይኖራል።

የተርጓሚው አስተያየት-«ከላይ እንደምንረዳው ክብረ ነገስት ንጉሳውያን የሚከበሩበት ብቻ ሳይሆን ሕዝብም የሚከበርበት ሕግና መመሪያ የያዘ የዘመኑ ሕገ መንግስት ነበር ለማለት ይቻላል። ሁሉም የበላይ ፈጣሪ አለብኝ ብሎ የሚያከብረውና የሚቀበለው መተዳደሪያ ነበር።

አገራችን ባሳለፈችው የረጅም ጊዜ ታሪኳ ብዙ የክልል ጉልበተኞችና አመጸኞች እራሳቸውን ንጉስና ንጉሰ ነገስት እያሉ በመሰየም፤የበላይ ሆነው ለመኖር ተቃዋሚና ተፎካካሪያቸውን እያጠፉ መኖራቸው የሚካድ አይደለም። ለዚህም የእርስ በርስ ግጭትና ውጊያ የውጭ አገር መንግስታትን ተገን ማድረጋቸውና ጣልቃ እየገቡ የሚፈልጉትን ለማድረግ የሚያስችል ስምምነትና ውል በመፈራረም በር መክፈታቸው፣ የአገር ጥቅም በስልጣን ጥቅም ለመቀየር መሞከራቸው መዘንጋት የለበትም። ሁሉም የሚጋሩት ነገር ቢኖር ይኸው የስልጣን ፍቅር የሚያስከትለውን ጨካኝነት ነው።የተነሱበት ወቅት ፣ዘመኑ የጉልበተኞች ዘመን ስለነበር ስርዓቱ የጉልበተኞች ስርዓት ነበር።ያሉበት ከባቢ ባለቤቶች፣አዛዥ ፈላጮች፣እነሱ ናቸው፡፡ሌላው እነሱን ለማገልገል የተፈጠረ፤ፈጣሪ አዞና ፈቅዶ የሰጣቸው ዕቃ ይመስላቸው ነበር፡እንጂ እንደነሱ ተፈጥሮ ፣ በእኩልነት ኖሮ የመሞት መብት አለው ብለው ማመን ቀርቶ አያስቡም ነበር።»

በዚያ ገባሪና አስገባሪ የባላባት ዘመን ብዙ ነገሥታትና የከባቢ መሪዎች ነን ባይ አባ ዱላዎች፣አመጸኞች ተነስተው አልፈዋል።ምንም እንኳን ስርዓቱ አንድ አይነት ቢሆንም እያንዳንዳቸው ስርዓቱን ለማሽከርከር የራሳቸው የሆነ ዘዴና ብልሃት ነበራቸው። አልፎ አልፎ በሚነሳ የሕዝብ እምቢ ባይነትና ከጊዜውም ጋር አብሮ መሄድ ስለሚገደዱ ከወረሱት የስርዓቱ ደንብና ልማድ እየወጡ አንዳንድ የጥገና ለውጥ ለማካሄድ ተገደዋል። ሌሎቹን የብዙ ዘመናትን ባላባታዊ ስርዓቶች ትተን በፕሮፌሰር ከተጻፈው ከአጼ ቴዎድሮስ ወዲህ የነበረውን የመሬት ስሪትና የአርሶ አደሩን ኑሮና እጣ ፈንታ ብናይ እንደሚከተለው እናገኘዋለን።

ገበሬው /አርሶ አደሩ/ መደበኛ ግብር ከመክፈሉም በላይ በወታደር ይበዘበዝ ነበር።በ1810-1818 ዓ ም.በትግራይ ውስጥ ይኖር የነበረ አንድ ፒርስ የሚባል የውጭ ታዛቢ እንደዘገበው፤-

ንጉሱ እራሱ ወይም እንደራሴው በቤቱ ውስጥ ተቀምጦ ለጥቂቶች ደግሶ ሲያበላ የቀሩት ባለሟሎቹ በገጠሩ መሬት እየተመሩ ከነዋሪው ግብር እየተቀበሉ፣እንዲጠቀሙ ይፈቀድላቸው ነበር። የአስገባሪና የገባሪ ግንኙነቱ ከገደብ ሲያልፍ የወታደሩ አድራጎት ወደ ውድመት ሲሻገር የህዝብ እምቢ ባይነትን ወለደ። የአንዱ ከባቢ አርሶ አደር ለሌላው ከባቢ እያስጠነቀቀ ጉዳቱን ለመመከት ይሞክር ነበር።መቋቋም ካቃተውና ግፉ ከበዛበት ወደ ንጉሱ ወይም ወደ ገዢው ሄዶ አቤት በማለት ብሶቱን ይገልጻል፤ ንጉሱም ጉዳዩን አይቶና በመልእክተኞች አረጋግጦ የአርሶ አደሩ አቤቱታ እውነት ከሆነ ወታደሩ ከአድራጎቱ እንዲታቀብ ወይም ለዘረፋ ከተመደበበት ቦታ እንዲመለስ ያዛል።ሆኖም ግን አርሶ አደሩ ከጊዜ በኋላ ከሚደርስበት የበቀል እርምጃ ለመዳን ሲል ለዘራፊው የወታደር ሃይል የሚፈልገውን ከማቅረብና ዝርፊያውን ችሎ ከመቀበል የተሻለ ምርጫ አልነበረውም።አለበለዚያ ግን ካጋለጠና እምቢ ካለ ታስሮ ከቤተሰቡና ከእርሻው ተነጥሎ የቤት አገልጋይ ሆኖ ለረጅም ጊዜ ይቆያል። ካስፈለገም ዘራፊው ወገን የውሸት ምስክሮች አሰልፎ የአርሶ አደሩን ክስና ውንጀላ ውድቅና መሰረተ ቢስ ያደርገዋል።አርሶ አደሩ በሕግ መብቱና ለማስጠበቅ የማይደርስበት ተራራ ስለሆነ ከወታደሩ ጋር የሚያደርገው ትንቅንቅ ብዙ መልክና ዘዴ ያካተተ ነበር።ያመረተውን ላለማስነጠቅ ሰፊ ጉድጓድ በመቆፈር ጠባብ አፍ /ቀዳዳ/ብቻ በማስቀረት ምርቱን እህሉን ይደብቅ ነበር።ጉድጓዱ እንዳይታወቅ በእበት በመቀባት /በመለሰን/ኩበት በላዩ ላይ በመከመር ከዓይን ለማራቅ ይሞክር ነበር።

ጉድጓዶቹ የሚዘጋጁት በመንደር ውስጥ ብቻ ሳይሆን ለጥ ባለ ሜዳና መስከ ጭምር ነበር።እህል ብቻ ሳይሆን ጠቃሚና ዋጋ ያላቸውም ንብረቶች ሁሉ ይከተታሉ።አፈርና አቧራ አብሮ እንዳይቀላቀል የጉድጓዱ አፍ በጥንቃቄ በእራፊ ጨርቅ ይሸፈናል።ከዚያ በላይ በጭቃ ይለሰናል።ከመሬት ጋር ይመሳሰላል።በእርሻ አካባቢ ውስጥ ከሆነ

ከእርሻው ጋር ተመሳስሎ ይቆፈራል።የትም ቢሆን ጉድጓዱ የከባቢውን መልክ እንዲይዝ ይሞከራል።በከተማና በመንደር ውስጥ ከሆነ የአመድና የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ለማስመሰል ይሞከራል።ከጊዜ በኂላ ግን የገበሬዎቹ ብልሃት በዘራፊ ወታደሮቹ እየታወቀ መጣ።የወረሩትን ቦታ ከአጠፉና ከደመሰሱ በኂላ በቡድን በቡድን በመሆን የተደበቀውን ለማውጣት አሰሳ ይካሄዳል።ከተጠቀሙበት ዘዴ መካከል የሽለላና የፉከራ ዘፈን እየዘፈኑ በመጨፈር በእግራቸው ሲረግጡት ልዩ ድምጽ የሚያሰማውን መሬት በመለየት በጋሻቸው ዙሪያ ከከበቡ በኂላ በእጃቸውና በጦር እየቆፈሩ የተደበቀውን ማውጣት ነው።ያወጡትን እህል በያዙት ስልቻ /አቅማዳ/ ከሞሉ በኂላ ወደመጡበት ይመለሳሉ።ግን በጉዞ ላይ በሸክም ብዛት ስለሚደክሙ የተወረረው የገበሬ ሕዝብ ከቦ የወሰዱበትን አስጥሎ ያስመልሳል።በዚህ ግርግር ብዙዎች ሞተውና ቆስለው ይቀራሉ። በዚህ ወቅት የሚጠፋው ህይወት በጦርነት ጊዜ ከሚሞተው ቢበልጥ እንጂ እንደማያንስ የታዘበው ፒርስ ይገልጻል።

ከፒርስ በኂላም የመጣው ዋልተር ፕላውዲን የሚባለው ሲመሰክር፣-ምንም እንኳን አንዳንድ ለውጥ ቢኖርም በአጠቃላይ በአርሶ አደሩና በወታደሩ መሃል የነበረው ግብግብ አለማክተሙን ነው።የወታደሩ የዘረፋ ባህል ወደ ሕዝቡ ገብቶና ተዋህዶ የአንዱ ከባቢ ሕዝብ /ገበሬ/ የሌላውን ከባቢ ሕዝብ/ገበሬ/መዝረፍ ለመደ፤ለትውልድ የሚሻጋገር ቂም አተረፈ፤ደም ተቃባ ብሏል።

ሌላውም ታዛቢ የሆነው ደ አባዲ የተባለው ሲመሰክር ብዙው ገበሬ ከእርሻው ይልቅ በጦርነትና በዘረፋ ላይ የተሰማራ ነበር።እርሻና የግብርና ሥራው ለሴቶችና ለልጆች የተወሰነ ሆነ።ብዙ የእርሻ መሬት ጦም አደረ፤ እንስሳት ተበተኑ፣ጠፉ። የዱር አራዊት የሰውን ቦታ ወረሱት፤ዘራፊ ወታደር አገሩን አጠፋው ብሏል።

ሩፔል የተባለውም ይህንኑ በማረጋገጥ ፣ሕዝቦች በአፋጣኝ ደኸዩ፤የመሬት ዋጋ ቀነሰ፣እርሻ ተዘነጋ፣መገናኛዎች ተፋለሱ፤በዚህም የተነሳ የእርሻ ውጤት ዋጋ ከቦታ ቦታ ልዩነት አመጣ።ለምሳሌ ጎንደር ውስጥ በአሥር ብር ይሸጥ የነበረው የእርሻ መሬት ወርዶ ሁለት ብር ተሸጠ።ስዊሳዊውም ሙንዢገር በተመሳሳይ አባባል፣ይህ ተከታታይ ጦርነትና /ሽብር/የማያቋርጥ ድርጊት የአገሪቱን ሃይል አዳከመ፣ንግድ ሕጋዊ ጥበቃ አጣ።እርሻ ተዘንግቶ ማረሻ በጦር ተተካ ሲል ይገልጸዋል።

ይህ ለዘመናት የቆዬ የገበሬ ስቃይ የተስተናገደበት የመሬት ይዞታ በአጼ ቴዎድሮስ ጊዜ በአዋጅ ተፋቀ(ተሻረ)። በ1855 ዓ. ም.በአምባ ጃራ ቤተመንግስት በታወጀው አዋጅ መሠረት ገበሬ ወደ እርሻው ነጋዴ ወደ ንግዱ፣ ወታደሩም ከዘረፋ ታቅቦ የሚፈልገውን እየገዛ እንዲጠቀም ፣ለመጀመሪያ ጊዜ ወታደር በደመወዝ እንዲተዳደር አዘዙ።

እርግጥ አልፎ አልፎ በሕዝቡ ላይ ያደረሱት ጉዳትና ስቃይ ብዙ ቢሆንም ለአገሪቱ አንድነትከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳደረጉና መስዋእት እንደሆኑ መካድ አይቻልም።

አጼ ቴዎድሮስ ከሳቸው በፊት እንደነበሩት መሪዎች ስልጣኑን በጉልበት መውሰዳቸው የሚታበል አይደለም። እንደአለፉት መሪዎች ፣እምቢ ያለውን እያጠፉና እየቀጡ በስራቸው እንዲሆን አድርገዋል።ከስልጣን መውደዳቸው ጎን ለጎን ደግሞ የአገር መውደድ ስሜትና አቋም ነበራቸው።የአገሪቱን ዳር ድንበር ለማስከበርና በዘመነ መሳፍንት የተነጣጠለውን ሕዝብና አገር አንድ አድርጎ ለማቆየት ሲባክኑ፣እላይ እታች ሲሉ ኖረዋል።በዚሁ ጥረታቸው በአደጋ ላይ የነበረውን የአገሪቱን አንድነት ለመጠበቅና የውጭ ሃይሎችንም በመከላከል የህይወት ዋጋ ከፍለዋል። በተጨማሪም ለመጀመሪያ ጊዜ ወታደር በደመወዝ እንዲተዳደር ደንብና ሕግ ያወጡ፣ አራሹን ሕዝብ አይን ካወጣ የወታደር ዘረፋ ያዳኑ በመሆናቸው ከሳቸው በፊት በነበሩት ንጉሶች ዓይን ሲታዩ ዘመናዊ መሪ ነበሩ ለማለት ያስችላል።ምንም እንኳን ወታደሩን በደመወዝ ማስተዳደራቸው ቢታወቅም ምን አይነት ደመወዝ፣ብር ወይም ዕቃ መሆኑን ለማወቅ አልተቻለም።በአመዛኙ ለንጉሱ ከሚገባው ግብር ማለትም ከእህል፣ከእንስሳትና ከመሳሰሉት ጋር የተያያዘ እንደሚሆን ይገመታል።አሞሌም በሳቸውና ከሳቸው በፊትና በኂላ በነበሩት ነገስታት ጊዜ የመገበያያ ዘዴ እንደነበር የሚታወቅ ነው።ምናልባትም በዚሁ በአሞሌ ሳይሆን አይቀርም የወታደሩ የደመወዝ ክፍያ ይካሄድ የነበረው።

የእርሻ መሬቶችን ከዘራፊ ለማዳን በታማኝ ወታደሮቻቸው እንዲጠበቅ አደረጉ።በንግስ ከተማቸውና ከባቢያቸው ብቻ ሳይሆን በሸዋ ግዛታቸውም በመሄድ የነበረውን የመሬት ይዞታ ለወጡ።የቤተክህነትን ይዞታ ቀነሱ።በዚህም ምክንያት ከካህናቱና ከደብተሮች ጋር ተጋጩ።በየደብሩ የቀሳውስቱና የዳቆናቱ ቁጥር በበዓል ቀን ብቻ ሰባት እንዲደርስ፣አለበለዚያ ግን በሰንበትና በሌላው ስነስርዓት ከአምስት እንዳይበልጥ አዘዙ።በተለይም በደብተራ ላይ ትልቅ ጥላቻና ንቀት ነበራቸው፤ሻሽ ጠምጥሞ፣ሥራ ፈትቶ በየከተማው ከሴት አዳሪና ከሰው ሚስቶች ጋር የሚማግጥ ፣ሠርቶ ግብር የማይከፍል፣ወይም እንደወታደር የማይዋጋ፣ወሬኛና አውደልዳይ ይሉት ነበር።

በ1855 ዓ.ም.ዘውድ ሲጭኑ ለወታደሩ ደመወዝ ቆርጠው ፣ከገበሬው እየወሰደ  ለሚጠቀምበት እንዲከፍል አወጁ።ይህንን እርምጃ በጊዜው የነበረው ቻርለስ ቤክ የሚባለው እንግሊዛዊ ታዛቢ ሕዝቡ በሰላም እንዲኖር የረዳና ትልቅ መሻሻል (great reform)ያመጣ እርምጃ ነው ብሎታል።  ይህን ለገበሬው ጥቅም የወጣ ሕግ በተግባር ለመግለጽ በጣም አስቸጋሪ ነበር።ለብዙ ዘመን የቆዬ ፣ስር የሰደደ ባህልም ሆኖ የኖረ ልማድና አሰራር በፍጥነት ከህዝቡ ለማላቀቅ ትልቅ ትግልና መስዋእትነት ጠይቋል።ደብተራ ዘነበ እንደጻፉት፣

ንጉሡ በደላንታ የነበሩ ተከታዮቻቸውን የፈለጋችሁትን ብሉ፤ግን የሕዝቡን ልብሱንና እንስሳቱን አትንኩ፣ አትቀሙት፤በማለት አዘው ነበር።ሆኖም ግን ተከታዮቻቸው /ወታደሮቻቸው/ ይህንን ትእዛዝ በመጣስ ከብቶች እየዘረፉ አርደው በሉ።በዚህ ጊዜ ንጉሡ በመበሳጨት የደሃውን ከብት እንደገደላችሁ ሁሉ አምላክም በናንተ ላይ ተመሳሳይ ቅጣት ያሳርፍባችኋል በማለት በሞት ፍርድ ቀጧቸው።

ቴዎድሮስ ከቤተክህነት ጋር የሚያደርጉት ግብግብ እንደማያዋጣቸውና ሕዝቡም በካህናቱ መዳፍ ስር ስለነበር እረገብ አድርገው እንዲይዙ ስለተመከሩ ለጊዜው እርምጃውን አለሳልሰው ያዙት።ምንም እንኳን ሌላውን ንብረቶች ባይነኩም የቤተክህነቱን ንብረትና ይዞታ የሆነውን መሬት በመንጠቃቸው የካህናቱን ቁጣ ቀሰቀሰ፣ቅዋሜው ከረረ እንጂ አልበረደም።ቀሳውስቱ የንጉሠ ነገሥቱ ባሮች እንዳልሆኑና ትዕዛዙን እንደማይቀበሉ አበሰሩ።ለደሃው  ጥቅም ሲሉ የወሰዱት እርምጃ በፀረ ሃይማኖትነት መደባቸው። በሚሰበስቡት ግብር ወታደራቸውንና አገሪቱን ለማሻሻል የነደፉትን አያሌ ውጥኖች ለማካሄድ ይገለገሉበት ነበር።በዚህ ውጣ ውረድ በበዛበት ወቅት ንጉሥ ቴዎድሮስ ኑሮአቸው ከተራ ሕዝብ አይነት የተሻለ አልነበረም።የቄሶቹ አትንኩኝ ባይነት ተቃውሞ ለኋላኋላ ለተከሰተው የንጉሥ ቴዎድሮስ መውደቅ ከዋናዋናዎቹ ምክንያቶች አንዱ ሆነ።ምንም እንኳን የሚወስዱትን የለውጥ እርምጃ ሕዝቡ ቢደግፍላቸውም ለተከሰተው አያሌ ተቃውሞ ካህናቱና ጳጳሱ ዋና ቀስቃሽና አንቀሳቃሽ ነበሩ።ቴዎድሮስ በእንግሊዞች ተወግተው ሲሸነፉ ወጥነውት የነበረው የለውጥ ጎዳና ተቀለበሰ፤ከሰመ።ከሳቸው በኋላ ቀጥሎ የላስታው ተወላጅ ዋግ ስዩም ጎበዜ አጼ ተ/ጊዮርጊስ ተብሎ ስልጣኑን ያዘ።ይህ የከባቢ ንጉስ ነኝ ባይ በቴዎድሮስ የተነጠቁትን የቤተክህነትና የቀሳውስት መሬት መልሶ በመስጠት ክብርና ድጋፍ ለማግኘት ሞከረ። በዚህም እሱ እውነተኛ ክርስቲያን ተብሎ በቄሶች ዘንድ ምስጋናና ውዳሴ አገኘ።

ከአጼ ቴዎድሮስ ቀጥለው በኢትዮጵያ በንጉሰ ነገሥትነት ስልጣኑን የያዙት በንግስና ስማቸው አጼ ዩሃንስ አራተኛ ተብለው የሚታወቁት የትግራዩ ደጃች በዝብዝ ካሳም እንዲሁ እንደነበሩት ነገስታት በጎና መጥፎ ጎን ነበራቸው።እሳቸውም የስልጣኑ ባለቤት የሆኑት በጉልበትና በከባቢ ሽኩቻ የበላይነቱን በማግኘት ነው።የንጉስ እምነት የግዴታ የሕዝቡ እምነት እንዲሆን፣ንጉሱ የሚወደውን እንዲወድ የሚጠላውን እንዲጠላ የሚያስገድድ ልማድና ሕግ በሰፈነበት አስተዳደር ሕዝብ በነጻ የሚወስነውና የሚያደርገው ነገር የለም።አጼ ዩሃንስ አክራሪ የኦርቶዶክስ አማኝ በመሆናቸው እሳቸው ከሚከተሉት እምነት ውጭ የሚያምን ሰው በግዛታቸው የመኖር፣ የመሬት ባለቤት የመሆን መብት አልነበረውም።በትንባሆ ጎራሽና ክርስቲያን ባልሆነ ሰው ላይ የነበራቸው ጥላቻ ከፍተኛ ስለነበረ ፣በግዛቴ ውስጥ እንዳይኖር የሚል ጠንካራና አስደንጋጭ አቋምና መመሪያ ነበራቸው። ዐፄ ዩሃንስ አገሪቱን በአንድ ክርስቲያን እምነት ሥር ለማድረግ ከፍተኛ ፍላጎት ነበራቸው።ከግብጽ ጋር በሚዋጉበት ጊዜ በ1875 ዓ.ም. ሁሉም እስላም ክርስቲያን እንዲሆን አለበለዚያ ግዛታቸውን ለቆ እንዲወጣ በአዋጅ ደነገጉ።በዚህም የተነሳ በአደዋና በአካለጉዛይ አካባቢ የሚኖሩ የእስልምና ተከታዮች ክርስቲያን በመሆን እርስታቸውን ያድኑ ነበር።መሬትም ያልነበራቸው የመሬት ባለቤት ለመሆን በቁ። እነዚህ ብዙዎቹ ለይስሙላ ሃይማኖታቸውን የለወጡ ዜጎች "የቀን ክርስቲያን የማታ እስላም" በትግርኛውም ማልቲ ክርስቲያን ላይቲ

እስላም "እየተባሉ ይተቹ ነበር። እንደተባለውም የአፄ ዩሃንስ ሥልጣን ሲያከትም የነሱም ክርስትና አብሮ አከተመ። ተመልሰው ሰለሙ።ከመሬታቸው ላይ ግን አልተነቀሉም።

በአፄ ዩሃንስ ዘመነ መንግሥት የመሬት ይዞታ በመሻሻሉ የሴቶች እርስት የመካፈል መብት በሕግ ታወቀ። የሃማሴን ግዛታቸው እንደራሴ የነበሩት እራስ አሉላ ጭምር የንጉሱን ትዕዛዝ በመቀበል የርስተ ጉልትን ሕግ በማውጣት በሥራ ተርጉመውታል። በደንቡና በወጣው ሕግ መሠረተ 'ሰው ነጻ ነው፣መሬት ግን ገባሪ ነው"በሚለው መመሪያ ግብር የሚገበርበት መሬት የገባሪው ቋሚ ንብረትና ከትውልድ ትውልድም ሊሸጋገር የሚችል ይዞታ መሆኑ ተረጋገጠ። "የአርባ ዓመት መብት" በሚልም መመሪያ ሥር ለአርባ ዓመት በይዞታ ስር የቆዬ መሬት በይርጋልህ እንዲሰጥ ተደነገገ። ከአርባ ዓመት በላይም ከርስቱ የተፈናቀለውም ተመልሶ በርስቱ ላይ መቀመጥ እንደሚችል ዋስትናና መብት የሚሰጥ ሕግ ወጣ።ይህም በእስልምና ሃይማኖታቸው የተነሳ ከመሬታቸው ተፈናቅለው የነበሩት ዜጎች ተመልሰው የመሬታቸው ጌታ እንዲሆኑ አብቅቷቸዋል። በትግራይ ውስጥ በነበረው ተለምዶና አሰራር እስላሞች የመሬት ባለቤት የመሆን መብት አልነበራቸውም ነበር።በአባባልም እስላም የለው መሬት ሰማይ የለው መሠረት ይባል ነበር።በትግርኛም አስላማይ አዲ ያቤሉ፣ሳማይ አይዲ ያቤሉ ይባል ነበር።

አፄ ዩሃንስ ለአገሩ ተወላጅ ብቻ ሳይሆን ለውጭ አገር ዜጎችም የመሬት ባለቤትነት መብትና ፈቃድ ሰጥተው ነበር።በተለይም ኪርክሃም ለተባለው እንግሊዛዊ የጦር አማካሪያቸው በጊንዳ የሚገኝ ሠፊና ለም መሬት ሰጥተውት እንደነበርና እሱም ከውትድርናው ይልቅ የግብርናውን ሥራ አሳምሮ እንደያዘውና ቅድሚያ እንደሰጠው የጊዜው ታዛቢ ያገሩ ተወላጅ የሆነው ዊልድ የተባለው በጻፈው የታሪክ መዝገብ ላይ ገልጾት ይገኛል።

አፄ ዩሃንስ ምንም እንኳን በግል ስሜትና ፍላጎት የሚያድሩና የሚያስተዳድሩ ቢሆንም በአገራቸው ጉዳይና ነጻነት እንዲሁም አንድነት የማያወላውል አቋም ነበራቸው። በየጊዜው የቀይ ባህርን ድንበር ጥሰው ለመውረር የመጡ ቱርኮችን እየወጉ መልሰዋል። ሆኖም ግን ዘላቂ ሰላም ሊሰፍንና እሳቸውም ሆኑ ሕዝቡ ከዘመቻ ሳያርፍ በውጭ ሃይል በተለይም በግብጾችና በስከጀርባም በእንግሊዞች ድጋፍና ትብብር በሱዳን በኩል የተሰነዘረውን የማህዲስት(የእስላሞች) ወረራ ለመቋቋምና ለመመለስ እንደ አንድ ወታደር ጦር ሜዳ መሃል ገብተው ሲዋጉ በመተማ ህይወታቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል።

ቀጥለውም ስላጣኑን የወሰዱት ሳህለ ማርያም ወይም የንግሥና ስማቸው አጼ ምንሊክ እንዲሁ ከሳቸው በፊት እንደነበሩት የከባቢ አባ ዱላዎች በጉልበት ስላጣኑን ከአባት ወደ ልጅ በመወራረስ የተረከቡ ናቸው።የስልጣን አያያዙ ብዙም ባይለይም ስልጣን ላይ ከወጡ በኋላ ግን በሰሩት ስራ ከሌሎቹ ይለያሉ።እኚህ ንጉስ ስልጣን ላይ የወጡበት ዘመንና የዓለም ሁኔታ የተለዬ ወቅት ስለነበር ከሳቸው በፊት ከነበሩት መሪዎች የተለዬ የአመለካከት ዝንባሌና እድል ነበራቸው።በአውሮፓ የኢንዱስትሪ አብዮት(industrial revolution) አድጎ የከበርቴው ስርዓት ቀደም ሲል በቅኝ ግዛት ያልያዛቸውን ሌሎቹን የክፈለ ዓለም አገራት በመዳፉ ስር ለማዋል እርስ በራሱ የሚፎካከርበትና መረቡን የዘረጋበት ወቅት ነበር።በዚህም የተነሳ በመጀመሪያ ደረጃ ሰላማዊ ግንኙነትን እየመሰረተ ለዘላቂ አላማው ዝግጅት ያደርግ ነበር።እንደነ ሚኒሊክ ያለውን ጊዜ ያነሳውን መሪ ወዳጅ መስሎ በመጠጋት ለወደፊት ዓላማው መንገድ ለመጥረግ መካሪና ደጋፊ እየሆነ፣ሲያስፈልግም የመሳሪያ እርዳታ እየለገሰ የእርስ በርሱ ግጭት እንዲቀጥል ያደርግ ነበር።እንደ አሁኑ ጊዜ እርስ በራሳቸው የሚፎካከሩትን የከባቢ አባ ዱላዎች እንደሚያመቸው እየተጠጋ፣አንድ እንዳይሆኑ ወይም አንዱ ጠንካራ እንዳይሆን በሚስጥር እየከፋፈለ መስራቱ የጊዜው ስልት ነበር።አሁንም ቢሆን የምዕራብና የከባቢ አገሮች ከሌላው አገር ለሚያገኙት ጥቅም መከላከያ መሣሪያ አድርገው የሚጠቀሙበት ይኸው በሌላው አገር ላይ የሚያስቀምጡት ተጽእኖና የውስጥ ችግር ማባባስ ስልት ነው።

በአውሮፓ የከበርቴው ስርዓት ማደግ በውስጡ ይዟቸው የመጣው የኤኮኖሚና የአስተሳሰብ ለውጥ የሚኒሊክን አስተዳደር ቀልብና ልብ ስቦት ነበር።ምንም እንኳን ባይናቸው ባያዩትም በሚሰሙት በመማረክ ባገራቸው ውስጥ ተመሳሳይ እድገት እንዲታይ ፍላጎት ነበራቸው።ከአውሮፓ መንግስታት በተለይም ከእንግሊዝ፣ከኢጣልያ፣ ከፈረንሳይ፣ከመስኮብ፣ከጀርመን፣ከሌሎችም መንግስታት ጋር የወዳጅነት ግንኙነት፣የንግድና የሌላም ስምምነት ያደርጉ

ነበር።ለንግድ ዘርፉ የሚሆኑትንም አሰራሮችና ተቋማት በመመስረት የመጀመሪያው ሆኑ።በኢትዮጵያ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በአውሮፓውያን በተቋቋመው የኢጅብት ባንክ ስር የተቋቋመውን የአቢሲኒያ ባንክ በ1906 ዓ.ም.በይፋ መርቀው ከፈቱ።በ1907 ዓ.ም.የመጀመሪያ የሆኑትን ሁለት ካሚዎን የመጓጓዣ መኪናዎች ወደ አገር በማስገባት ለመጠቀም ቻሉ። በ1908 ዓ.ም.በስማቸው የዳግማዊ ምኒሊክን ት/ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ከፈቱ።በ1910 ዓ.ም.በስማቸው የሚጠራውን"የዳግማዊ ምኒሊክን" ሃኪም ቤት፣በተከታዩም ዓመት በ1911 ዓ.ም የመጀመሪያውን ማተሚያ ቤት አቋቋሙ።የስልክና የፖስታ ቤት ከፈቱ። በተከታታይ የኤሌክትሪክ፣የስፌት መኪና፣የእንጨት መሰንጠቂያ መሳሪያ፣የእህል ወፍጮ፣የሳሙና ፋብሪካና የመሳሰሉትን እያስመጡ በማሰራት ለውጥ አሳይተዋል። ከዕቃ ለዕቃ ልውውጥ ገበያም ምስላቸው ያረፈበት ገንዘብ በማሳተም ሰራተኞች በደመወዝ እንዲተዳደሩ አድርገዋል።

በሳቸው ዘመነ መንግስት በአገሪቱ ውስጥ ይሽከረከር የነበረው የመገበያያ ገንዘብ ከአሞሌ ጎን ለጎን በኦስትሪያዋ ንግስት በነበረችው በንግስት ማርያ ተሬሳ ስም ይታተም የነበረው  በአገራችን ሕዝብ አጠራር ማርትሬዛ፣ የድንጋይ ብር ወይም ጠገራ ብር በመባል የታወቀው ከንጹህ ብር የተሰራ የውጭ አገር ገንዘብ ነበር።ይህ በቪዬና ከተማ ታትሞ የወጣ ገንዘብ በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቀ ነበር።

በ1894 እ.አ.አ.የመጀመሪያ የሆነው የምንሊክ ታለርስ ለጥቅም ሲውል፣የመዳብ ፍራንክም ተሰርቶ ለገበያ ዋለ።በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት አካባቢ የአቢሲኒያ ባንክ ወደ አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሽህ ጠገራ ብር ወደ ኢትዮጵያ አስገብቶ ያንቀሳቅስ ነበር።ይህ ከንጹህ ብር የተሠራ ገንዘብ ለረጅም ጊዜ እስከአሁንም ድረስ ለጌጣጌጥ መስሪያ አገልግሎት ሲሰጥ ኖሯል።

የተርጓሚው ተጨማሪ ማብራሪያ-«ይህንን የማርትሬዛ ጠፍጣፋ ብር እኔም በዕድሜዬ የደረስኩበትና የማውቀው በተወለድኩበት በደሴ ከተማ ሸርፍ ተራ በሚባለው የምንዛሬ ንግድ ቦታ በመላክ የመነዘርኩት ነው።በዛን ጊዜ የምንዛሬው ተመን አንድ ማርትሬዛ ብር ሁለት ብር ከሃምሳ ወይም አምስት ሽልንግ ነበር።እዚህ ላይ መዘንጋት የሌለበት ነገር በኢትዮጵያ ውስጥ የገንዘብ መፈጠርና መሽከርከር በአፄ ምኒሊክ እንዳልተጀመረ ነው፤፤ ቀደም ሲል በሳባውያን  የጉብስ ዘለላ የተሳለበት የወርቅ ሳንቲም በጥቅም ላይ ውሎ እንደነበር የታሪክ ማስረጃዎች ቀርበዋል።ይህን በሚመለከት በዶር.አሰፋ እንደሻው "ኢትዮጵያ፣የሕዝቦች ስብጥርና የአገዛዞች አወቃቀር አጭር ታሪክ"በሚል እርእስ የተጻፈውን አነስተኛ የታሪክ መጽሃፍ ማንበቡ የበለጠ ግንዛቤ ይሰጣል።»

 አፄ ምኒሊክ የቀየሱት የለውጥ ሂደት በሌላውም ያገሪቱ ጉዳይና አሠራር ልማድና ባህል ላይ የተዳረሰ ነበር። አገሪቱ ከአንድ ንጉሰ ነገስት ውሳኔና ፈቃድ ይልቅ እንደ አውሮፓውያኑ የስራ ክፍፍል ተደርጎ በካቢኔ መልክ መንግስት የሚዋቀርበትን የመጀመሪያ የካቢኔ አሰራር ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተዋወቁና ሚኒስትር ቢሮዎችን ያቋቋሙ መሪ ናቸው።በዚህም መሰረት፣-

1ኛ አፈንጉስ ነሲቡ የፍርድ ሚኒስቴር

2ኛ.ፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ የጦር ሚኒስቴር

3ኛ.ሊቀ መኳስ ከተማ ያገር ግዛት ሚኒስቴር

4ኛ.ነጋድራስ ሃይለ ጊዮርጊስ የውጭ ጉዳይና የንግድ ሚኒስቴር

5ኛ. በጅሮንድ ሙሉጌታ የገንዘብ ሚኒስቴር

6ኛ. ከንቲባ ወ/ጻድቅ የርሻ ሚኒስቴር

7ኛ.አለቃ ገብረ ስላሴ የጽህፈት ሚኒስቴር

8ኛ.አዛዥ መታፈሪያ የግቢ ሚኒስቴር

9ኛ.ቀኛዝማች መኮንን ተወንድ በላይ የስራ ሚኒስቴር

10ኛ.የስልክ አገልግሎት ሚኒስቴር ሳይሾምበት በአዋጅ ተቋቁሞ ልጅ በየነ ይመር ተሹመውበት ነበር።ይህ እንግዲህ የመገናኛ ሚኒስቴር መሆኑ ሳይሆን አይቀርም

11ኛ የትምህርት ሚኒስቴር ተቋቁሞ ነበር ግን የተሾመበት ሰው ለጊዜው አልነበረም።

የተረጓሚው አስተያየት-«እርግጥ አመዳደቡና የሰዎቹ ምርጫ በዘመናችን እንደምናየውና እንደምናውቀው የዲሞክራሲን አሰራር በችሎታና የሕዝብን ድምጽና ምርጫ በተከተለ መልክ አልነበረም፤ አሁንም አልፎ አልፎ እንደሚታየው ለንጉሱ ወይም መሪ ነኝ ብሎ ስልጣኑን ለያዘው ግለሰብና ቡድን ታማኝ አገልጋዮችና ታዛዥ ለሚሆኑ ሰዎች የሚሰጥ የመጠቃቀሚያ ስጦታ ነበር።ሆኖም ግን ካለፉት አሰራሮች የተለዩና የዘመኑ ትልቅ እምርታ ነበር።»

ለአድዋ ጦርነት ሁለት ዓመት ሲቀረው አጼ ምኒሊክበምክር ይረዳቸው ለነበረ ለፈረንሳዩ ተወላጅ ለሆነው መሃንዲስ ለሙሴ ኢልግ፣በመጋቢት 1 ቀን-1886ዓ.ም ከጅቡቲ እስከ ሃረር፣ከሃረር እስከ እንጦጦ፣ከእንጦጦ እስከ ከፋ ከዚያም እስከ ነጭ አባይ ድረስ የሃዲድ መንገድ እንዲዘረጋ በውል ፈቅደውለት ነበር፤ በተጨማሪም ከጅቡቲ ወደ ሃረር ከሃረር ወደ ጅቡቲ ሸቀጥ የማመላለሱ ብቸኛ መብት ለዚሁ መሃንዲስ ማህበር ብቻ የተፈቀደ ነበር።ከሚወጣውም ከሚገባውም ሸቀጥ ቀረጥ ከመቶ አስረኛውን እንዲያገኝ ተፈቅዶለት ነበር።ይህ ውል የሚጸናው ለዘጠና ዘጠኝ ዓመት ሲሆን ጊዜው ሲደርስ ማህበሩ ለስራው ያወጣውን ገንዘብ ሳይጠይቅ የሃዲዱን መንገድ ከሙሉ መሳሪያው ጋር ለኢትዮጵያ መንግስት ለቆ እንዲሄድ በአንቀጽ ሰፈሮ ተስማምተውበት ነበር።

የተረጓሚው አስተያየት-«ይህን የመሰለው ሰፊና ትልቅ የመገናኛ ዕቅድ እንደታሰበው ሙሉ ለሙሉ ሳይዘረጋ ከጅቡቲ እስከ አዲስ አበባ ድረስ ባለው ሃዲድ ብቻ ተወስኖ ቀረ።ከመጀመሪያው ያገልግሎት ዓመት ጀምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ትርፍ እንጂ ምንም አይነት ኪሳራ ያልገጠመው ድርጅት ገቢው በባለስላጣኑ የግል ካዝና እየገባ እንኳንስ ሊያድግና ሊስፋፋ ቀርቶ የነበረው የባቡር ፉርጎ ሳይለወጥ እንደጫጨ ቀረ።ከዚያም አልፎ አሁን የሚሰጠው አገልግሎት ተቆራርጦ ከናዝሬት አላለፈም።እንኳንስ ከመቶ አስራ አምስት ዓመት በላይ እድሜ ያለው የባቡር መስመር ቀርቶ የአስር ዓመት ዕድሜ ያለው ተመሳሳይ ድርጅት በቅጡ በመያዝ የት እንደሚደርስ ከእኛ አገር በኋላ ለዚህ አይነት ዕድል የበቁትን እያዩ መገመት ይቻላል።በእኛ የረዥም ታሪክ ጉዞ የተለመደው ግን አንዱ በሰራው ላይ ሌላው ከሚቀጥልበትና ከሚጨምርበት ይልቅ በማፍረሱና በመሰባበሩ ላይ የሚያሳየው መተባበር ነው።ይህ የማፍረስ ባህል አሁን ላለንበት ዝቅተኛና የሚያሳፍር ኑሮ ዳርጎናል"ከዚህስ በኋላ ወዴት ያመራን ይሆን?»

ዐጼ ምኒሊክ ሌላው በብዙሃኑ የሚመሰገኑበት፣በጥቂቶች ክልላውያን የሚወቀሱበት ትልቁ ስራ በዘመነ መሳፍንት የተከፋፈለው ሕዝብና አገር ቴዎድሮስና ዩሃንስ ለማዋሃድና እንደ ጥንቱ አንድ አገር ለማድረግ የወሰዱትን እርምጃና ሙከራ ለዳግመኛና ለመጨረሻ ጊዜ መስዋእት ተከፍሎ ያደረጉት አስተዋጽኦ ነው።በዚህ በተበታተነና ክልላዊ አባ ዱላዎች በሚፈነጩበት ጊዜና መሬት የሚኖር ሕዝብ ከመበታተንና ለውጭ ወራሪ አመቺ ከመሆን እንዲተርፍ በአንድ መንግስትና በአንድ አገር ዜግነት እንዲኖር በማድረግ ኢትዮጲያ የምትባል አገር በቀጣይነት ለእኛ ትውልድ እንድትደርስ አብቅተዋል። የኢትዮጵያ ማእከላዊ መንግስት ተዳክሞ ዳር ድንበሩ ተደፍሮ መሃሉ ሳይቀር በክልል አባ ዱላዎች ተነጣጥሎ የኖረውን ያገሪቱን ግዛት በውድና በሃይል እያሳመኑ አረጋግጠዋል። እንደገና በማሰባሰብ በአንድ መንግሥታዊ አስተዳደር ሥር እንዲውል አድርገዋል።በአሚር አብዱላሂ ቤተሰብ ቁጥጥር የነበረውን የሀረር ክ/ሃገር ከግለሰብ ስልጣን እጅ እንዲወጣና በመካከለኛው መንግስት ስር ተመልሶ እንዲገባ አድርገዋል። በራስ መኮንን አዝማችነት ከሃረርም አልፎ ኢሳንና ውጋዴን አልፎ እስከ ሶማሌ ወሰን ድረስ ያለውን የተበታተነ በመሰብሰብ ከዚያም ከፋሌ ጀምረው የሺሆጀሌን ግዛት ወደ ኢትዮጵያ መልሰው እስከ ሱዳን ጠረፍ ያለውን የኢትዮጵያ መሬት አስከብረዋል።

በደጃዝማች ተሰማ ናደው አዝማችነት በኢሉባቦር በኩል ያለውን አገር የባሮን መሬት እያቋረጡ እስከ ሶባትና ነጭ አባይ ድረስ ያለውን የአገር ክልል አስከብረዋል።

ራስ ወ/ጊዮርጊስ ደግሞ ከፋን፣ኮሎን፣ሊሙን፣ከዚያም እስከ ነጭ አባይ ድረስ አልፈው የኢትዮጵያን ግዛት ተቆጣጥረዋል።

ፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ በቦረና በኩል እስከ ኬንያ ድረስ ያለውን አገርና ሕዝብ ኢትዮጵያዊነት አረጋግጠዋል።

የተርጓሚው አስተያየት-«እንግዲህ ምኒሊክም ሆኑ ከሳቸው በፊት የነበሩት ነገስታት በተለይም አጼ ቴዎድሮስ የተበታተነውን አገር መልሶ ለመሰብሰብ ያደረጉት ጥረትና ዘዴ በሌላው ዓለም በተለይም በአውሮፓ አገሮች የተካሄደውን የአገር ግንባታና የማእከላዊ መንግስት አመሰራረትን የተከተለና የሚመሳሰል እንጂ ባሕር አቋርጦ የሄደ የውጭ ወራሪ ሃይል የፈጸመው ድርጊት አይደለም።ለዚህ አገራዊ ግንባታ በአንድነት የሚያምኑ የየክልሉና የየማህበረሰቡ ተወላጆች ተካፍለውበታል፤ የሕይወት ዋጋም ከፍለውበታል።ካለከባቢው ተወላጆች ድጋፍና ተሳትፎ ለአንድነት የተደረገው ትግል ውጤት አይኖረውም ነበር።

በዘመኑ ያገሪቱ መንግስት የሃብት ምንጭ መሬት ነበር፣ አሁንም ወደፊትም ይኸው ነው።አገር፣መንግስትና መሬት አይነጣጠልም።አገር ማለት መሬት መሬት ማለት አገር ነው።በአገር ላይ የሠፈረው ሕዝብ ደግሞ የመሬቱ ና የአገሩ የጋራ ተጠቃሚና ባለቤት ነው።በአግባቡ ተጠቅሞ ለሚከተለው ትውልድ ጠብቆ የማስረከብ አላፊነትና አደራ አለበት።»

እያንዳንዱ መንግሥት በግዛቱ ሊኖርና ሊያድር የሚገባውን መሬት ጊዜው በሚጠይቀው መንገድ አስከብሮ ሕዝቡ ሊጠቀምበትና ሊተዳደርበት የሚችልበትን ሕግና ደንብ ያወጣል፤ ያወጣው ሕግ በውድም ሆነ በግድ ተግባራዊ እንዲሆን ይሞክራል።ምኒሊክም በጊዜአቸው የመሬት ስሪትን ለማሻሻልና ለመለወጥ እርምጃ ወስደዋል።

የመሬትን የባለቤትነት መብትና ግዴታ በሚመለከት የሚከተሉትን አሠራሮች ተከትለዋል።

1ኛ.-በጦርነት መልክ የተያዙ/የተወሰዱ/መሬቶች

2ኛ.-ባለቤት የሌላቸው ጠፍና ሌጣ መሬቶች

3ኛ.-በወንጀል ሥራ ወይም አመጽ ላይ ከተሰማራ ሰው ላይ የሚነጠቁ መሬቶች

4ኛ.-የመንግሥት ባለሥልጣኖች መሬት

5ኛ.-የቤተክህነት መሬት

6ኛ.የገባርና የባላባት መሬት

ከጥቂት የሥልጣን ዓመታት በኋላ ንጉሥ ምኒሊክ ሰፊና ትልቅ የፖለቲካ ሃይል ገንብተው ነበር፤የፈረንሳይ ተልዕኮ ቡድን በ1901-1903 ታዛቢ የነበረው እንደገለጸው የመንግሥቱ ሥልጣን ገደብ ቢስ ነበር፣ሕዝቡም አገሪቱም የንጉሱ የግል ንብረቶቹ ነበሩ ሲል ገልጾታል።

በጊዜው መሬትን የመውረስና የመንጠቅ እርምጃ እንደቅጣት የሚወሰድ የበቀል እርምጃ ነበር።ከሳቸውም በኋላ እስከ አሁን ድረስ ይህ አሠራር ሲሰራበት ቆይቷል።የመንግስት ደጋፊና ተከታይ ያልሆነ ከቦታው ሲወገድ፣ ሲታሰር፣ ሲፈታ፣ሲሰደድ ማየቱ በሌላውም በኩል መሬት ለሚወዱትና ለሚያምኑት የሚሰጥ ገጸበረከትና ሽልማት ሆኖ ኖሯል።

ከላይ እንደተገለጸው ምኒሊክም ሆኑ ከሳቸው በፊት የነበሩት መሪዎች አገሪቱን አንድ አድርገው ለማስተዳደር የወሰዱት እርምጃ አሁን በምዕራቡ አገር አንድ ሆነው የምናያቸው አገሮች የጥንት መሪዎች ከወሰዱት ጋራ የሚመሳሰል እንጂ የተለዬ አይደለም።እርግጥ በአፈጻጸምና በስልት ደረጃ እንደቦታው፣እንደመሪው ብስለትና እንደሕዝቡ ባህል ይለያያል።

የምንሊክ የደቡብና የደቡብ ምዕራብ ክፍለ ሃገር መልሶ መያዝ በሚመለከተው ሄንሪ ብላንክ የተባለው ተጓዥ እንግሊዛዊ ሲገልጸው፣-በ1860ኛው ዓመት ላይ ከጋላ/ከኦሮሞ/ ጋር ተዋግተው ድል ባደረጉ ጊዜ በመዝረፍና በመበዝበዝ ፈንታ በደግነትና በጨዋነት የአክብሮት አያያዝ፣ከራሱ ጎሳ መሪዎች በተሻለና ለዘብ ያለ አስተዳደር ስላሰፈኑለት ሕዝቡ ያልጠበቀው ስለነበር በመደነቅና በማክበር የሚያስፈልገውን አነስተኛ የዓመት ግብር እየከፈለ ለመኖር ተስማምቶ አገዛዛቸውን ተቀብሎ አደረ።ግንኙነቱ ከጠላትነት ወደ ወዳጅነትና ወደ አጋርነት ተለውጦ ለሚያደርጉት ዘመቻና ውህደት ተባባሪና ተከታይ ለመሆን በቃ።ይላል።ከአንድ ትውልድ በኋላ የመጣውና የታዘበውም ሌላው የእንግሊዝ ወታደራዊ ባለሥልጣን ሻለቃ አውስቲን ተመሳሳይ አመለካከት ነበረው። ሲመሰክርም፣-በሚኒሊክ አስተዳደር ጋሎች/ኦሮሞዎች/ የበለፀጉ ነበሩ፤በማለት አስተዳደሩና መንግሥቱ በሕዝቡ የተደነቀና ለሕዝቡ የተስማማው፣በአስራ ሰባት ዓመት ውስጥ ብዙ ለውጥ ያሳዬ መሆኑን ገልጾታል። የቀድሞ የባህላዊና ጎሳዊ አስተዳዳሪዎችና ባለሥልጣኖች/ባላባቶች/ይዞታቸው ሳይነካ የመንግሥት አካል ሆነው ይሠሩ ነበር።ሌላው ቀርቶ የጋላ/የኦሮሞ/ሴቶች ቀድሞ በትውልድ የሚገባቸው የሥልጣንና የንብረት ውርስ መብታቸው ሲከበር የተነፈጉት የመሬት ባለቤትነታቸውም መብት ታውቆላቸው ነበር ይላል።

ዳግመኛ በተቀላቀሉት ክ/ሃገሮች የነበረው ሁኔታ ከቦታ ቦታ ይለያያል።አንዳንዱ ክ/ሃገር ምኒሊክን ወዶና ፈቅዶ ሲቀበል፣የሃገሩ ተወላጅ የሆኑት ባላባቶችና አስተዳዳሪዎች ሥልጣናቸው ሳይነካ እንዲቀጥሉ፣የሕዝቡም የነበረ የኑሮ ዘይቤና ግንኙነት ሳይደፈርስና ሳይለወጥ እንዲቆይ ሲደረግ እምቢ አሻፈረኝ ብሎ የሚያምጸው ክ/ሃገር ላይ ግን የንጉሡ ባለሟሎችና ረዳቶች አስተዳደሩን በመውሰድ የሥልጣኑ ባለቤቶች ይሆኑ ነበር። ምንሊክን በመቀበል የነበረው ባህላዊ አስተዳደር ሳይነካ ተከብሮ የቆየባቸው ክ/ሃገሮች፣-በምዕራብ ቤኒሻንጉል፣ወለጋ፣ጅማና ከፋ ሲሆኑ በምሥራቁም የአውሳ ግዛት ነበር።በነዚህና በሌሎቹም የሰላም ውህደት በተፈጸመባቸው ከባቢዎች እንደተቀሩት የሰሜን ክ/ሃገሮች ትግሬ፣ጎጃም፣ወሎና ቤጌምድር የመሬት ይዞታው ሳይለወጥ በነባሩ ሕዝብና ባህላዊ አስተዳደር ፣የከባቢው ባላባቶች መዳፍ ስር ነበር።

የግብጾችን ወረራ ተከትሎ በሐረር የነበረው ባህላዊ አስተዳደርና አሰራር በምንሊክ/በራስ መኮንን/አስተዳደር በተተካ ጊዜ ሳይለወጥ አንዳንድ የጥገና ለውጦች ብቻ ተካሂደውበት ነዋሪው ሕዝብ ረክቶና ተደስቶ ይኖር ነበር። በተለይም በኋለኛው ንጉሠ ነገሥት በቀ.ሃ ሥላሴ /በተፈሪ መኮንን/እንደራሴነት ወቅት የገባሩን ሸክምና ቀንበር ለማቃለል በሰኔ ወር 1903 ዓ.ም. /May12-1910/አንድ አዲስ መመሪያ አዋጅ አውጥተው ነበር።ይህም መመሪያ ገባርና ጭሰኛው በኑሮው ተማርሮና ተንገሽግሾ ለገዢው አቤቱታውን ባሰማ ጊዜ ያወጡት ነበር።ጭሰኛና ገባሩን በማጽናናት ለምን እራሳችሁን አስጨንቃችሁ በብዛት ወደ እኔ ትመጣላችሁ? አሁን የዝናብ ጊዜ ነው፤ሄዳችሁ እረሱ።ይህን የማያደርግ /የማይቀበል/ ካለ አስር ዳውላ እህል እንዲቀጣ እወስንበታለሁ። ባላባቱ ጌሾ አምጡ፣እህል ጫኑ ብሎ ቢያዛችሁ አትቀበሉት፣ እምቢ በሉት።ለእኔ አንድ አህያ የማገዶ እንጨትና አንድ ቁና ዱቄት በየወሩ ይበቃኛል።ቤት እንድትሠሩ ፣አጥር እንድታጥሩ ብትጠየቁ እምቢ በሉ፣አትሥሩለት።ሲሉ ለገባሮቹ ትዕዛዝና መመሪያ ሰጡ።ይህ እራሱ በጊዜው ገባሩን ከባላባቱ መዳፍ ለማላቀቅ የተደረገ አዲስ እርምጃ ነበር።

ገባሮቹ ይህንን መመሪያ በሰሙ ጊዜ በማድነቅ እያለቀሱ እራስ መኮንን ቢሞቱም አላጣናቸውም፣ለደሃ የነበራቸው ፍቅርና ደግነት /ሰብአዊ ልቦና/በልጃቸውም ላይ ሰፍኗል፤እያሉ ወደመጡበት ተመለሱ።ሲል ይህንን የታዘበው የፈረንሳይ ሚሽነሪ በጋዜጣው አምድ ላይ አስፍሮት እንደነበር የታሪክ ገጽ ይመሰክራል።

በቡና ምርት በታወቀው ከሓረር በስተ ምዕራብ በሚገኘው በጨርጨርም ተመሳሳይ ለውጥና የመሬት ስምሪት ተካሂዶ ነበር።ከሚኒሊክ ጊዜ በፊት በግራኝ ወረራ ጊዜ ወደ እስልምና የተቀየረው የኢቱ ጋላ/ኦሮሞ/ማህበረሰብ

በባህሉ መሬት የቤተሰብ ይዞታ ሆኖ አንድ ወንድ ልጅ 18 ዓመት ዕድሜ ሲሞላው እስከሚሞት ድረስ በግሉ የሚጠቀምበት መሬት ይሰጠው ነበር።በአባ ቡርካ ወይም የከባቢ መሪ ተይዞ የነበረው መሬት ተራ ቤተሰብ ይይዘው ከነበረው በስፋትም በልማትም ስለሚበልጥ የተዛባና አድልኦ የተሞላበት ይዞታ ነበር።እራስ መኮንን ሕግ በማውጣት የነአባ ቡርካን ይዞታ በመቀነስ ወደ አንድ ጋሻ በማውረድ ቀሪውን ለተቀረው ሕዝብ አከፋፈሉ። ደመወዝና ሌላ መተዳደሪያ ላልነበረው ወታደርና የመንግሥቱ ሠራተኛ በሥልጣን ተዋረድ የሚመጣጠን መሬት በርስትነትና በማደሪያነት/ከሥራው ሲሰናበት የሚመልስው ይዞታ/መልክ አደሉ።ለገዳማትና ለቤተክርስቲያኑም ቀሳውስት የሚሆን መሬት ተመደበ።

ቡርካዎች የዱሮ የጋላው/ኦሮሞው/ ባህላዊና ባላባታዊ መሪዎች በቁጥጥራቸው ሥር በነበረው አካባቢ/መሬት/ ላይ የአዲሱን አስተዳደር አሰራር ያግዙና በተግባርም ይተረጉሙ ነበር።ግብር ይሰበስቡ፣ለወታደሩ ስንቅና ድጋፍ ይሰጡ፣ሕዝቡንም ለሥራና ለወታደራዊ ዘመቻ /ግዳጅ/ያስተባብሩ ነበር።በዚህ ትብብራቸውና ጥረታቸው ከግብር ነፃ እየሆኑ ፣ክብርና ጥቅማቸው ተጠብቆላቸው ይኖሩ ነበር።ገባሩም ባስፈለገ ጊዜ ስንቅና መጓጓዣ እንዲያቀርብላቸው የሚያስችል መብት ነበራቸው።የኋላ ኋላ ግን ቡርካዎቹ መሬታቸውን እየሸጡ የሥልጣን ደረጃቸውን ብቻ በማስከበር ለመኖር በመወሰናቸው ለመግዛትና ለመክፈል የሚችለው የመሬቱ ጌታ እየሆነ መጣ።እነዚህ የግል መሬት ባለሃብቶች ለመንግሥት መክፈልና ማስገባት ከነበረባቸው ግብርና መስጠት ከሚኖርባቸው አገልግሎት ነጻ አልነበሩም።ሠላምና ጸጥታን በማስከበር፣መንግሥቱንና ቡርካዎችን ያግዙ ነበር። በቀውስና በድንገተኛ አደጋ ወቅት እራሳቸውንና ተከታዮቻቸውን /ቤተሰባቸውን/በማንቀሳቀስ፣በጦርነትና በግጭትም ጊዜ የራሳቸውን መሣሪያና ተዋጊ በማቅረብ፣በከባቢያቸው ለሚያልፍና ለሚያርፍ ዘማች ስንቅና ድጋፍ በማበርከት ፣በሰላምም ጊዜ የመንግሥት ቢሮዎች፣መንገዶችንና ቤተክርስቲያኖችን በመገንባትና በማነጽ ይተባበሩና ይሳተፉ ነበር።

አልፎ አልፎ የውጭ ታዛቢዎችና መርማሪዎች የገባርን ትርጉም በማጣመም ከባሪያ ወይም ከአገልጋይ ጋር ያመሳስሉታል።ምንታዶን የተባለ የውጭ ዜጋ ግን ገባር ማለት ለመንግሥት ወይም ለአስተዳደሩ ግብር/ ታክስ/፣ ለሚጠቀምበት ኪራይ እየከፈለ የሚኖር ማለት ነው። የመንግሥት ባለሥልጣኖች፣ቀሳውስትና ወታደሮችም ገባሮች ናቸው ብሏል።

የእንግሊዝ ቆንስል የነበረውም ወከር ሲገልጽ ገባር ማለት የሚገብር/ግብር የሚከፍል/ማለት ነው።ሌላው ቀርቶ ምንሊክም ለመንግሥት ግብር ይከፍላሉ፤ስለሆነም እሳቸውም ሆኑ የቀሩት ባለሥልጣኖች ጭምር ገባሮች ናቸው። የግብሩ አይነትና ብዛት የሚገበርለት ሰው ወይም ክፍል ይለያይ እንደሁ እንጂ በተግባር ያው የመገበር ግዳጅ የሚመለከተው ሁሉ ገባር ነው ማለት ነው።በአጭሩ ለሚገለገሉበት ወይም ለሚጠቀሙበት ነገር የሚከፍሉት ኪራይ ወይም አበል ማለት ነው።በዘመናችን በሌላው አገር አባባል ግብርና ግብር ከፋይ( Tax and Tax payer) እንደማለት ነው።

የገባሪ ገባሪም እንዳለ መዘንጋት የለብንም።ይኸኛው ገባሪ ከማለት ጭሰኛ ማለቱ ይቀላል።ይኸውም አንዱ ለተሰጠው/ለያዘው/ መሬት ለመንግሥት ግብር የሚከፍለው  መሬቱን ለሌሎች አሳልፎ በመስጠት እንዲያርሱና በተስማሙበት ግምት መሰረት  አበል የሚቀበል ከሆነ ያ የገባሪ ገባሪ በመሬቱ ላይ የመቆየት ሕጋዊ መብት ስሌለለው ባለመሬቱ ወይም ባለመተዳደሪያው ባሻው ጊዜ ሊያሰግደው ይችላል።

የገባሪና ያስገባሪ ግንኙነትና መብት ከቦታ ቦታ ይለያያል።ከከተማና ከመንግሥቱ ማዕከል በራቀ ቁጥር የገባሩ በተለይም የጭሰኛው ግዴታ እየበረከተ፣ግንኙነቱ ከሰውነት እየራቀ ይሄዳል። ጭራሽ የመልከኛው/የባለመሬቱ /የግል ንብረትና አገልጋይ እየሆነ ይመጣል።ከእርሻ ሥራው በተጨማሪ ብዙ ግዴታና ሥራዎች ማሟላት ይጠበቅበታል። ይህን ያልተቀበለና የመረረው በልዩ ልዩ መልክ ተቃውሞውን ይገልጻል።ወይ አገር ቀይሮ ይሄዳል ወይም እምቢ አሻፈረኝ ብሎ ያምጻል፣ይሸፍታል።

ምንም እንኳን በዚህ መደብ ነክ ግንኙነት በተመሰረተ ግጭት ላይ የተመዘገበ ምንጭና ማስረጃ ባይኖርም በ1880 ዓ.ም. ላይ ጎራ በል በተባለው በአንኮበር አካባቢ በሚገኘው ቦታ የሚኖሩ ጭሰኞች አመጽ ቀስቅሰው ነበር።ኢጣሊያናዊው ተጓዥ ማሪቲኒ እንደገለጸው 500 የሚሆኑ ጭሰኞች ጦርና ጋሻ ታጥቀው አምጸው እንደነበር ያወሳል። ምንም እንኳን ይህንን አይነት እንቅስቃሴዎች ተደጋግመው ባይታዩም በሚያዝያ ወር 1917 ዓ.ም.በወታደሮችና በአርሶ አደሮች የተቀናጀ አድማ ተካሂዶ የካቢኔ አባላትና ሚኒስትሮች እንዲወገዱና ለጊዜውም ቢሆን እንዲርቁ አድርጎ ነበር።

በአርሶ አደሩ ሕዝብ፣በተለይም በጭሰኛው ላይ የሚደርሰውን በደልና ስቃይ በሚኒሊክ ዘመነ መንግሥት በውጭ አገር የትምህርት ዕድል አግኝተው የወጡት የአማራው ማህበረሰብ ምሁራንም አጥብቀው ይቃወሙ፣ይተቹና ያጋልጡ ነበር።ከነዚህም አንዱ በስዊዘርላንድና በጣሊያን አገር የተማሩት አፈወርቅ ገ/እየሱስ ነበሩ።በ1908 ዓ.ም.የኢትዮጵያ የጉዞ መረጃ/guide du voyageur en Abyssinie/ በሚለው በሮም ውስጥ በታተመ መጽሄት ላይ የፊውዳል/የባላባት/ ሥርዓት በአገሪቱ ውስጥ እስካለ ድረስ እኩልነትም ሆነ ነጻነት ይኖራል ማለት ዘበት ነው።የሸዋ ጭሰኛ በባለሥልጣኖችና የከባቢ ባላባቶች አላግባብ ሲንገላታና ሲቀጣ ቤሳ ቤስቲኒ ሳይቀረው እንደሚዘረፍ እንዲህ በማለት ለመግለጽና ለማሳየት ሞክረዋል።ጭሰኛው ከሚገደድበት የከፋ ሥራዎች ውስጥ እህል ፈጭቶ፣ዱቄቱን ፣ላሙን አልቦ ወተትና ቅቤውን ፣ማሩን ቆርጦ፣ተሸክሞ መልከኛው ወይም ሹሙ ቤት ያደርሳል፤በዛም አያበቃም እንጨት ለማገዶና ለቤት መሥሪያ ይቆርጣል፤አጥር ያጥራል፣በወረራ ጊዜ የአለቃውን መሣሪያ/ጠመንጃ/ድንኳንና ስንቅ ተሸክሞ ይከተላል።ሹሙ ያዘዘውን ሁሉ ያደርጋል ሲሉ የምሬትና የሃዘን ትችታቸውን ሰንዝረዋል።ሌላው በጀርመን አገር የተማሩት ኢትዮጵያዊ ገብረ ህይወት ባይከዳኝ የተባሉትም ምሁር ተመሳሳይ አስተያየት ሰጥተዋል።በአገራችን የአርሶ አደሩ ኑሮ በጣም ከባድ ነው።በማለት ይጀምሩና፣ ማረሻውን ከማንሳቱና እርሻ ከመጀመሩ በፊት የመንግሥት ዘበኛ ይመጣና የመሬት ግብር ይጠይቀዋል።ከከባድ የቀን ሥራ በኋላ ወደ ቤቱ ሲመለስ ሚስቱ በወታደሮች ተደፍራና ተደብድባ ፣ምግብ እንድታዘጋጅ ተገዳ ስታለቅስ ያገኛታል። በማንኛውም ጊዜና ቦታ በአለቃዎች/በሹሞች/ሲታዘዝ የራሱንየእርሻ ስራውን ትቶ በቅድሚያ የነሱን ሥራ ለመሥራት ይገደዳል።ለዚህ መፍትሄው አራሹ ሊከፍል የሚገባው ግብር በዘመናዊ መንገድ ሆኖ በምርቱና በገቢው መጠን በገንዘብ ክፍያ እንዲሆን፣ ያለው ኋላ ቀር ግንኙነትና ክፍያ ማሶገድ ነው ብለው ነበር።

የግብር ክፍያው የሚወሰነው በከባቢው ሹም ነው።የሚከፈለውም ግብር ከቦታ ቦታ ይለያያል።የሚከፈልባቸው ወቅቶች በዓመት ውስጥ የፋሲካን፣የመስቀልንና የገናን በዓላት ተንተርሶ ነበር።የሚከፈሉት የግብር አይነቶች ደግሞ

1ኛ.-በደጋው ከባቢ፣-ቅቤ፣በግ፣ፍየል፣በቅሎ፣ ሸማና በርኖስ

2ኛ.-በቆላውና በበረሃው/ጫካማ/ከባቢ፣-ማር፣ቅቤ፣የቀንድ ከብትና ጥሪኝ

3ኛ.-በአባይ፣ሩዶልፍ ሓይቅና በኦጋዴን፣-የዝሆን ጥርስ፣የአንበሳና የነብር ቆዳ፣ጥሪኝ፣ቅቤና ጥጥ

ከጊዜ በኋላ ይህ ክፍያ ወደ ገንዘብ እየተለወጠ መጣ።የጉልበት ሥራ ምንም እንኳን እንደ ግዳጅ ባይቆጠርም መሬቱን ለማረስ ፍቃድ ለማግኘት ሲባል ማባበያና ማግባቢያ አድርጎ ገበሬው ይጠቀምበት ነበር።

በየአይነቱ የሚከፈለው ግብር በቀጥታ ከመንግሥት እጅና ካዝና አይደርስም ነበር።ለከባቢው ሹምና አስተዳዳሪ ግምጃ ቤት ገቢ ሆኖ ተከታዮቹንና በሥሩ የተኮለኮሉ ረዳቶቹን ፣ወታደሮቹን፣ቤተሰቦቹን ለመንከባከብና ለማስተዳደር ይጠቀምበታል። በአንዳንድ ድግሶችና ልዩ ልዩ አጋጣሚዎች የሹሙ ቤተሰብ ሲወልድ፣ ሲያገባ፣ ሲሞት፣ለክርስትናው ለሠርጉና ለተስካሩ የቅቤ፣የሰንጋ፣የማር፣የቡና፣የሸማ፣የበርኖስ የአንበሳና የነብር ቆዳ ስጦታ ማቅረብና መስጠት የተለመደ  የውዴታ ግዴታ ነበር።

ታሪክ ጸሃፊው አቶ ማህተመ ሥላሤ በተለያዩ ቦታዎች ይሰበሰቡ የነበሩትን ግብሮች እንደሚከተለው አመልክተዋል።

በውርጅ ውጫሌ፣-ሦሥት ዳውላ እህል/አንድ ዳውላ ሃያ ቁና ነው/፣አንድ ጉንዶ ማር፣አንድ ሙክት

በራጀት፣-የመንግሥቱን የእርሻ መሬት/ሁዳድ/ ማረስና በተጨማሪም አንድ ጉንዶ ማር

በባኮ፣-ሶስት ዳውላ እህል፣አንድ ጉንዶ ማር፣ሸክም የማገዶ እንጨት

ወላሞና ከምባታ፣-በየወሩ አምስት ቁና እህል፣አንድ ቁና ጌሾ፣አንድ ጭነት የማገዶ እንጨት፣በተጨማሪም በየዓመቱ አምሳ ጉንዶ ማርና በከባቢው የሚሠሩ ጌጣጌጦችና የቤት እቃዎች ማለትም፣ገንቦ፣ድስት፣ምጣድ ወፍጮ፣ሙቀጫ፣ሰፌድ ቁናና ሞሰብ እንዲሁም አዲስ ሹም በመጣ ቁጥር አንድ ብር ለየበዓላቱ ደግሞ ስሙኒ ይከፍል ነበር።

በኢሉባቦር፣-ሶስት ዳውላ እህል፣ከአምስት እስከ ሰባት ብር የሚያወጣ ወለላ ማር

በጠቅላላ በአገሪቱ ዙሪያ የተለመደው የግብር መጠን ከመቶ አሥር እጅ (10%)የሆነው የእርሻው ምርት ነው። ይህም በአማካኝ ከሰባ አምስት እስከ መቶ ዘጠና አምስት ኪሎ እህል ይደርሳል።በአንዳንዱ ክ/ሃገራት የሚከፈለው ግብር መጠን ከዚህ የተለዬ ነበር።ለምሳሌ

የጁ የእራስ ወሌ ግብር አሥር እጅ (10%) ሲሆን፣ወደ ሰሜኑ ሲዘልቁ እስከ ሃያ እጅ(20%) ይደርሳል።ይህ የአስርና የሃያ እጅ ግብር በጣምም የሚያስከፋ አልነበረም፤የሚያስመርረው ነገር ግብር ሰብሳቢው በመጣ ቁጥር ለራሱ የሚጠይቀው ድጎማና እጅ መንሻ፣ዘማች አዝማቹን ተከትሎ በከባቢው በገባ በወጣ ቁጥር የሚጠይቀው ቀለብና መስተንግዶ የገበሬውን/የአርሶ አደሩን ጓዳ ያራቆተውና ኑሮውንም የከፋ ያደረገው ነበር።

አፄ ምኒሊክ ቀድሞ ሲሰራበት የነበረውን በትውልድ እየተወራረሰ የሚሄደውን የመሬት ባለቤትነት ልማድ እንደገና እንዲያንሰራራ ወሰኑ።በዝዋይና በአዋሽ መካከል ያለው የጋላ/የኦሮሞ/መሬት ለወታደሩ በርስትነት እንዲረጋለት አዘዙ።ወንጀለኛ ጭምር ንብረቱ እንዲዘረፍ ቢፈቀድም የመሬት ባለቤትነት መብቱ በሕጉ ተጠብቆለት ነበር።ከአስር ዓመትም በኂላ በ1903-4 ንጉሱ ተጨማሪ ሕግ በማውጣትና በማዘዝ በአባታቸው በሳህለ ሥላሤ ጊዜ በተነሳው ጦርነትና ውጊያ ምክንያት መብታቸውን አጥተው የነበሩት የጋላ/የኦረሞ/ተወላጆች እንደገና የመሬት ባለቤትነታቸው መብታቸው እንዲታወቅ "እኔ በምገዛት አገር ውስጥ የጋላ/የኦሮሞ/ባላባት ልጆች የእኩልነት መብት አይጣስም"በማለት መሬቱ በጋላው/በኦሮሞው/ና በአማራው መካከል ልዩነት ሳይኖር እንዲከፋፈል አደረጉ።

የተርጓሚው አስተያየት-«ምንም እንኳን የባላባታዊው ሥርዓት በውስጡ የያዘው ጎጂና አስከፊ ልማድና አሰራር ቢኖረውም የዛው ስርዓት አንቀሳቃሽ የሆኑት መሪዎች የተበታተነውንና በከባቢ ባላባቶች ሲበዘበዝ የኖረውን ሕዝብ በአንድ መንግስታዊ ሥርዓት ስር ሰብስበው፣በአንድ አገር ዜግነት አዋቅረው ኢትዮጵያ ለረጅም ዘመናት በባእዳን ስር ሳትረገጥ በነጻነት አቆይተው ማለፋቸው የሚያስመሰግናቸው ነው።

ይህንን የሚቃወሙ ለምን እንደተበታተን፣በከባቢ ባላባትና አባዱላዎች ስንበዘበዝና ተረግጠን አልኖርንም፣ በሚኒልክ ፈንታ በንጉስ ጦና፣በአባ ጅፋር፣በደጃች ጆቴ፣በነአሚር አብዱላሂ ወዘተ..እየተቀጠቀጥን ፣ከትልቅ አገር ዜግነት በትንሽ ክልል ታስረን አልኖርንም ብሎ መጥበብና በጠባቡ ማዬት ነው።ከዚህ አይነቱ ውዥንብርና የጠባብ በሽታ ለመዳን የዓለም ሃገሮችንና የማዕከላዊ መንግስትን አመሰራረት ለማወቅ ጆሮና አዕምሮን መክፈት ከብዙ ስህተት ያድናል።መቸም ምንም ቢሆን ወደ አለፈና ኂላ ቀር ዘመነ መሳፍንት ፊቱን ለማዞር የሚሻ ጤነኛ አእምሮ ያለው ኢትዮጵያዊ አይኖርም።በየትውልዱ አቅምና ችሎታ የነበረው እየተሻሻለ ይቀጥላል እንጂ የተመሰረተ ነጻ አገር መፍረስ አይኖርበትም፤ችግሩ ኢትዮጵያዊነትና አንድነት ያመጣው ሳይሆን ስርዓት የወለደው ነው። የሚበጀውንና ለህዝብ የሚጠቅመውን ስርዓት አስፍኖ የተሻለችና ጠንካራ ኢትዮጵያን መፍጠር እንጂ ያለፈ ብሶት

እንዲያገረሽና ህዝብ እርስ በራሱ እንዲተላለቅና ለውጭ ሃይል ሰለባ እንዲሆን ማድረግ ትልቅ ወንጀል እንደሚሆን መረዳቱ ጠቃሚ ነው።አንዱt ጠፍቶ ሌላው በሰላም ሊኖር እንደማይችል መታወቅ አለበት።»

## ስለ አዲስ አበባ ከተማ አመሰራረት

የአዲስ አበባ ከተማ መመሥረት እንደ ቀድሞው ከተሞች አክሱምና ጎንደር በአገሪቱ ታሪክና ሂደት ላይ ትልቅ ለውጥና አስተዋጽኦ አምጥቷል።የአዲስ አበባ በከተማነት መመሥረት ምኒሊክ የሸዋ ንጉስ በነበሩበት ጊዜ የተቀመጡበትን አንኮበርን ለቀው በአንጦጦ አካባቢ ውቃቃ በተባለው ኮረብታ ላይ ከመስፈራቸው ጋር የተያያዘ ነው።ምንም እንኳን በእንጦጦ ላይ ከተማቸውን ለመመሥረት ፍላጎት ቢኖራቸውም፣ ልባቸው ቢከጅልም የእንጦጦ መልከዐ ምድርና ተራራማነት ለመገናኛና ለመጓጓዣ አዳጋች፣ በተጨማሪም ነፋሻና ብርዳማ ስለነበር ለከተማነት አመቺ ሆኖ አልተገኘም። ስለሆነም ወደ ሌላ ቦታ ለመንቀሳቀስ ፍላጎት ነበር።እቴጌ ጣይቱ ብጡል የንጉስ ምንሊክ ባለቤት ዐይናቸውን የጣሉበትና የተማረኩበት ከባቢ ከእንጦጦ ባሻገር ከዝቅተኛው/ከረባዳው/መሬት ላይ ነበር።

የተርጓሚው አስተያየት-«ቦታው ላይ ፊኒን እያለ(እየፈነነ)የሚወጣ ውሃ/ጠበል/በመኖሩ ምክንያት በሕዝቡ አጠራር ፊኒኔ ወይም ፊንፊኔ ይባል እንደነበረ ታሪኩን የሚያውቁ ሰዎች ይመሰክራሉ።አሁንም በቅርቡ የአዲስ አበባ ከተማ ጥንት ሸገር ተብሎ ይጠራ እንደነበር ለመታወቅ ተችሏል።ለዚህ ፍንፊኔ ለሚለው አጠራር እንደማስረጃ ያህል ለማቅረብ፤ በተጨማሪም ጨዋታን ጨዋታ ያነሰዋል ይባላልና በተመሳሳይ መንገድ እኔ የተወለድኩበት መንደር ስም እንዴት እንደመጣ ታሪኩን ጠቀስ አድርጌ ባልፍ ለአንባቢው የበለጠ ግንዛቤ ይሰጣል ብዬ አምናለሁ።

የተወለድኩት ደሴ ከተማ ሳላይሽ ተብሎ በሚጠራው ሰፈር ውስጥ ነው።የሰፈሩ አጠራር የመጣው በአደዋ ዘመቻ ጊዜ የአፄ ምኒሊክ ጦር ወሎ ውስጥ ወረኢሉ በሚባለው ቦታ እንዲሰበሰብና ጉዞውን ወደ ሰሜኑ እንዲቀጥል በወጣው አዋጅና ጥሪ መሠረት የጦር አበጋዞችና መሪዎች ከነጭፍሮቻቸው በዛው በተባለው ቦታ ተሰበሰቡ።ወደ ሰሜኑ የጦር ሜዳ ለመሄድ የግድ በደሴ ከተማ በኩል ማለፍ ነበረባቸው።ከዘማች መሪዎቹ መካከል አንዱ እራስ (ለጊዜው ስማቸውን አላስታወስኩትም)አድዋ ደርሰው በድል አድራጊነት  ሲመለሱ እንደመጀመሪያው ጊዜ በደሴ ማለፍ ሳይሆን አዳርም አድርገው ነበር።ድንኳናቸው የተተከለውና እረፍት ያደረጉበት ቦታ እኔ የተወለድኩበት መንደር ነበር።ደጃዝማቹ ከመንገድ እንዳረፉ የሚጠጣ ውሃ ይጠይቃሉ፤ በቀንድ ዋንጫ የቀረበላቸውን ውሃ ጭልጥ አድርገው ከጠጡ በኋላ እንዲደገማቸው ይጠይቃሉ ፣ተደገማቸው። ከዛም እንዲህ ያለው ውሃ ከየት መጣ ብለው ሲጠይቁ ከዚሁ ሠፈር ከሚመነጭ ምንጭ የተቀዳ ነው የሚል መልስ አገኙ፤ ደጃዝማቹም በመገረም«ለካስ ወደ አድዋ ስሄድ ትልቅ ነገር አምልጦኝ ኖሯል፤ ምንም እንኳን በቦታው ባልፍም ቦሩ ሜዳ ገብቶ ለማደር በመገስገሴ ይህን የመሰለ ጣፋጭና የሚያረካ ውሃ ለመቅመስ አልቻልኩም ነበር፤ሳላየውና ሳልቀምሰው አልፌዋለሁ፤በሉ ከአሁን በኋላ ምንጯን "ሳላይሽ" ብላችሁ ጥሯት አሉ ይባላል።ከዚያ በኋላ ሠፈሩ በደጃዝማቹ በተሰየመችው ምንጭ በሳላይሽ ለመጠራት በቃ።ይህን ታሪክ የነገረችኝ ወላጅ እናቴ ነች።ሌሎችም ታሪኮች ማታ ማታ እሳት ዳር ሆነን ቆሎ እየቆረጠምን ነግራኛለች። ከዛም ከማስታውሳቸው መካከል በአስተዳዳሪዎች ያልተደሰተው ሕዝብ እንዲነሱለት አድማ እንደሚያደርግ እንዲህ ጠቅለል አድርጋ ነግራኛለች።አንድ ባለሥልጣን ሕዝቡን ስላሰቃዩት ሕዝቡ በአድማ ይነሱልንና በምትካቸው የእገሌ ልጅ እገሌ ይሁንልን ብሎ ይጠይቃል። ለጥያቄው የበላይ ባለሥልጣን መንግሥት መልስ በመስጠት በምትኩ የጠየቁት ሰው  እንዲሾም ያደርጋል።የተሾመው ሰው ከበፊቱ የከፋ ይሆናል። በዚህ ጊዜ ሕዝቡ በእንጉርጉሮ እንዲህ በማለት ብሶቱን ገለጸ ስትል ነገረችኝ።እናቲ ፊደል ባትቆጥርም የዕድሜ ምሁር ነበረች፤ነፍሷን ይማረውና!!!

ይምጣ ይምጣ ብለን ያመጣነው አልጋ፤

የማያስኮረትም የማያዘረጋ።

በሌላውም ጊዜ ሕዝቡ ጉቦ መስጠት መረረውና እንዲህ ሲል ገጠመ ብላ ነግራኛለች፤

ለምስለኔው ሙክት ለጭቃው ወጠጤ፣

እየገበርኩ ነው ባገር መቀመጤ።

አምላኩንም ሲማጠን

ሁሌ ለተሾመ ከምታሰግደኝ

ወይም አንተ ውረድ ወይ እኔን ውሰደኝ።

አዎ ብዙ ጊዜ ወይም አልፎ አልፎ የተሞኙት በጎ ነገር ይቀርና በምትኩ የባሰ ችግር ውስጥ መግባት የተለመደ ነው።የቀዳማዊ ሃይለስላሴ መንግሥት እንዲወድቅ ስንመኝ የተተካው ዓይን ያወጣ ግድያ የሚፈጽመው አረመኔው ደርግ ነበር።በእሱ ስንማረር ተተከቶ የመጣው ሕዝብን በጎሳና በክልል ከፋፍሎ መከራ የሚያሳየው ጎጠኛ ፣ጸረ አንድነት የሆ አሁንም በስልጣን ኮርቻ ላይ የተቀመጠው ቡድን ነው።ለወደፊቱ ደግሞ ምን ይመጣ ይሆን?ጥያቄ አቅርቦ መቀመጡ ሳይሆን ተመሳሳይ ጨቋኝ፣ በዝባዥና አስበዛዥ ቡድን፣የነጠላ ቡድን የበላይነት፣ዘርና ክልልን መሠረት ያደረገ ሃይልና ስብስብ ሥልጣን ላይ እንዳይወጣ በህብረት መከላከል ነው።የአገር አንድነትና የሕዝብ እኩልነት የሚረጋገጥበት ህጋዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለማምጣት በህብረት መታገል ነው።»

እንግዲህ የአዲስ አበባ ከተማም  አልፎ አልፎ ፊንፊኔ በሚለው አጠራር የሚታወቀው ፊኒን እያለ በመውጣቱ በሕዝቡ ፊኒኔ ተብሎ ይጠራ በነበረው ውሃ/ጠበል/የአሁኑ ፍልውሃ በሚገኝበት ከባቢ ሳቢያ ለመሆኑ በአብዛኛው መልኩ ይመሳሰላል።

የነበረውን አጠቃላይ መልክ የታሪክ መዝጋቢው ገ/ሥላሤን በመጥቀስ ፕሮፌሶር ሪቻርድ እንዲህ ሲሉ ያቀርቡታል፦

በክረምቱ ወራት በ1886 ዓ.ም. ንጉሥና ንግሥቲቱ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ፍል ውሃ ለጠበል ሄደው በከባቢው ብዙ ድንኳኖች ተተከሉ።ንግሥት ጣይቱ ባላቸውን አፄ ምንሊክን በዛ ከባቢ ቤት ለመሥራት እንዲችሉ ፈቃድ ጠየቁአቸው።ንጉሡም አሁን የቤት መሥሪያ ቦታ በኋላ ደግሞ አገር እሰጥሻለሁ ሲሉ ፈቀዱላቸው።ንግሥቲቱም የት ቦታ ላይ ልሥራ ብለው ባላቸውን ቢጠይቋቸው፣ምኒሊክ በእጃቸው እየጠቆሙ፣ከዛ አባቴ፣ንጉስ ሣህለ ሥላሤ በአጥር ከልሎ ካስቀመጠው ቦታ ላይ ሥሪ አሏቸው ብለው ጸሃፊው ይገልጻሉ። ቀጥለውም ምንሊክ ስለአባታቸው ምኞትና ትንቢት አብረዋቸው ለነበሩት መኳንንት   "አባቴ ከዛ ዛፍ ስር ገበጣ እየተጫወቱ በነበረበት ጊዜ እንደ ትንቢት አንተ ቦታ ወደፊት የልጅ ልጄ ከተማ ይመሠርትብሃል" ብለው ተናግረው እንደነበር ገ/ሥላሤ ገልጸዋል።

በማግስቱ እቴጌ ጣይቱ የሚፈልጉት ቤት እንዲሠራ ትዕዛዝ ሰጡ።በሚቀጥለውም ዓመት በ1887 ዓ.ም.የቤቱ ሥራ ተጠናቆ እቴጌ ጣይቱ ከእንጦጦ ለቀው ከጠበሉ በላይ ከተሠራው ወደ አዲሱ መኖሪያ ቤታቸው ተንቀሳቀሱ።አብሯቸው የተንቀሳቀሰው አጃቢ እንደየማዕረጉ እያራራቀ የግል መኖሪያውን ሠራ።የከባቢው መልክ ተለወጠ።የሚያምር መንደር ሆነ።በዚያም ወቅት ነው የከባቢውን ማማርና ለውጥ የተገነዘቡት እቴጌ ጣይቱ አዲስ አበባ የሚል መጠሪያ ስም ያወጡለትና መጠራት የጀመረው።

ከግማሽ መቶ ዓመት በኋላ የወጣው የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት መግለጫ እንደሚያሳየውና የመጀመሪያው ከንቲባ ፊታውራሪ ደምሴ ወ/አማኑኤል እንደገለጹት በፊንፊኔ ዙሪያ የነበረው መሬት እንደ ግለሰቡ የሥልጣን ደረጃና ለንጉሡ እንዳለው አቅርቦት እንደሚከተለው ተደልድሎ ነበር።

ልዑል ራስ መኮነን፣ንጉስ ሚካኤል፣ራስ ወልዴ፣ፊታውራሪ ሀብተ ማርያም፣ራስ ደረጀ፣ደጃ.ወ/ገብርኤል፣እቴጌ ጣይቱ፣የቤተመንግሥት ጥበቃ ክፍል፣የሠንጋ ማረጃ ክፍል/ቄራ/፣ሊጋባ ጣሰው፣አፈንጉስ ነሲቡ፣ጽሃፌትዕዛዝ ገ/ሥላሤ፣ራስ ናደው፣እጨጌ ገ/ሥላሤ፣በጅሮንድ ፍቅረሥላሤ፣ራስ አባተ(በኋላም እቴጌ ሆቴል)፣ደጃ.ገርማሜ፣ ፊታውራሪ አባኮራን፣ነጋድራስ አግደው፣የሠራተኞች ክፍል(ማድ ቤቶች)፣ደጃ.ውቤ፣ደጃ.ብሩ ሀ/ማርያም፣ ፊታውራሪ ገበዬሁ፣ጎላ ሠፈር፣ንጉስ ወ/ጊዮርጊስ፣አዛዥ ግዛው፣ራስ ቢትወደድ ተሰማ፣ደጃ.በሻህ አቦዬ፣ሊቀመኳስ አድነው፣ጠመንጃ ያዥ ሠፈር፣ራስ ልዑል ሰገድ

የአዲስ አበባ ከተማ ቦታ በነዚህ ከዚህ በላይ በተገለጹት ባለሥልጣኖች ይዞታ ሥር ውሎ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አሁንም አንዳንዱ ከባቢ በስማቸው ለመጠራት ችሏል።

የአዲስ አበባ ከተማ እያደገ፣የውጭ አገር ተወላጆችም እየመጡ መኖር ጀመሩ።የጆርጅያ ተወላጅ የነበሩት ሃኪም፣ መድሃኒት ቀማሚ/ፋርማሲስት/ዶር.መረብ እንደገለጹት፣–

በ1891 ዓ.ም.ምኒሊክ የንጉሡ ከተማ ወደ ሌላ ቦታ ዳግም እንደማይንቀሳቀስ ቃል በመግባት ቁጥራቸው ከ15 ለማያንሱ የውጭ አገር ተወካዮች/ዜጎች/የመኖሪያና የመሥሪያቤት መገንቢያ ቦታ እንዲሰጣቸው በመወሰናቸው ግንባታው በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጠናቀቀ።

ከጊዜ በኋላ ግን በከተማዋ ውስጥ ችግር እየተከሰተ መጣ፣የብዙ ነገሮች እጥረት ተፈጠረ።በተለይም ለማገዶ የሚሆን እንጨት ጠፋ።በከባቢው የነበረው ጫካ አለአግባብ በግፍ በመጨፍጨፉ፣ለተቆረጠውም መተኪያ ስላልተተከለ፣ጭራሮና ሣር ሳይቀር እየተመነጠረ ለማገዶ ስለዋለ ችግሩ ጣራ ነካ።በኢትዮጵያኑ ዘንድ ለተቆረጠው ዛፍ ምትክ የመትከሉ ልማዱም፣እውቀቱም፣ፍላጎቱም አልነበረም።በችግሩ የተነሳ አዲስ አበባን ለቆ ወደ ሌላ ቦታ ለመስፈር ሃሳብ ቀርቦ ነበር።ሆኖም ግን በውጭ አገሩ ተወላጆች ምክርና ተቃውሞ ለመንቀሳቀስም የሚያመጣውን ድካምና የንብረት ውድመት በማየት ለማገዶ የሚሆን እንጨት ከሩቅ እያመጡ ለመጠቀም ተወስኖ የከተማው ምስረታ እንዲቀጥል ሆነ።በጫካውና በዛፉ ምክንያት መናገሻ፣ሜጫና፣አዲስ ዓለም ለከተማነት ታጭተው ነበር።በንጉሱ የመጨረሻ ውሳኔ አዲስ አበባ የመንግሥቱ መቀመጫ ዋና ከተማ ሆነች።የመጀመሪያዎቹ ያውሮፓውያን የድንጋይ ቤቶች መሠራት ተጀመሩ።የችግሩ መከሰት ኢትዮጵያኑን በተለይም ምኒሊክን የጫካን ልማት ጥቅም እንዲረዱና እንዲስፋፋ፣ዛፍ አለአግባብ እንዳይቆረጥ የሚያግድ አዋጅ እንዲያወጡ ገፋፋቸው።ለአገሩ እንግዳ የሆነውም ባሕር ዛፍ(ከባህር ማዶ ስለመጣ)በሰፊው እንዲተከል መመሪያ ወጣ።በ1910 ዓ.ም.የአዲስ አበባ ነዋሪ ቁጥር ከ60-100 ሽህ እንደሚሆን ይገመት ነበር።

የንጉሳዊ ቤተሰቦችና የቅርብ መሳፍንቶች የሚበልጠውን ሠፋፊ የከተማ ቦታ ሲይዙ ከከተማው 58% የሚሆነው ቦታ በ1768 በሚሆኑ ባለቤቶች ማለትም ከ10.000-71.000 ካሬ ሜትር በነፍስ ወከፍ ተይዞ እንደነበር በኋላ የተመረመረው ማስረጃ ያሳያል። ከዚያም ሌላ 24.590 የሚሆኑ ዝቅተኛ ባለይዞታዎች 7.4% ሚሆነውን ቦታ ሲይዙ፣12.7% ለመንግሥትና ለውጭ አገር ኤምባሲዎች,12% ለቤተክህነት፣ቀሪው 9.9% በስውር ለቤተመንግሥቱ ቤተሰቦች ተከፋፍሎ ተይዞ ነበር።

የከተማ ቦታ ምሪት በ19ኛው መቶ መጀመሪያ ዓመት ላይ የባለቤትነትን የሚያረጋግጥ አዲስ መልክ ያዘ።ይህም በመሬቱ ባለቤቶች ላይ የነበረውን ስጋት ሊፍቀው ቻለ።ምንም እንኳን ንጉሥ ምኒሊክ የቦታው፣የመሬቱ ባለቤትና ሰጭ ነሹ እራሳቸው ሆነው ሳለ በቋሚነት ለሌሎቹ መብት አሳልፎ መስጠቱ ቢያሰጋቸውም በውጭ አገር አማካሪዎች ግፊት ሙሉ በሙሉ ባያምኑበትም የሚከተለውን 32 አንቀጽ የያዘ ሕግ በማህተማቸው ተረጋግጦ በ1907 ዓ.ም.በአዋጅ ወጣ።

አንቀጽ 1- እኔ ምኒሊክ ሁለተኛ የኢትዮጵያ ንጉሥ ለአገሬና ለውጭ አገር ተወላጆች ሕጉን እስካልጣሱ ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ መሬት የመግዛት መብት የሚያስችላቸውን ልዩ ሕግ ፈቅጀ አሳልፌአለሁ።

አንቀጽ 2- መንግሥት ለመሬቱ የሚከፈለውን የዋጋ ተመን ያወጣል።

አንቀጽ 3- ግለሰብ የመሬት ባለቤቶች/ባለይዞታዎች/በሕጉ መሰረት የያዙትን መሬት ለመሸጥ ይችላሉ።

አንቀጽ 4- የመሬቱ ልክ በካሬ ሜትር ይሆናል።አንድ ካሬ ሜትር ማለትም አንድ ሜትር በአንድ ሜትር ነው።

አንቀጽ 5- መሬቱን የሚሸጥና የሚገዛ የመሬቱ ስፋት በምስለኔ(በባለሥልጣን) የተረጋገጠና መሃንዲስ በካርታ ያስቀመጠው መሆን ይኖርበታል።

አንቀጽ 6- የካርታው ግልባጭ ለመንግሥት ቢሮ ቀርቦ በአዲስ አበባው የካርታ ዝርዝር ካድስትራል ውስጥ መካተት ይኖርበታል።

አንቀጽ 7- የድንበሩ፣የዋጋው መጠን፣የመሬቱ ስፋት በሁለት መሃንዲሶች የሚወሰን ሲሆን ከሁለቱ አንዱ ወይም ሁለቱም መሃንዲሶች የመንግስት ተቀጣሪዎች መሆን ይኖርባቸዋል።እነሱም ለመቃኘትና ለመመዝገብ አላፊነት ሲኖርባቸው ለሥራቸው አበላቸውን የሚከፍለው መንግሥት ነው።

አንቀጽ 8- የመንግሥት መሬት በሚሸጥበት ወቅት የመሃንዲሱን ዋጋ ገዥው ይከፍላል።የተለዩ ሁኔታ ሲገጥም ወጭውን ማን መክፈል እንደሚኖርበት ገዥውና ሻጩ ተስማምተው ይወስናሉ።

አንቀጽ 9- የመንግሥት ተወካይ የመሬቱን ዋጋ የመተመን ሥልጣን አለው።መንግሥትም ለገዢ ቀብድ የመክፈል መብት ይሰጠዋል። ሆኖም ግን በሙሉ ተከፍሎ የሚያልቅበት የጊዜ ገደብ በግልጽ መቀመጥ ይኖርበታል። በተወሰነው ቀን ተከፍሎ ካላለቀ መንግሥት መሬቱን መልሶ የመውሰድ መብት አለው።ለገዥውም የከፈለው ገንዘብ ያለ ወለድ ተመላሽ ይሆናል።

አንቀጽ 10- መንግሥት ለመሬት ገዡ የባለቤትነት የምስክር ወረቀት በመስጠት ለመስራት የሚፈልጉትን ነገር በሕጉ መሰረት እንዲሰሩ ፈቃድና እውቅና ይሰጣል።ነገር ግን ይህን የምስክር ወረቀት የሚያገኙት የገዙበትን ገንዘብ ሙሉ ለሙሉ መክፈላቸውን በሕጉ መሰረት የተደነገገውን ማክበራቸው ሲረጋገጥ ነው።

አንቀጽ 11- የምስክር ወረቀቱ ኮፒ በመዝገብ ቤት ውስጥ መኖር ሲገባው ቁጥሩ፣የሻጩ ስም፣የገዡ ስም፣ የመሬቱ ስፋት፣በቦታው ላይ ያለ ቋሚ ንብረት፣ድንበሩ፣የጎረቤቶቹ ስም፣የከባቢው ስም፣የመሬቱ ዋጋ፣እንዲሁም የተሸጠበት ዓመት ወርና ቀን ተተንትኖ መቀመጥ ይኖርበታል።

አንቀጽ 12- የሚሰጠው የምስክር ወረቀት የመንግሥት ማህተም የሰፈረበት ሲሆን ለማህተሙ 10 ብር በተጨማሪም ቀረጥ 1መቶኛ(1%) ብር ከጠቅላላው የመሬቱ ዋጋ ተተምኖ ለመንግሥት ይከፈላል።

አንቀጽ 13- አንድ ግለሰብ መሬት ሲሸጥና ሲገዛ የመንግሥት ተወካይና ሁለት እማኞች መገኘትና በምስክር ወረቀቱ ላይ መፈረም ይኖርባቸዋል።

አንቀጽ 14- ግለሰብ መሬት በሚሸጥበትና በሚገዛበት ወቅት ሽያጩ(ውሉ)በመንግሥት ማህተም ተረጋግጦ ከመንግሥት መዝገብ ውስጥ መመዝገብ ይኖርበታል።በአንቀጽ 12 መሰረትም የተደነገገው የ 10 ብር ክፍያና የጠቅላላው የመሬቱ ዋጋ የመቶ አንደኛ(1%)ክፍያ ገቢ ይሆናል።

አንቀጽ 15- ገዥና ሻጩ የተስማሙበትን እውነተኛ የገንዘብ ልክ ሸፍነው የተሳሳተ ዋጋ ለመንግሥት ካቀረቡና ከተደረሰበት ገዢው አራት እጥፍ ለመንግሥት የሚገባውን ገቢ ይከፍላል።ሻጭና ምስክሮቹ የገዢው ተያዦች ይሆናሉ።ነገር ግን ወንጀሉ ሳይታወቅና ሳይጋለጥ ሁለት ዓመት ከሞላው ማንም በጥፋቱ አይጠየቅም።

አንቀጽ 16- የውጭ አገር ተወላጆችና ኩባንያዎች በሕጉ መሰረት መሬት የመግዛት መብት ሲኖራቸው መጠኑ ግን ከአስር ሄክታር አይበልጥም።ሆኖም ግን መንግሥት ለመጨመር መብት ይኖረዋል።ይህን ሕግ የሚጥስ ከፍተኛ ቅጣት ይቀጣል።መሬቱ ይወረሳል።የገዛበት ዋጋ ብቻ ተመላሽ ይሆናል።

አንቀጽ 17- የመሬቱ ባለቤት መሬቱን ከገዛበት ጊዜ በ25 ዓመት ውስጥ መልሶ በትርፍ ሲሸጥ ለመንግሥት ከትርፍ አንድ ሶስተኛውን(1/3)የመስጠት ግዴታ አለበት።ይህን ሕግ ጥሶ የተገኘ በ15 አንቀጽ የተገለጠው ሕጋዊ እርምጃ ይፈጸምበታል።

አንቀጽ 18- ከመንግሥት የተገዛ መሬት ዋጋው ሙሉ ለሙሉ ተከፍሎ ሳያልቅ ቢሸጥ ሻጭና ገዢ ቀሪውን ማን እንደሚከፍል ለመንግሥት ማሳወቅ/መግለጽ/ ይኖርባቸዋል።ይህም የውል ስምምነት በመንግሥት መዝገብ ውስጥ ይሰፍራል።

አንቀጽ 19- ለመንግሥት የሚከፈል የመሬት ማለትም የሽያጭና የግብር ዕዳ ከሁሉም ቅድሚያ ይኖረዋል።

አንቀጽ 20- መሬቱን የገዛው ግለሰብ የምስክር ወረቀቱን/ሰርቲፊኬቱን/ለመረከብ የሚያስችለው የሚጠበቅበትን ክፍያ ሙሉ ለሙሉ ከከፈለ በመሬቱ ላይ የፈለገውን የማድረግ መብት አለው።ሙሉ ለሙሉ ወይም ቀንሶ ለመሸጥ፣አሳልፎ ለመስጠት፣ወይም በማስያዝ ገንዘብ ለመበደር ይችላል።የሚሸጠው ቦታ በከተማ ውስጥ ከሆነ ግን የሚሸጠው ቦታ ከአራት መቶ(400) ካሬ ሜትር ማነስ የለበትም።

አንቀጽ 21- የመሬቱ መጠን እንዳለ ተከብሮ ይቆያል።ከሕጉ ውጭ መከፈልና መሰንጠቅ አይቻልም።

አንቀጽ 22- ገዢው እዳውን ከመክፈሉ በፊት ቢሞት ወራሹ ይከፍላል።ወይም ከመንግሥት ጋር በመነጋገር ዘዴ ይፈጥራል።ይህን ለማሟላት ካልቻለ በአንቀጽ ዘጠኝ በተጠቀሰው መሰረት መንግሥት ቦታውን ይወስዳል። በቦታው ላይ ቤት ተሰርቶበት ከሆነ ቤቱና መሬቱ ተሸጦ ከእዳው የተረፈው ገንዘብ ለባለቤቱ ገቢ ይሆናል።

አንቀጽ 23- የመሬቱ ወራሽ መሬቱን ለመካፈል ከፈለገ ይችላል።ሆኖም ግን ድርሻውን ከአራት መቶ(400)ካሬ በታች ለመቀነስ ከፈለገ የመንግሥት ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል።

አንቀጽ 24- ወራሽ ለመንግሥት የወረሰውን የመሬቱን ግምት ሁለት በመቶ(2%)መክፈል ይኖርበታል።

አንቀጽ 25- መንግሥት ለከተማው ልማትና እድገት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው መሬቱን በመውረስ ለባለቤቱ የመንግሥት ባለሙያዎች በወሰኑት መሰረት ካሳው ይሰጠዋል።

አንቀጽ 26- መንግሥት ለሥራ የሚፈልገው መሬት ካነሰ ወይም ስፋቱ ከሁለት ሜትር በታች ከሆነ መንግሥት ለባለቤቱ በቀድሞው የመሬት ዋጋ ተመን መሰረት ካሳ ይከፍላል።ሆኖም ግን ይዞታው ከአስር ዓመት በላይ ከሆነ የመንግሥት ባለሙያ በገመተው መጠን መሰረት ካሳ ይሰጣል።

አንቀጽ 27- በመሬቱ ላይ ህንፃ ከቆመበት መንግሥት የመሬቱን ግምት ይሰጣል።ወይም በስምምነት ሌላ ቦታ በምትክ እንዲያገኝ ይሆናል።

አንቀጽ 28- የንብረቱ ባለቤት የሆነ የውጭ አገር ዜጋ ቢሞት ወራሽና ታዛቢ ወይም ጉዳይ ፈጻሚ ከሌለው መንግሥት ቦታውን ወስዶ ያከራያል።ሆኖም ግን በማንኛውም ጊዜ ወራሽ ነኝ ባይ በሚቀርብበት ጊዜ መንግሥት

1.የመንግሥት ዕዳ ቢኖርበት

2.መንግሥት ለቦታው ማሻሻያ ያወጣው ገንዘብ ካለ

በመሬቱ ዋጋ ግምት ሁለት ከመቶ(2%)የሚከፈለው ግብር ተደምሮ ለመንግሥት ገቢ ይሆናል።

አንቀጽ 29- እስከ ሰላሳ ዓመት ድረስ ወራሽ ነኝ ባይ ካልቀረበ መንግሥት መሬቱን ይወስዳል።ያገባኛል ጥያቄም ሊነሳ አይችልም።

አንቀጽ 30- ሟች ወራሽ ከሌለው መሬቱ የመንግሥት ንብረት ይሆናል።

አንቀጽ 31- በመሬት ዙሪያ ለሚነሳ ጭቅጭቅና ውዝግብ ዳኛ በሕጉ መሰረት ፍርድ በመስጠት ጠቡን ሊያሶግድ ይችላል።ነገር ግን ያንን ለማድረግ የሚያግዝ ሕጋዊ አንቀጽም ሆነ ሕጋዊ መንገድ ከሌለ ዳኛ በመሰለው (ናፖሊዮኒክ)ይፈርዳል።

አንቀጽ 32- ይህ ሕግ በጽሁፍ በከተማው መጋቢና በአመቺ ቦታዎች ላይ ይለጠፋል።

ተጻፈ ጥቅምት 20 ቀን 1900 ዓ.ም.አዲስ አበባ

በዚህ አዋጅ ሕግ መሰረት በዓመቱ በእቅዱ ቀስቃሽ በሆኑት የውጭ አገር ተወላጆች በጃኮብ ማርና በፈረንሳዊው ሊዮን ሽፍኬ መሪነት በመሃንዲሱ ያውም እርዳታ የመጀመሪያው የአዲስ አበባ ቅየሳና ምዝገባ/ ካዴስትራል ሰርቬ/በ1909 ዓ.ም.ተጀመረ።ቀጥለውም ንጉሡ በአዲሱ ካደስትራል መሰረት የባለቤትነት መብት እንዲረጋገጥ አዘዙ።በትእዛዙም መሰረት በቅድሚያ

1ኛ.መሬቱ እርስት ወይም የግል ይዞታ መሆኑ እንዲረጋገጥ

2ኛ.ከቀድሞ ባለቤቱ ጋር የተደረገውን ውል የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዲቀርብ

3ኛ.በንጉሡ ወይም በቤተክህነቱ የተሰጠ ለመሆኑ የስጦታውን ማስረጃ ማቅረብ

4ኛ.ከባለ እርስቱ በውርስ ወይም በስጦታ የተወሰደ መሆኑን ማረጋገጥ

ይህ ከተሟላ በኍላ የመሬቱን ባለቤትነት የሚያረጋግጠው በአማርኛና በፈረንሳይኛ የተጻፈው የርስት ወረቀት የአጎራባቹ ዝርዝር በስዕል የተነደፈበት የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

ይህን የምስክር ወረቀት ለማግኘት የበቃ የመሬት ባለቤት የቅየሳውን ዋጋ፣እንዲሁም በመሃንዲሱ በተገመተው ጠቅላላ የመሬት ዋጋ በሽህ ብር አምስት ብር እንዲከፍል መመሪያው ወጥቶ በሥራ ላይ ዋለ።

ይህ ዋስትና ከተረጋገጠ በኍላ የውጭ አገር ዜጎች ቤታቸውን በድንጋይ መሥራት ጀመሩ።አንድም የእንግሊዝ ኩባንያ ለውጭ ሰዎች መኖሪያ ሠፈር ለመሥራት/ለመገንባት/ፈቃድ በጠየቀ ጊዜ ዳግማዊ ምኒሊክ ቤቱ ከሚያርፍበት ቦታ ላይ ዙሪያው በስፋት የዛፍ ተክል እንዲያጠቃልል ትዕዛዝ ሰጡ።ከሕጋዊው ምዝገባ ጋር ተያይዞ የአቢሲኒያ ባንክ በ1905 ተቋቁሞ ግዴታውን ለሚያሟሉ ጠያቂዎቹ ለቤት መሥሪያ የሚሆን ብድር?ሞርጌጅ/ለመስጠት በቃ።

የውጭ አገር ሰዎች ሁኔታ

እንደተወላጁ በልማድ የውጭ አገር ዜጎች ቦታ የመያዝ መብት ነበራቸው።ሕንዶች፣ አውሮፓውያንና አርመናውያን በአገሪቱ ውስጥ ልዩ ልዩ ቦታ ይኖሩና መሬትም ይይዙ ነበር።ሆኖም ግን ከስጋት የተላቀቁ አልነበሩም። በ1901-1902 የነበረ አንድ ሚሲዮናዊ ሲናገር"በአውሮፓ እንደምናውቀው የመሬት /የንብረት/ትርጉም በኢትዮጵያ ውስጥ የለም።በአዲስ አበባ ውስጥ ቦታ ይዘው የተቀመጡትም ቢሆኑ በንጉሱ የተሰጣቸው መሬት በጊዜያዊነት የሚጠቀሙበት እንጂ በቋሚነት አይደለም"ሲል ተችቷል።

ለውጭ አገር ዜጎች የመሬት መግዛቱ መብት በልጅ እያሱ ጊዜ በ1910 ዓ.ም. ተሰረዘ።ኪራይም ከ30 ዓመት በላይ እንዳይሆን ታገደ።

ዶር.ሜራብ በ1908 ዓ.ም.ላይ እንደገለጸው፤-በከተማ ዋና ቦታ፣በገበያው ከባቢ በካሬ ሜትር ስሙኒ የሚያወጣው መሬት አንድ ብር ደረሰ፣ከከተማው ውጭ/ጠርዝ /ላይ በሚገኘው ከባቢ ግን ተመሳሳይ መሬት የብር አንድ አስራ ስድስተኛ (1/16 ብር) ከሰባት ሳንቲም በታች ማውጣቱን ሲገልጽ ፣አንድ ብር ያወጣ የነበረው መሬት ከ15 ዓመት በኋላ በ1923 ዓ.ም.አራት ብር መድረሱን ገልጿል።ቀጥሎም የአርመኑ ነጋዴ ጋራቤድ በ1929 ዓ.ም.የገበያው ከባቢ ከ5-8 ብር ድረስ ማውጣቱን፣ከከተማው ጠርዝ ደግሞ ከ50 ሳንቲም -አንድ ብር ማውጣቱን በመግለጽ በሃያ ዓመታት ውስጥ የዋጋው እድገት ከ8-32 እጥፍ መጨመሩን መስከሯል።ዶር.መረብም አስተያየቱን በመቀጠል አራትና አምስት ክፍል ያለው የአውሮፓውያን ቤት ከነበረንዳው የሚያሰራ ቦታ ከነአትክልት ጓሮው አንድ ሽህ ብር ሲያወጣ የቤቱም ኪራይ በወር ከ30-60 ብር ይደርስ እንደነበረ ገልጿል።

ዳግማዊ ምኒሊክ በአገር ውስጥ በልዩ ልዩ መስክ ከሚያከናውኑት የአላፊነት ተግባር በተጨማሪ በዓለም አቀፍ ዙሪያም በዲፕሎማሲ ደረጃ ያገሪቱን ጥቅም አሳልፎ ላለመስጠትና ያገሪቱን ነጻነት በማስጠበቅ በዘዴና በብልሀት ገፍቶ የመጣውንም በሃይል በመመከትና በመቋቋም የሚያኮራ ሥራ ሠርተዋል።

የሶስቱ አውሮፓ ታላቅ አገሮች እንግሊዝ፣ፈረንሳይና ጣልያን በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ አገሪቱን ለመያዝና ሃብቷን ለመዝረፍ ባቀዱበት ጊዜ ያገሪቱን ነጻነት ላለማስደፈር የሚገባውን አድርገዋል።

አንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በዲሴምበር 13 ቀን 1906 ዓ ም፣፣እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ታህሳስ 13 ቀን 1899 ዓ.ም.የነዚህ ሶስቱ ሃያላን መንግስታት ተወካዮች ለንደን ከተማ ላይ ተገናኝተው ኢትዮጵያን ለመያዝ ያደርጉ የነበረውን የርስ በርስ የጥቅም ግጭት ለጊዜው አሶግደው አገሪቱን ተከፋፍለው የሚይዙበትን ስምምነት አርቅቀው ተፈራረሙ።በስምምነቱ መሰረት፣-

1ኛ.የእንግሊዝ መንግስት በአባይ ውሃና ከአባይም ወጥቶ ወደ ግብጽና ወደ ሱዳን በሚወርደው ውሃና በዚያ ይዞታ ባለው አገር ላይ በጥቅም በኩል ልዩ ስልጣን እንዲኖረው፣

2ኛ.የፈረንሳይ መንግስት ከጅቡቲ ባለው በቅኝ አገሩ ይዞታ ከዚህ ቀደም በጀመረው የሃዲድ መንገድ መሰረት ለሃዲዱ መፈጸሚያና ለመመላለሻ የሚሆነውን መንገድ እንዲያገኝ።

3ኛ የጣሊያን መንግስት ከኢትዮጵያ ሰሜን በኤርትራና በደቡብም በሱማሊያ በኩል ያለውን ይዞታ ተከትሎ ብዙ ስፍራ እንዲያገኝ።

እነዚህ የሶስቱ መንግስታት ወኪሎች የስምምነት ግልባጭ ለአጼ ምኒሊክ እንዲደርስና ባሳቡ እንዲተባበሩበት ተጠየቁ።ነገር ግን ንጉሱ ምንም እንኳን በውሉ መጀመሪያ አንቀጽ ላይ የኢትዮጵያን ነጻነት፣የንጉሰ ነገስቱን ስልጣንና መብት አንነካም የሚል የማታለያ ቃል ቢሰፍርበትም ንጉሱ የኢትዮጵያን ጉዳይ የኢትዮጵያ መልክተኛ በሌለበት ብቻችሁን በተስማማችሁበት ግን እኔን ሊያስገድደኝ የሚችል የለም ብለው በዚያው ወርና ዓመት ለሶስቱ መንግስታት መልክተኞች በደብዳቤ አስታወቁ።

አጼ ሚኒልክ ለአገሪቱ ጥለውት የሄዱት ቁም ነገር በአጼ ቴዎድሮስና በአጼ ዩሃንስ ተጀምሮ የነበረውን ብሄራዊ አንድነትና አገር ግንባታ ቅርጽና መልክ እንዲይዝ ከማድረጋቸው በላይ አልፎ ተርፎ የአውሮፓውያን የከበርቴ ስርዓት እርስ በርሱ እየተፎካከር አገራትን በተለይም የአፍሪካ አገሮችን ለመቀራመት ወረራ ሲያካሂድ በአፍሪካ መሬት የመጀመሪያ የሆነውን የጥቁር ሕዝብ ድል በነጮቹ ወራሪዎች የደረጀ የጦር ሃይል ላይ በአድዋ ጦር ሜዳ ለቀረው የቅኝ ግዛት አገሮች ሕዝብ የነጻነትና የድል ምሳሌ የሆነውን ተጋድሎ ያደረጉና በድል ያጠናቀቁ አዋጊና ተዋጊ መሪ ነበሩ።አፄ መኒሊክ ለውጭ ሃይል ብቻ ሳይሆን በአገር ውስጥ ለሚነሳባቸውም ተቀናቃኝ

የሚያቀርቡት መፍትሔም በሳልና የረቀቀ ነበር።ከከባቢ ባለሥልጣንና ንጉሶች ጋር ለሚነሳ አለመግባባት በጠብና በጦርነት ከማንበርከክ ይልቅ በወዳጅነት፣በቤተሰብ ግንኙነት ማለትም በጋብቻና በአበልጅነት እንዲከስም ያደርጉ ነበር፡፤ከወሎው ንጉስ ከንጉስ ሚካኤል ጋር ለነበረው ፉክክር ሴት ልጃቸውን በመዳር ልጅ እያሱ ተወልደው ጠቡ በቤተሰብ ትስስር እንዲፋቅ አደረጉ።በየጁ በኩል የነበረውን የኦሮሞ ተወላጆች ሃይልና ተቃውሞ ለማምከን ጣይቱ ብጡልን በማግባት የአማራውንና የኦሮሞውን የገዢ መደብ በቤተሰብ ሰንሰለት አስተሳሰሩት። በዓለም አቀፍ ደረጃ የአውሮፓውያንን የቅኝ አገዛዝ ሰንሰለት ለመበጠስ አጼ ምንሊክና የኢትዮጵያ ሕዝብ ላደረገው አስተዋጽኦ የመከራው ሰለባ የሆኑት አገር ሕዝቦች አድናቆታቸውን በልዩ ልዩ መንገድ ገልጸዋል።ከነዚህም መካከል የብራዚል የጥቁሮች የነጻነት እንቅስቃሴ አንዱ ነበር።ይህ እንቅስቃሴ ለሚያደርገው ቅስቀሳ የሚጠቀምበትን ጋዜጣ ምኒሊክ ሲል ሰይሞት ነበር።በአገር ውስጥም የሚኒሊክን የጦር አመራር ችሎታና ያመጣውን ውጤት በሚከተለው ስንኝ ኢትዮጵያኖች ቋጭተውታል።

ምኒሊክ ተነስቶ ባያነሳ ጋሻ፣

ግብሩ እንቁላል ነበር ይህንጊዜ አበሻ።

በማለት የኢትዮጵያ ሕዝብ ቢሸነፍ ኖሮ ለጣሊያን ከሚገብረው ግብር አንዱን በመጥቀስ ለማሳየት ተሞክሯል። የኻላ ኻላ ግን አልቀረለትም።ከአርባ ዓመት በኟላ ጣልያን ተደራጅቶ የበቀል እርምጃ ወስዶ አገሪቱን ሙሉ ለሙሉም ባይሆን ለአምስት ዓመት በተቆጣጠረበት ጊዜ በተግባር ታይቷል።

ከምኒሊክ ቀጥለው ስላጣኑን የተረከቡት የሴት ልጃቸው ልጅ የሆኑት ልጅ እያሱ ናቸው። በዙፋኑ ላይ የተቀመጡት ለሶስት ዓመት ብቻ ነበር።በቤተመንግስት ውስጣዊ ፉክክር በተለይም በደጃዝማች ተፈሪ መኮንን (የኟላው አጼ ሃይለ ስላሴ) ደጋፊዎች በሆኑት የቤተክህነት አለቆችና መኳንንት የተቀነባበረ ተንኮል የኘህ ንጉስ የግዛት ዘመን አጠረ፤በግዞት በተቀመጡበት ቦታ በጭካኔ ህይወታቸው ጠፋ።ከሳቸው ቀጥለው ሕዝቡን ለማረጋጋትና አመቺ ሁኔታ እስኪፈጠር ድረስ ለስሙ የአጼ ምኒሊክ ሴት ልጅ ንግስት ዘውዲቱ ዘውድ እንዲጭኑ ተደርጎ ብዙም ሳይቆዩ እሳቸውም በተንኮል ተወግደው በዛው በተለመደው አሻጥር መንገድ ስልጣኑን የያዙት፣ ብዙዎቻችን ተወልደን ያደግንበትና የምናውቀውን የመጨረሻ ዘውዳዊ ስርዓት የመሩትና የወከሉት አጼ ሃይለ ስላሴ ናቸው።

ተፈሪ መኮንን ዘውድ ከመድፋታቸው በፊትም ሆነ ደፍተው አጼ ሃይለስላሴ ንጉሰ ነገስት ዘኢትዮጵያ ከተባሉ በኟላ ከእርሳቸው በፊት በንጉስ አጼ ምንሊክ፣ በልጅ ኢያሱና በንግሥት ዘውዲቱ የተጀመሩትን ስራዎች በመቀጠል ለማጠናቀቅ ሞክረዋል።የትምህርት ቤት፣የመንገድ ሥራው ሳይቋረጥ በ1915 ዓ.ም.እ.አ.አ.የወረቀት ብርና ፣ከነሃስ ከመዳብ፣ከብር የተሠሩ ፍራንኮች ታትመው በጣሊያን ወረራ ጊዜ በጣልያን ሊሬ እስከተተኩ ድረስ በጥቅም ላይ ውለዋል። በ1929 የአውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር ለመጀመሪያ ጊዜ አውሮፐላን ወደ አገር ውስጥ አስገቡ፣ በሚኒሊክ ጊዜ የተቋቋመው የአቢሲኒያ ባንክ ስሙ ተለውጦ የኢትዮጵያ ባንክ ተብሎ እንዲጠራ፣ በ1931 ዓ.ም.እ.አ.አ ሁለት መቶ ሰላሳ አምስት ሽህ ፓውንድ በመክፈል ይዞታውም ሙሉ ለሙሉ በኢትዮጵያ መንግስት ስር እንዲሆን አድርገዋል።በኢጣልያንና በእንግሊዞች ቁጥጥር ሥር በነበረችበት ጊዜ አገሪቱ ትጠቀምበት የነበረው የሊሬና የምስራቅ አፍሪካ ሽልንግ ተወግዶ በ1945ዓ ም.ጣልያን ከወጣ በኟላ እንደገና የአገሪቱ ሕጋዊ ገንዘብ የኢትዮጵያ ብር ታትሞ እስከ ደርግ ስልጣን የመጀመሪያ ዓመቶች በጥቅም ላይ ዋለ።

የተርጓሚው አስተያየት-«አጼ ሃይለ ስላሴ እንደቀሩት መሪዎች ለተቃዋሚና ለሕዝባዊ ጥያቄ ደንታና ትግስት አልነበራቸውም። በስልጣናቸው የመጣውን ወይም የአስተዳደር ለውጥና መሻሻል እንዲደረግ የሚጠይቀውን በምስጢርና በገሃድ እየጨፈለቁ ከአርባ ዓመት በላይ በስልጣን ላይ ቆይተዋል።በዚህ የስልጣን ዘመናቸው እንደቀሩት መሪዎች ፈተናና መከራ አሳልፈዋል።አገራቸው በውጭ ጠላት ሲወረርና ዘውዳዊ አገዛዛቸው ሲናጋ በማይጨው የጦር ሜዳ ላይ ባይዘልቁበትም ለውጊያ ተሰልፈዋል።የጠላት ሃይል የማይበገር ሲሆንባቸው፣እያሸነፈ ወደ ፊት ሲገሰግስና የወገን ጦር ሲሳነው የነበራቸው ምርጫ አንድ ብቻ ነበር። ይኸውም ወደ ውጭ አገር

ወጥቶ እራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ማትረፍ በተጨማሪም በደልና ወረራውን ለዓለም መንግስታት ማስረዳትና የዲፕሎማሲ ትግል ማድረግ። በኢትዮጵያ ንጉሶች ታሪክ ውስጥ ታይቶ ተሰምቶ የማይታወቀውን የስደት ኑሮ ቀምሰዋል።እርግጥ በመውጣታቸው ብዙ ትችትና ተቃውሞ መኖሩ ባይካድም በነበረው ሁኔታ አገር ውስጥ በጫካ ቢቆዩ በስደት ያደረጉት አስተዋጽኦ ያገኙት ድጋፍና እርዳታ ሊገኝ ይችል ነበር ወይ? ብሎ መጠየቁ ሳይሻል  አይቀርም።በተጨማሪም ለአርበኞች ምክር፣ስንቅና ትጥቅ እያሰባሰቡ በመላክ ትግሉ እንዲጠናከር ያልተቆጠበ ጥረት አድርገዋል።አርበኞችም በደፈጣ/የሽምቅ ውጊያ(ጎሬላ ዋርፌር)ጠላትን በማስጨነቃቸው ቻይናዎች በማድነቅ በወቅቱ ያካሂዱ ለነበረው ጸረጃፓን ውጊያ  የስልት ምሳሌ አድርገው ተጠቅመውበታል።

አገራቸው በወራሪ ሃይል ሲያዝ የተሰደዱ መሪ እሳቸው ብቻ አልነበሩም፤አንዳንድ የአውሮፓ አገር ንጉሳዊ ቤተሰቦችም የዚሁ ዕድል ቀማሾች ሆነዋል።የሆላንድ ንግሥትየነበሩት ዊለሚናም አገራቸው በጀርመን የናዚ ጦር ሲወረርና ሲያዝ ቤተሰቦቻቸውን ይዘው በእንግሊዝና በካናዳ በስደት ኖረዋል።ከድል በኋላ ተመልሰውም በዙፋናቸው ላይ ተቀምጠዋል። ግራም ነፈሰ ቀኝ ግን ንጉሥ ሃይለሥላሴ ከሳቸው በፊት እንደነበሩት መሪዎች ለአገሪቱ አንድነትና ነጻነት የድርሻቸውን አበርክተዋል።ብዙ መልካምና በጎ ነገር ሰርተዋል። አገሪቱን ለማሳደግና ለማሻሻል ከሌሎቹ የተለዩ ዕድልና አጋጣሚ ነበራቸው።ስልጣኔ ይነካል ወይም ይደፈራል የሚለውን የመሳፍንቶች ፍርሃት ምክርና ስጋት ወደ ጎን ትተው የተማረ ዜጋ አስፈላጊነት ተቀብለው ለትምህርት መስፋፋት ጥረት አድርገዋል። ከእኔም በፊት ሆነ የእኔም ትውልድ ፊደል የቆጠረውና ለከፍተኛ ትምህርት የበቃው እሳቸው ባስፋፉትና በከፈቱለት የትምህርት ዕድል ነው።ትምህርት እንደማስፋፋታቸው ለአገሪቱ እድገት የሚበጀውን በተማረው ክፍል የሚቀርብላቸውን ምክርና ፍላጎት ግን ሊቀበሉ አልቻሉም።በዕድሜ ጫና ግንዛቤአቸው እየከዳቸው ሄደ።በዙሪያቸው የነበሩትን የተማሩ ሰዎች ምክርና እውቀት ሳይጠቀሙበት ቀሩ፣ ከጊዜው ጋር መሄድ ተሳናቸው። በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ በተለይም በአፍሪካ ምድር ተከብረውና ተፈርተው እንዳልኖሩ በነገሱበት አገር፣በስማቸው ይምል በነበረው የወታደር መንጋ ከሥልጣናቸው ተወግደው ከተራ ሰው ባነሰ ደረጃ ተዋርደው ለመሞት በቁ።መሞታቸው ብቻ ሳይሆን የተቀበሩበት ቦታ ሳይታወቅ ለረጅም ጊዜ ቆዩ። ከደርግ መውደቅ በኋላ የተቀበሩበት ቦታ በአረመኔው መንግሥቱ ሃይለማርያም ቢሮ ውስጥ  በሽንት ቤት ጉድጓድ ውስጥ መሆኑ ታውቆ ፣አጽማቸው ወጥቶ እንደገና በቅድስት ሥላሤ ቤተክርስቲያን ውስጥ ከቤተሰቦቻቸው የመቃብር ቦታ ለማረፍ ቻለ።የሰሩት መልካም ነገር ሁሉ እንዳልነበረ ሆነ።

እኚህ ንጉስ ሌላው ቢቀር የመሬት ይዞታን ቢያሻሽሉና የመለስተኛ ዲሞክራሲ መብቶችን ቢያውቁና ቢያከብሩ ኖሮ ለተተካው የደርግ አረመኔ መንግስት እድልና በር አይኖርም ነበር።አገሪቱ ወደ ተሻለ አስተዳደር ታመራ ነበር።የአሁኑም መልኳ የተለዬ ይሆን ነበር የሚል አስተያየት በሰፊው ሲቀርብ ይሰማል፤ እኔም ይህንን ሃሳብ እጋራለሁ። ከደርግ መነሳት ከአስራ ሶስት ዓመት በፊት በነጀነራል መንግስቱ ነዋይ ተሞክሮ ያልተሳካው ወታደራዊ አመጽ ትልቅ ትምህርት ሊሰጣቸው በተገባ ነበር። መረሳት የሌለበት ነገር የቆሙበትና የስልጣናቸው መሰረት የሆነው የባላባታዊው ስርዓት እንደመሆኑ መጠን ያንን የሚቃረንና የሚጋፋ፣ የመሬት ባለቤቶችን ጥቅም የሚነካ ሕግና አስተዳደር ለማምጣት የመደብ ጥቅማቸውና አስተሳሰባቸው የማይፈቅድላቸው መሆኑን ነው። የሚቀርቡት ጥያቄዎችና የሕዝቡ ፍላጎት የሶሻሊስቱንና የዲሞክራሲ ስርዓትን የሚያንጸባርቅ ስለነበረ ከሳቸው ስርዓት ለውጥ መጠበቅ ዶሮን አልቤ ወተት እጠጣለሁ የማለት ያህል ነበር።

እያንዳንዱ ሥርዓት የራሱ የሆነ ጸባይና ይዘት አለው።የአጼ ሃ/ስላሴ ዘመነ መንግስት ከሌሎቹ ነገስታቶች የግዛት ዘመን የተለዬ ነው።ዓለም በብዙ መልኩ ተለዋውጧል። ከዚህ ለውጥ ጋር አብሮ መሄድ ግድ ስለሆነ ስርዓቱ ምንም እንኳን ስር ነቀል ባይሆንም በአቀራረብ ደረጃ ከበፊቱ የመቀየር መልክ አሳይቷል። ለዘመናት የሰፈነው ኋላ ቀርና ባህላዊ አስተሳሰብና የቤተ ክህነት መሪዎች ተቃውሞ  ለዘመናዊ አስተሳሰብና ትምህርት ትልቅ እንቅፋት ነበር። ባሕላዊው ትምህርት ከመንፈሳዊ አገልግሎት ውጭ ዘመኑ ለሚጠይቀው እድገት የሚሰጠው ወይም የሚያበረክተው አነስተኛ በመሆኑ የዘመናዊ ትምህርት ባገሪቱ እንዲስፋፋ ንጉስ ሃ/ስላሴ በዘዴና በማግባባት ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል።እራሳቸው ከአገራቸው ባህላዊ የቄስ ትምህርት በተጨማሪ ለውጭ አገር በተለይም ለፈረንሳይ ቋንቋና የአስተዳደር ዘይቤ እንግዳ ስላልነበሩ ለዘመናዊ ትምህርት ትኩረት ሰጥተውት ነበር። በአጼ ምኒልክ የተጀመረው የትምህርት ቤት ማቋቋም ስራ ቀጥሎ የመጀመሪያ የሆኑትን ዘመናዊ አዳሪ ትምህርት

ቤቶች ከፍተው፣ መምህራን ከውጭ አገር አስመጥተው፣ በመጀመሪያ የመሳፍንቱ፣የመኳንንቱና በተዋረድም የሹማምንቱ ልጆች በትምህርቱ ገበታ እንዲሳተፉበት አድርገዋል።በቀጣዩም ትምህርት ለተራው ሕዝብ እንዲዳረስ እድሉን ከፍተዋል።እድል መከፈት ብቻ ሳይሆን ተማሪዎቹን ለማበረታታትና የኤኮኖሚ አቅማቸው ደከም ላለው፣ ከየጠቅላይ ግዛቱ በአዲስ አበባ ለከፍተኛ የቴክኒክና ፣የንግድ ሙያ ትምህርት ለሚመደቡት በየወሩ ከአስራ አምስት እስከ ሃምሳ ብር አበልና የኪስ ገንዘብ በመስጠት እንዲሁም በሌሎቹ የኮሌጅ ተቋማት የነጻ ትምህርትና የመኖሪያ ቤት ከነቀለባቸው (ነጻ የምግብ አቅርቦት) በማሟላት፣በየጠቅላይ ግዛቱም ላሉት የመደበኛ ትምህርት ተከታታዮች ለኀበዙትና የአስራሁለተኛን ክፍል ፈተና ማትሪክን በጥሩ ውጤት ላለፉት የወርቅ ሰዓት፣ የወርቅ ብዕር፣ገንዘብና ሌላም ሽልማትና ማበረታቻ ይሰጡ ነበር።ከጊዜ በኋላም ወደ ውጭ አገር ለከፍተኛ ትምህርት እየተላኩ የሚማሩበትን ዕድል ከፍተዋል። ትልቁን ቤተመንግስታቸውንም የመጀመሪያው ኮሌጅ እንዲቋቋምበት ሰጥተዋል። ምንም እንኳን አገሪቱን ለማሻሻል ጥረት ቢደረግም ስርዓታቸው ወይም አስተዳደራቸው ከጊዜው ጋር መሄድ በማይችሉ መሳፍንትና ባላባቶች መዳፍ ውስጥ ስለቀረ እሳቸውም የዛው መደብ አባል በመሆናቸው ዘልቆ ሊሄድና የሚፈለገውን ያህል ለውጥና እድገት አላመጣም።ያም ስለሆነ የኋላ ኋላ ለውድቀታቸው ምክንያት ሆነ።

የሚወክሉት ስርዓት ከዚያ አልፎ የሚሄድበት አቅምና ችሎታ ስላልነበረው፣ለዘመኑም ጥያቄ መልስ መስጠት ስላዳገተው ተንገጫግጮ ለመቆም ተገደደ።የታሪክ ምዕራፉ ባልታሰበ መልክ ሊደመደም በቃ።በዙሪያቸው የነበሩት የተማሩ ሰዎችም በዛው የመሳፍንቱ ሰልፍ ውስጥ የገቡ ስለነበሩ የሚያስቡትን ሊያደርጉ አልቻሉም፤የላቀ የትምህርት ደረጃና በውጭ አገር ኑሮ የቀሰሙትን የዲሞክራሲ ተመክሮ ፣በአገራቸው ውስጥ ለመተርጎም ፍላጎት ቢኖራቸውም የንጉሱን ፈቃድ ለማግኘት የነበሩበት ሁኔታ አልረዳቸውም።

በወቅቱ ዘመናዊ ትምህርት ሃይማኖትንና ባሕልን የሚበክልና የሚያጠፋ፣የሰይጣን ስራና የነጮች ሃይማኖት መስፋፊያ መንገድ ነው ተብሎ በቀሳውስቱና በሃይማኖት መሪዎች ትልቅ ተቃውሞ ነበር።ያንን ሁሉ በመቋቋም ነው ዘመናዊ ትምህርት ወደ አገር ለመግባት የቻለው።በአጠቃላይ በአገሪቱ ውስጥ ትምህርት እንዲስፋፋ ያልተደረገ ጥረት አልነበረም።ለተማሪ ደብተር ፣እርሳስና ላጲስ እየሰጡ ከሚያበረታቱት ህጻን ተማሪ መካከል እኔ እራሴ አንዱ ነበርኩ። በእድሜ ለገፋውና የትምህርት ዕድሉ ላመለጠው ሳይቀር "ፊደል ሠራዊት"በሚል ዝግጅት ሌላው ቢቀር የማንበብና የመጻፍ ችሎታ እንዲኖር ያደረጉት ጥረት በቀላሉ የሚታይ አይደለም።በኋላም ደርግ እድገት በሕብረት በሚለው ፕሮግራሙ ሥር ያካሄደው የተምሮ ማስተማር ዘመቻ የዚሁ ንጉሱ ጀምረውት የነበረው ቅጥያ እንጂ አዲስ ግኝት አይደለም።

በዳግማዊ ምኒሊክ በህግ የተሻረው የባሪያ ንግድ በዘመናቸውም እንዳይካሄድ መመሪያ አውጥተው አንዱ ሻጭ ሌላው ተሻጭ አለመሆኑን፣እኩል ዜጋ መሆኑን አረጋግጠዋል።ለዘመናት የባሪያ ንግድ ይካሄድባቸው የነበሩትን እንደ ግንደበረት የመሳሰሉትን የአገር ውስጥ ገበያዎች አስቀርተዋል።በሰው ልጅ የሚነግዱትም በሕግ እንዲቀጡ አድርገዋል።በየመሳፍንቱና መካንንቱ ቤት ውስጥ የሚኖሩ አገልጋዮች በባርነት ሳይሆን በሠራተኛነት በደመወዝ እንዲተዳደሩ አድርገዋል።በሃይማኖትም ልዩነት ሳቢያ ሕዝብ እንዳይበደልና ግጭት እንዳይፈጠር ሃይማኖት የግል አገር የጋራ መሆኑን በሚያበስር ንግግራቸውና መመሪያቸው አረጋገጠዋል።

የባሪያ ንግድ በኢትዮጵያ ብቻ የተከናወነ ድርጊት ሳይሆን በሌሎችም አገሮች ጥንት በሮማውያን፣በግሪኮች፣ በፋርሶችና በግብጾች የሚከናወን ድርጊት ነበር።ከዚያም በኋላ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አሁን በሥልጣኔአቸውና በዲሞክራሲ ሥርዓታቸው በሚደነቁትም አገሮች አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ደቾች፣ፖርቱጋሎችና ስፓኒሾች ይህንኑ ሥርዓት ተገልግለውበታል።ከአፍሪካና ከኤስያ በሃይልና በግዢ የሰበሰቡትን የሰው ልጅ እንደከብት በሰንሰለት አሥረው ወረው በሚቆጣጠሩት አገርና መሬት ላይ ማስፈራቸው ቀለሙ ያልደረቀው የትናንትና ታሪካቸው ይመሰክራል። የዚህ ስርዓት ቅሪት የሆነውም በእኛ ዕድሜ የደረስንበት የደቡብ አፍሪካ ፣ የዚምባብዌ (የሮዴሽያ) የሞዛምቢክ የሌሎችም የቅኝ ግዛት አስተዳደር አንዱ ገጹ ነው።አሁንም ቢሆን ምንም

እንኳን የሰው ልጆች እኩልነት በሕግ ፊት ቢረጋገጥም ብዙ ነጮች መቀበል እያቃታቸው ያላቸው አስተሳሰብ ከዱሮው የተለዬ አይደለም።በዘረኝነት የሚፈጸመው በደል፣አድልኦና ግድያ ብዙ ነው።

በኢትዮጵያም እንዲሁ በጊዜው ስልጣን ላይ የተቀመጠ ሃይል የራሱንም ጎሳ ተወላጅ ሳይቀር በባርነት ማሠራቱንና መሸጡን፣ለእርቅና ለድርድርም እንደዕቃ አሳልፎ መስጠቱን መካድ ትክክል አይደለም።ከሌላ አካባቢ በመጣ ጎሳ የሚካሄድ ግፍና በደል ነው ብሎ የራስን ድክመት መሸፋፈን ሕዝብን ለቅርሾ መገፋፋት ነው። የኦሮሞው ባላባት ኦሮሞውን ሸጧል፣የወላይታው ባላባት ወላይታውን ሸጧል ለውጧል፣የአማራው ባላባት አማራውን ሸጧል፣የትግሬው ባላባት ትግሬውን ሸጧል ለውጧል።ሌላው ሌላውም እንዲሁ።በነበረው ስርዓት የነበሩት ሃይለኞች ጥቅማቸውን እስካገኙ ድረስ ይኸ ወገኔነው፣ ይኸ የጎሳዬ ተወላጅ ነው ብለው አይራሩለትም ነበር።ይዘርፉታል፣ ጉልበቱን በቤት ውስጥና በእርሻ መስክ እንክት አድርገው ይገለገሉበታል፣የበለጠ ጥቅምና ገቢም ለማግኘት እንደ ዕቃ በገበያ አውጥተው ይሸጡታል። የሁሉም የኑሮ ዘይቤ ነበር።በባሪያ ንግድ ትልቅ ሚና የተጫወቱት አንዱ የከፋው ባላባት አባጅፋር ነበሩ።መረን የለቀቀውን ተግባራቸውን እንዲያቆሙ አጼ ምኒሊክ በተደጋጋሚ ትዕዛዝም ማሳሰቢያም ሰጥተዋቸዋል።

በውጭ አገር ታዛቢዎች ግፊትና ምክር አፄ ምኒሊክ የባርያ ንግድን በሕግ ከለከሉ።ግን ንግዱ ውስጥ ለውስጥ ሲካሄድ ለረጅም ጊዜ ቆዬ።የባላባት ስርዓቱን ግን አልነኩትም።በዚህም የባላባት ስርዓት የተጠቀመው የአንድ ጎሳ ተወላጅ ባላባት ሳይሆን በአገሪቱ ውስጥ ያሉት የተለያዩ ጎሳዎች ባላባቶች ናቸው።የአማራው ባላባት ለአማራው ገባር ወይም ጭሰኛ የሚያደርሰውን ጭቆናና ዘረፋ ያህል የኦሮሞው ባላባት በኦሮሞው ገባር ወይም ጭሰኛ ላይ የተለየ አያያዝ አልነበረውም።የሌላውም ጎሳ ባላባት እንደዚሁ።የየጎሳው ባላባት ለጎሳው ተወላጅ አልራራለትም፤ሲበዘብዘው፣ሲተክለው፣ሲነቅለው ኖሯል።የጎሳውን ተወላጅ የሚያስታውሰው ግብር ሲሰበስብና በሌላ ባላባት ሲወረርና ለጦርነት ሲነሳብቻ ነው።

አፄምኒሊክም ሆኑ አጼ ሃይለሥላሴ የሚወክሉት ስርዓት ምንም እንኳን ሥረመሰረቱ ያው የባላባታዊ ቢሆንም፣ በየጊዜው ለሚነሳው የመሬት ጥያቄ ምንም እንኳን ስር ነቀል ባይሆንም በጥገና መልክ መልስ ለመስጠት ሙከራ አድርገዋል።በተለይም ሕዝቡን አስመርሮት የነበረውን ግብር በሚመለከተው ዙሪያ የሚከተለውን ማሻሻያ አዋጅ በ1940 ዓ.ም.አወጡ።

አንቀጽ 1- ማንኛውም የሚከራይ የከተማ መሬት ልኩ /መጠኑ/በካሬ ሜትር ይሆናል፣የገጠሩ መሬት ግን የሚመለከታቸው በሚስማሙበት ልኪት ይመጠናል።

አንቀጽ 2- የመሬቱ ግብር የመሬቱ ልማትና ሌላውም ታይቶ ሁለቱ አካላት በተስማሙበት መጠን ይሆናል።

አንቀጽ 3- አንድ የውጭ አገር ዜጋ ኮንተራቱ ባለቀ ጊዜ በመሬቱ ላይ ያሰፈረውን ቋሚ ንብረት /ቤትና ህንፃ/ለባለቤቱ ለመመለስ/በነፃ ለመስጠት/ከተስማማ የሚፈልገውን ያህል ህንፃ ሊገነባ ይችላል።ካልሆነ ግን ውሉና ገደቡ በቅጡ መቀመጥ ይኖርበታል።

አንቀጽ 4- ከሰላሳ ዓመት በላይ መከራየት አይቻልም።ሆኖም ግን መንግሥት ከፈቀደ ሊራዘም ይችላል።

አንቀጽ 5- በእርሻ ላይ የተሰማሩ የውጭ ዜጎች የተለመደውን /ተገቢውን/አንድ አሥረኛ (1/10)ምርትና በተጨማሪ የገቢ ግብር መክፈል ግዴታው ነው።አስቀድሞ ፈቃድ ካልተሰጠ በስተቀር ምርቱን ወደ ውጭ አገር ሊልክ አይችልም።በምርቱ ላይ በአገሪቱ ሕግ መሰረት ቀረጥ ይጣልበታል።

አንቀጽ 6- ታሪካዊ ቅርስና የተፈጥሮ ሃብት የሚገኝበት መሬት የመንግሥት ሃብት ሲሆን እንዳጋጣሚ በውጭ አገር ተወላጅ ይዞታ ስር ከዋለ ውጤቶቹን ያለፈቃድ በድብቅ ከአገር ሊያስወጣ አይችልም።መንግሥት ተከራዩ ያወጣውን ወጭ ከፍሎ መሬቱን ይወርሳል።

አንቀጽ 7- በውጭ አገር ዜጋ በያዘው ግቢ አቋርጦ የሚሄድ የመስኖ ውሃ ቢኖር ሊያግድና ሊከላከል አይችልም ።ሆኖም ግን በውሃው ሊደርስበት የሚችል ጉዳት ካለ ካሳ ሊጠይቅና ሊያገኝ ይችላል።

አንቀጽ 8- መንግሥት ለገበያ፣ለቤተክርስቲያን፣ለወታደራዊ ተቋም፣ለባቡር ሃዲድና መንገድ፣ለተመሳሳይ አገልግሎት ሊውሉ የሚፈለጉ መሬቶችን ካሳ በመስጠት መውረስ ይችላል።

አንቀጽ 9- የውጭ አገር ዜጋ በተከራየው መሬት ላይ የሚኖሩ ሰዎች ጋር ጭቅጭቅ ቢነሳ ጉዳዩ በአገሪቱ ሕግ መሰረት ይታያል።

አንቀጽ 10- ለማንኛውም የኪራይ ውል ማስፈጸሚያ ምዝገባ መክፈል ሲገባው የመሬቱ ባለቤት ከዓመት ገቢው አንድ መቶኛ (1%)ግብር ይከፍላል።

አንቀጽ 11- የውሉ የጊዜ ገደብ ሲያበቃ አከራይና ተከራይ በሚመርጣቸው፣በየእራስ ሁለት ተወካዮች በባለቤቱ ፈቃድ በመሬቱ ላይ የተሰሩትን ቤቶች የዋጋ ተመን ይመረምራሉ።አራቱ ለመስማማት ካልቻሉ አምስተኛ ሰው በመጨመር ለሚያሳልፈው ውሳኔ ተገዥ ይሆናሉ።ውሳኔውም የመጨረሻና የጠና ይሆናል። ካለባለመሬቱ ፈቃድና እውቀት በውጭ አገር ዜጋው የተገነቡ ቤቶች ባለመሬቱ በግዥ መልክ ለማስቀረት ካልተስማማ እንዲፈርሱ ይደረጋል።/ይፈርሳል/

ከላይ እንዳየነው በአጼ ሃይለሥላሴ መንግሥት የተቀመጠው ደንብ በተለይም በውጭ አገር ተወላጆች ስለሚያዝ መሬት የወጣው ሕግ ከሃያ አምስት ዓመት በኧላ በደርግ ከወጣውና አሁን ከ60 ዓመት በኧላ የህወሃት/ኢሕአዴግ ካወጣው የመሬት ስሪት ሕግ ጋር ሲነጣጠር ምን ያህል ለአገሪቱ ክብርና ቅድሚያ የሰጠ እንደነበር ለመረዳት እንችላለን።ኧላ ቀር ተብሎ የሚጠራው ዘውዳዊ አገዛዝ አሁን ካለው የበለጠ ለአገሪቱ የሚቆረቆር ነበረ።በተራ ቁጥር አንቀጽ 5፣6፣7 ላይ የሰፈረውን ብንመለከት ለዚያ በቂ ማስረጃ ነው።የአሁኑ መሪዎች የአገሪቱን ለም መሬት በርካሽና በነጻ ለውጭ አገር ተባባሪዎቻቸው ለዘጠና ዘጠኝ ዓመት አሳልፈው ሰጥተዋል፣የልጅ እያሱና የቀዳማዊ ሃይለስላሴ መንግስት ለውጭ ዜጎች የመሬት ሙብት ከሰላሳ ዓመት አይበልጥም ነበር።የመሬት ባለቤት ሕዝብ ሳይሆን መንግስት ሆኗል፤ሕዝብ የመንግስት ጭሰኛ ነው ማለት ነው።ሕዝብ በግዥና በውርስ ለብዙ ዓመታት የያዘው መሬት ካለምንም ልዋጭና ካሳ እየተነጠቀ ሜዳላይ እንዲወድቅ ሆኗል። ተለዋጭም ቢሰጠው ጠፍና ከነበረው የመሬት መጠን በአስር እጅ ያነሰ ነው።በስልጣን ላይ ያለው ቡድን ከአገሩ ደሃ ሕዝብ ይልቅ ዋስትና የሚሰጠውና የሚጠቅመው የውጭ አገር ባለሃብቶችን ነው። የወንዝና የመስኖ ውሃዎች እንዲበከሉ ወይም አቅጣጫቸውን እንዲቀይሩ፣የውጭ አገር ባለሃብቱ እንደሚፈልገው እንዲያደርጋቸው ተፈቅዶለታል፤የሚያመርተውንም ምርት ካለምንም ገደብና ቁጥጥር እንዲሁም ግብር ሳይከፈልበት ወደ ፈለገው አገር አውጥቶ የመሸጥና የመጠቀም ሙብቱ ተጠብቆለታል። ሕዝቡ ግን የበይ ተመልካች ሆኖ፣የሚመረተውን ሳይቀምስ በርሃብ እንዲያልቅ ተፈርዶበታል።

የዘውዳዊ ስርዓቱ ተቃዋሚ ብሆንም የተሰሩ መልካም ነገሮችን ግን ለመመስከር አቋሜ አያግደኝም።ሚዛናዊ የሆነ ሲሆን ጥሩ ነው።በጭፍን ጥላቻ የተሠራን በጎ ነገር መካድና መቃወም ከሚሰጠው ጥቅም ይልቅ የሚያመጣው ጉዳት ያመዝናል ብዬ አምናለሁ።

በአጼ ሃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ምንም እንኳን በየጊዜው ለሚነሱ የሕዝብ ጥያቄዎችና ተቃውሞዎች መልስ ለመስጠትና ለማብረድ ሙከራ ቢደረግም፣አልፎ አልፎም የሃይል እርምጃ በመውሰድ ለማብረድ ጥረት ቢካሄድም የሕዝቡን ብሶትና ምሬት ሊቀንሰው አልቻለም።በአንድ ወቅት በአንድ ቦታ የተነሳው ችግር በገሃድና በድብቅ በሌላው ጊዜ ወደ ሌላው ቦታ እየተዛመተ ውስጥ ውስጡን ሲብላላ፣ሲወድቅ ሲነሳ ኖረ።

የአጼ ሃይለስላሴ መንግስትና ሥርዓት እድሜ ልኩን በሰላምና ካላንዳች ተቃውሞ የተጓዘ አይደለም፡፡ በየወቅቱ በተለያየ ቦታ ተቃውሞና ሕዝባዊ አመጽ ገጥሞታል።ከዚህ በታሪክ ጎልቶ የሚታየውና የሚነገርለት ተቃውሞ በ1953 ዓ.ም. በከፍተኛ የጦር መኮንኖችና የንጉሱ ክብር ዘበኞች፣በሲቪል ባለስልጣኖችና በተማሩ

ዜንች የተደገፈና የተሳተፉበት መፈንቅለ መንግስት ነው።ምንም እንኳን የሶስት ቀናት እድሜ ብቻ ኖሮት የተቀጨው እንቅስቃሴ ግቡን ባይመታና በጦሩ መከፋፈል የተነሳ ቢኮላሽም ሙከራው ከንጉሱ ይልቅ ለሕዝቡ በተለይም ለተማረው ክፍል የትግል ምሳሌና ቀስቃሽ ደወል ሆኖለታል።በዚያ አጭር ወታደራዊ አመጽ ወቅት ስርዓቱን በማዳን ረገድ ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ሚና ተጫውታለች።የአገሪቱ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የመጀመሪያው ሊቃነ ጳጳስ የነበሩት አቡነ ባስሊዎስ የመስቀል አርማ የሰፈረበት ወረቀት በአውሮፐላን በማስረጨት ሕዝቡ አመጹን እንዲያወግዝና ለንጉሰ ነገስቱ እንዲገዛ በማሳሰብ እምቢ የሚለውንም በመገዘት ተባባሪ ሆነዋል።ይህን የመስቀል ምልክት በአናቱ ላይ ያሰፈረ በአረንጓዴ፣ቢጫና ቀይ ፣የኢትዮጵያ ባንዲራ መልክ ባላቸው ወረቀቶች በአውሮፐላን የተበተነ የግዝተትና፣ የውግዘት ጥሪ አጭር ጽሁፍ እየተሯሯጥን በመሰብሰብ ለቤተዘመድና ጎረቤት በማንበብ መልእክቱን ካደረሱት የሠፈር ልጆች አንዱ ስለነበርኩ ሁኔታውን በደንብ አስታውሳለሁ።የሦሥተኛ ክፍልም ተማሪ ስለነበርኩ እኔና ታላቅ ወንድሜ በእለቱ ምሽት በቤት ውስጥ የንባብ ውድድር አድርገንበታል።

ከዚህ «የታህሳስ ግርግር»በፊት በራያ ገበሬዎች በ'ኳላም ላይ በጎጃምና በባሌ የተነሳው ህዝባዊ እንቅስቃሴ ስርዓቱ ሰላም የለሽ መሆኑን ያሳያል።

ማንኛውም ሥርዓት መልካምና መጥፎ ገጽ አለው።የአጼ ሃይለሥላሤም መንግሥት እንደዚሁ ከመጥፎው ጎን ለጎን መልካምና ጥሩ ተግባሮችን አጣምሮ የያዘ ነበር። በተለይም በትምህርት በኩል ከሌሎቹ ነገሥታት የተሻለ ለውጥ ተገኝቷል።በዓለም አቀፍ ግንኙነትና ፖለቲካም የነበራቸውና አገራቸው የነበራት እውቅና ከፍተኛና የሚያኮራ ነበር። በአፍሪካም የአህጉሩ አባት ተብለው የሚቆጠሩ ሲሆን ለአፍሪካ ህብረት መመስረትም ግንባር ቀደሙን ሚና ተጫውተዋል። በዚያም መሰረት ዋና ጽህፈት ቤቱ በዋና ከተማቸው ለመሆን በቅቷል።አሁን ግን ያ የሰሩት ውለታ ተክዶ በጽህፈት ቤቱ አደባባይ ላይ የሌሎቹ መሪዎች ሃውልት ሲቆም የሳቸው ቦታም አልተሰጠውም።ይህ እሳቸውን ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ያደረገችውን አስተዋጽኦም የሚክድ ነው።እውነተኛ የኢትዮጵያ መንግስት ሲመሰረት የተካደው ታሪክ ቦታውን ያገኛል።

አንድ የታሪክ ምስክር የሆነውን ነገር እንደ ነበረ ማቅረብ ይኖርበታል መልካሙን ወይም መጥፎውን ብቻ እየመረጠ ካቀረበ የሚሰጠው ምስክርነት የተሟላ አይሆንም፣ አመኔታንም ያጣል።ስለሆነም በእኔ ዕድሜ የነበረውንና ያለፍኩበትንጊዜ በጥቂቱም ቢሆን ማሳየቱ ለአሁኑ ትውልድ በትንሹም ቢሆን ግንዛቤ ይሰጠዋል ብየአምናለሁ፤ወደፊት በሚገባ ለማብራራት እቅድ አለኝ።

ምንም እንኳን ያለፈ ታሪክ ቢመስልም አሻራው እስካሁን ድረስ ጎልቶ የሚታየው የጣልያን ወረራና የኤርትራ በቅኝ ግዛትነት መቆየት እንዴት እንደነበረ በጥቂቱም ቢሆን ታሪክ እየጠቀሱ ማሳየቱ ለተፈጠረው አልተገቢ መለያየት ግንዛቤ የሚሰጥ መስሎ ስለታየኝ ለማቅረብ እወዳለሁ።ማወቅ ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም።በፕሮፌሶር ሪቻርድ ፓንክረስ«መንግስትና መሬት በኢትዮጵያ ታሪክ»/"State and land in Ethiopian history" /ከሚለው መጽሃፍ ላይ ያገኘሁትን እንደሚከተለው ተርጉሜ ለማቅረብ ሞክሬያለሁ።

በኤርትራ ውስጥ የቅኝ አገዛዝ በውጭ ሃይል በተለይም በጣሊያኖች ተካሄደ እንጂ በራሱ ዜጋ በኢትዮጵያዊው አልተካሄደም።የጣሊያን ወረራና የቅኝ አገዛዝ እንዴት እንደተጀመረ በፕሮፌሶር ሪቻርድ መጽሃፍ ውስጥ ከተገለጸው በአጭሩ የህን ይመስላል፤-

## የጣሊያኖች ሰፈራ በኤርትራ

በኤርትራ የነበረው የመሬት ስሪት እንደተቀረው የኢትዮጵያ ግዛት በተለይም እንደ ሰሜኑ ክፍል በእርስትና በእርስተ ጉልት መልክ የተከፋፈለ ነበር።( እርስት መሬት ማለት ከትውልድ ትውልድ ለቤተሰብ የሚወራረስ

መሬት ማለት ሲሆን ጉልት ደግሞ እንደ ደመወዝ ለአገልግሎት መተዳደሪያ የሚሰጥ ፣አገልግሎት ሲያበቃ የሚመለስ መሬት ማለት ነው።)

በተደጋጋሚ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ በአጼ ዮሃንስና በራስ አሉላ አባ ነጋ መሪነትና አዝማችነት የአገሪቱን ብሄራዊ ነጻነትና አንድነት ከቱርክ፣ ከግብጽ ከሱዳንና ከጣሊያን ወራሪዎች ለማዳን በጉንዳት፣በጉራዕ፣በከረን፣ በኩፊት፣በዶጋሊና በመተማ የጦር ሜዳዎች ባካሄደው ትግል በህይወትና በንብረት ታላቅ ጥፋትና ውድቀት ደረሰበት።በተከታታይ ጦርነትና ችግር ተዳክሞ በ1889 እ.አ. አቆጣጠር መረብ በመለስ የጥንቱ ታሪካዊ ባህረ ነጋሽ የኢትዮጵያ ግዛት ከትግሬ ክልል ከአገሩም ተቆርጦ "ኤርትራ" በሚል ስያሜ በጣልያን ወራሪዎች እንደ ቅኝ ግዛት ተያዘ።

በኤርትራ ደጋማ ቦታ ላይ አውሮፓውያኖችን የማስፈሩ ሃሳብ በጣልያኖች የቅኝ ግዛት እንቅስቃሴ ውስጥ ታላቅ ትኩረትና ቦታ ነበረው።በየካቲት 1885 አድሚራል ቻይሚ/Caimi/ የማሳዋን ወደብ ያዘ።በ1889 ከዚያ ተጉዞ የደጋውን ቦታ ለመያዝ ቻለ።በዓመቱም መጨረሻ ላይ በበሽታ፣በጦርነትና በርሃብ የተነሳ ነዋሪው ለቆት የሄደውን አየሩ ለአውሮፓውያን የተመቸ ቦታ በቁጥጥሩ ስር አዋለ።

አስመራንና የከባቢውን ደጋማ ይቆጣጠር የነበረው ጄኔራል ባልዲሴራ ከሕዝቡ ጋር ላለመናቆርና ቅዋሜ ለማሶገድ ሲል በነሃሴ ወር /august-2-1889/ አንድ ያዋጅ መመሪያ አወጣ።በዚህም አዋጅ ለወንጀለኞች ምህረት እንደሚሰጥ፣ከዚህ በፊትም መሬት የተነፈጉት እንደሚያገኙ ቃል ገባ።መንግስቱ የጣሊያን መንግስት ነው።አትፍሩ፣ ኑ፣ የአባቶቻችሁ የነበረውን እርስት ጉልት ሹመት እሰጣችኋለሁ፤ቅረቡና ጠይቁ ብሎ ለፈፈ።

በኢትዮጵያ መሪዎች ላይ እርምጃ በመውሰድ ይዞታቸውን ነጠቀ፤በዚህ እርምጃው ሌሎቹን ፣ሕዝቡ የሚያከብራቸውን ሽማግሌዎችና የከባቢ ሹሞችን ግን አልነካም ነበር። ይዞታቸውን አክብሮላቸዋል።

በዚያን ጊዜ የሃማሴን ክፍለ ሀገር በራስ አሉላ ይተዳደር ነበር።የነበራቸው መሬትና በአስመራ የነበረው ቤታቸው ተወሰደ።በትግራይም የነበራቸው ሃብት እንዲሁ ተወረሰ።በአክሱም ብቻ የነበረው ቤታቸውና ንብረታቸው አልተነካም ነበር።ምክንያቱም የአክሱምን ሕዝብና የክርስቲያኑን እምነት ተከታይ በሙሉ ሊያስነሳ ይችላል በሚል ፍርሃት ነው።

መስፋፋቱ ከሞላ ጎደል ከተጠናቀቀ በኋላ ከጣሊያን ገበሬዎችንና የንግድና የፋብሪካ ባለቤቶችን ለመሳብ እቅድ ወጣ።የቦታው መስማማት፣የመሬቱ ለምነት፣የአየሩም፣የሁሉም ነገር መልካምነት በሰፊው ተነገረ።በተጨማሪም ለሚመጣው የጣሊያን ሰፋሪ የሚያስፈልገው ሁሉ፣የገንዘብም ሆነ የቁሳቁስ እርዳታ እንደማይነፈገው በመግለጽ ቅስቀሳው ተጧጧፈ።እንደ ውጥኑ ከሁለት ሚሊዮን በላይ ጣልያኖችን በማስፈር በጊዜው ጣልያን ተወጥራ የነበረችበትን የስራ አጥ ችግርና የምግብ እጥረት ለማርገብ ነበር።

ከጣልያኑ ወረራ ጋር ተያይዞ መረሳት የሌለበት ነገር ቢኖር ሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በታሪክ ታይቶ ተሰምቶ በማይታወቅ የኤኮኖሚ ችግር የተወጠረና  በጦርነት የደቀቀ ነበር።

ከ1875-1876 ከግብጽ ወራሪዎችና አባሪ ሽፍቶች ጋር ውጊያ ተካሂዶበታል።ከ1873-1878 ድረስ ያለው ጊዜ የመከራ ጊዜ ነበር።

የሽ መንደሮች መሬት ይባል በነበረው ከባቢ ግማሽ እንኳን የማይሆን የማይኖርበት ደረጃ ላይ ደረሰ። ሰው ተሰዶ የቀሩት ሰው የማይታይባቸው ጎጆዎች ነበሩ።በ1889 የተከሰተው የከብት በሽታ የአገሪቱን ጠቅላላ ከብት እንክት አድርጎ ጨረሰው።እርሻ ላይ የሚውል በሬ ጠፋ።የደሃው ገበሬ ቤተሰብ ለእርሃብ፣ለኮሌራና ለተስቦ በሽታ ተጋለጠ። እርሻና ቤቱን እየለቀቀ ከውጭ የገባ የእህል እርዳታ ፍለጋ ወደ ወደብ ዳርቻ ተሰደደ። በኤርትራ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላ አገሪቱ ላይ በጦርነትና ድርቅ ሳቢያ የተከሰተው ችግር የወረደው መከራ በግልጽ ጎልቶ ይታይ ነበር።በዚያ ሳቢያ የተከሰተው የመንደሮች/ የቦታዎች ባዶነት ለጣሊያን ወራሪ ሃይል ፣ለሰፈራ ፖሊሲ አመቺ ሁኔታ ፈጠረ።ይህን አጋጣሚ በመጠቀም በ1890 የጣሊያን ንጉስ ኡምቤርቶ በቅኝ ግዛት አገሮች

የመሬት ባለቤትነትን የሚያረጋግጥ መመሪያ ደንብና ሕግ አወጣ።ይህ ደንብ በጣሊያንና ከጣሊያን ውጭ የሚኖሩ ነጮችን ስሜት ስቦ በአስራ ሁለት ዓመታት ውስጥ ቁጥሩ ከሁለት ሚሊዮን ተኩል በላይ የሆነ ሰፋሪ ጣሊያንን ለቆ በቅኝ ግዛት ወደ ተያዘው የተለያዩ አገሮች ተንቀሳቀሰ።

የኤርትራ ደጋ ክፍል ለምና የውሃ/የዝናብ/ ችግር የሌለበት አየሩም ለአውሮፓውያን እንደሚስማማ በመግለጽ ሰፈራው ተቀባይነት እንዲያገኝ በፓርላማውና በሕዝቡ ዘንድ ሰፊ ቅስቀሳ ተደረገ።ለናሙናና ለሙከራ የሚሆን በ1890 ላይ የእርሻ ጣቢያ ከአስመራ ውጭ በጉራና፣በአካለጉዛይ እንዲሁም በሰራዬ በቁንዲ ፈላሲ ተቋቋመ። በረቀቀ ዘዴና ተንኮል የተወላጁ ንብረት የሆነው መሬት ከእጅ እየወጣ ለጣሊያን ሰፋሪዎች ታደለ። በአክሱምና በደብረ ቢዛን አዲስ የይዞታ /የካደስትራል/ ምዝገባ ተካሄደ።ባዶና በቀድሞ ባለስልጣኖች እንዲሁም በአማጽያን እጅ የነበረው ቦታ በቀጥታ በጣሊያኖች ቁጥጥር ስር ዋለ።

ምንም እንኳን ሰፊ መሬት በርካሽ እየገዙ በትርፍ የሚሸጡ ሰዎችን ያበረታታል የሚል ስጋት ቢያድርባቸውም በተለምዶ በገበሬው ቤተሰብ ሲወራረስ የነበረውን መሬት በግል ገንዘብ እየገዙ ለሚጠቀሙ ሰዎች መብትና ፈቃድ ተሰጠ።ይህ የመሸጥና የመግዛት ዘዴ የቅኝ ግዛትን ለማስፋፋት የመጀመሪያው የመንደርደሪያ እርከን በመሆን አገልግሏል። በኢትዮጵያ በነበረው የአገሪቱ ሕግ መሰረት በኤርትራም የእርስቱ ባለቤት የሆነው ተወላጅ በምንም ጊዜ ቢሆን ከመሬቱ የሚነቀልበት ሕግና ልማድ አልነበረም።ከቦታው ለዘመናት የተለያዩ ቢሆን እንኳን ተመልሶ ሲመጣ የሚገባውን የውርስ መሬት የማግኘት መብቱ የተጠበቀ ነበር።ስለሆነም ጣሊያኖች ለጊዜው ከሕዝቡ ጋር ላለመጋጨት ሲሉ ያተኮሩት ሕዝብ ጥሏቸው በሄደው ወይም ባልተጠቀመባቸው ሰፋፊ መሬቶች ላይ ነበር።በወቅቱ ጌራርድ ሮልፍ የተባለው የጀርመን ጸሃፊ እንደዘገበው የጊንዳ ሸለቆ ብቻ ከ 1000 ሰው በላይ ሊያሰፍር እንደቻለ መዝግቧል።

በ1893 መጨረሻ ላይ በአዲ ኡቅሪ የሰፋሪዎቹ የድንጋይ ቤቶች መገንባት ተጀመሩ።በዚሁ ዓመት መጨረሻ ላይ በዲሴምበር ወር የመጀመሪያዎቹ 29 የጣሊያን ገበሬዎች ከ15 ሴቶችና 17 ህጻናት ልጆች ጋር ሆነው በቦታው ሰፈሩ።ለያንዳንዱ ቤተሰብ ከ20-25 ሄክታር የሚሆን ቦታ፣የእርሻ መሳሪያ፣ከብትና ምርት እስኪሰበሰብ ድረስ የሚያስፈልጋቸው የምግብ እርዳታ ድጋፍ ተሰጣቸው።ከጥቂት ጊዜም በኋላ ሁለት መቶ ጣሊያኖች ተመሳሳይ ስጦታና እርዳታ ተደርጎላቸው በዚሁ በጊንዳ ሸለቆ ሰፈሩ።

ሆኖም ግን ያ ተስፋ የተጣለበትና ብዙ የተነገረለት ሰፈራ እንደተጠበቀው ሆኖ አልተገኘም።በድርቀትና በረሃቡ ክፋት የተነሳ ሰፋሪው ከችግር ላይ ወደቀ።አስተዳደሩም የገባውን ቃል ለመፈጸም ተሳነው።አልፎ ተርፎም ውሃና ደረቅ ምግብ መጓጓዣ በቅሎ ሳይቀር ከጣሊያን ድረስ ለማስመጣት ተገደዱ።ይህ ሁኔታ በባለስልጣኑ መካከል ሽኩቻና ቅራኔ ቀሰቀሰ።ተስፋ መቁረጥ፣ እርስ በርሱ መናከስና መወነጃጀል ጀመሩ።

ይህ ውጥረት በሰፈነበት ሁኔታ የጣሊያን መንግስት በሰፈራው ላይ የነበረውን አቋም በማጠናከር ሌላ መመሪያ አወጣ።በዚህ መመሪያ ማንም ቢሆን፣የቀድሞ ባለመሬትም ቢሆን በተለቀቁ ባዶ መሬቶች ላይ ከጣሊያን አስተዳዳሪዎች ፈቃድ ውጭ መስፈር እንደማይችል ተደነገገ።ይህ መመሪያ የተወላጁን የይገባኛል መብት ሽሮ ለአዲስ መጡ የጣሊያን ሰፋሪዎች ሙሉ ዋስትና የሚሰጥና የሚያረጋግጥ ሆነ።

ተወላጁ በነባር ቦታው ላይ ከቆየና ከሰፈረ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑና ከአማጽያኑ ጋር ለመገናኘት ስለሚረዳው፣በባንዳነት የገቡትንም ልብ ስለሚያሸፍት በሕግ ማገዱ ተገቢ ነው ብለው አመኑ።ከኤርትራ ውጭ በተለይም በትግራይ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ መጥቶ ሊሰፍር ይችላል ብለው ስለሰጉ የመሬት ባለቤትነትን መብት ነፈጉ።እርግጥ በጦርነቱና ታላቁ እርሃብ ባስከተለው ችግር ከየአቅጣጫው ሕዝብ እየፈለሰ ወደ ሌላ ቦታ የሚሄድበት ወቅት ነበር።የጣሊያኖችም የእርሻና ከዚህም ጋር የተያያዘ አንዳንድ ጥቃቅን ድርጅት ለብዙም ባይሆን ለጥቂቱ የአገሩ ተወላጅ "ስራ አገኛለሁ"በሚል ጉጉት ወደ ኤርትራ ለመፍለስ ፍላጎት አሳድሮ እንደነበር አይካድም።

በአስመራ በከረንና በአንዳንድ ጠቃሚ ቦታዎች ላይ የጣሊያኖቹን ሰፈራ ማስፋትና የኑዋሪውን ቁጥር ማሳደግ እንደ አስተማማኝ መሳሪያ ተደርጎ በጥቂት ጊዜ ውስጥ በነዚህ ቦታዎች ውስጥ የሚኖረው የመጤ ነጭ ቁጥር ከእጥፍ በላይ አደገ።በጠፍና በአማጽያን ንብረትነት ስም ብዙ መሬቶች በውርስ በጣሊያን አስተዳደር ተወሰዱ። ከ1893-1895 በሁለት ዓመት ውስጥ ብቻ በነዚህ ከባቢዎች ከ315.000 ሄክታር በላይ መሬት ውርስ ሆነ።

ከባቢውን ለመጎብኘት የቻለው ዊልድ የተባለው ሰው እንደገለጸው በተወላጁ ለዘመናት በጥሩ ሁኔታ የለሙ ሰፋፊ መሬቶች አሁን በመጡ ነጮች ተነጥቀው ለማየት ችያለሁ፤ ኢትዮጵያውያንን መጨረስና ቁጥራቸውን እንደ አውስትራሊያና ኒውዚላንድ ተወላጆች ማመናመን አይቻልም፤በጣም ብዙዎች ናቸው።ኢትዮጵያውያንን በሚገባ መንገድ ካልያዟቸው እሽ ብለው አይኖሩም።ለጥሩ እንጂ ለመጥፎ ነገር አይመቹም። ሰላም ወዳዶች ናቸው፤ ስለሆነም የተያዘው መንገድ ጣሊያኖች የሚጠፉበት ይሆናል ሲል ለመጠቆም ሞክሯል።

ከዳግማዊ ምኒሊክ ጋር በውጫሌው ስምምነት መሰረት ( በ 02/05/1889)የገዳማት መሬትና ይዞታ እንደተጠበቀ ሆኖ ንብረትነቱ የኢትዮጵያ መንግስት ነው።በሚለው ስምምነት ሁለቱም ወገኖች ፈርመው ነበር። ነገር ግን ጣልያኖቹ የመጀመሪያ ብትራቸውን ያሳረፉት በዚሁ በደብረ ቢዛን ገዳም ላይ ነበር።በዚህ የተነሳ ቀሳውስቱና መነኮሳቱ ጉዳት ደረሰባቸው።ስለሆነም በቀይ ባህር ከባቢ በጣሊያኖች ላይ ከተነሳባቸው ቅዋሜና አመጽ የመጀመሪያውን ቦታ የያዘው የነዚሁ መነኮሳቱ የቀሰቀሱት ተቃውሞ ነበር።

የጣሊያኖቹ የእለት ተእለት የቦታ ዘረፋና ንጥቂያ የሕዝቡን ተቃውሞ ቀሰቀሰ። በተለይም የጣሊያኑን የካቶሊክ እምነት ተቀብለው የአጼ ዩሃንስንና የራስ አሉላን ጦር በመውጋታቸው በጣሊያኖቹ ታማኝ አጋር ተብለው የተወሰዱት ፤በአንድም ወቅት ላይ አድዋን በቁጥጥራቸው ስር እስከማድረስ ችለው የነበሩት ደጃዝማች ባህታ ሃጎስ በዚሁ የመሬት ምሪት ሳቢያ በተለይም በአካለ ጉዛይ በጣሊያኖች ላይ ለማመጽ ወንድማቸውን ሸንግልን አማከሯቸው።ወንድማቸው፣ሸንግል በምን ምክንያት በጣሊያኖች ላይ እናምጻለን? ብለው ቢጠይቋቸው፣ወንድሜ ሸንግል ሞኝ አትሁን፤ነጭ እባብ ቢነክስህ ከሚደርስብህ ጉዳት ምንም ብትሞክር አታመልጥም፣ልትድን አትችልም፣ አሏቸው ይባላል።

ደጃች ባህታ በአመጹ ጊዜ ጣሊያኖች መሬታችንን እየወሰዱ ነው፣እናውግዛቸው እንታገላቸው፤የሚል ጥሪ በማድረጋቸው ብዙ ሕዝብ በተለይም በትግራይ የራስ መንገሻ ወታደሮች ሳይቀሩ "ጥቁር እባብ ቢነክስ መርዙ አይገድልም፣ትድናለህ፤የነጭ እባብ መርዝ ግን ይገልሃል፣አትተርፍም"በማለት ከዳር እስከ ዳር ተነሳ።ይህ አይነቱ የተቃውሞ ጥርቅም ተከታዩን የአድዋ ጦርነት ወልዶ ጣሊያን በጥምር የኢትዮጵያ ሃይሎች በመጋቢትወር 1888 ዓ.ም.(01-03-1896) ድል ሆነ።በዚህ ሽንፈትና ውድቀት የተነሳ በተለይ በጣሊያን መንግስትና ሕዝብ ፤ በአጠቃላይ በአውሮፓ ቅኝ ገዥ መንግስታት ዘንድ ትልቅ መደናገጥና ብስጭት እንዲሁም የውስጥ/የርስ በርስ /ቅርሾና ጭቅጭቅ ቀሰቀሰ።የሰፈራው መመሪያ/ፖሊሲ/ በራሳቸው በጣሊያኖች ፓርላማ እንዳለ ተወገዘ። በኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክና ልማድ እንዲህ አይነቱ ዘዴና እርምጃ ከጥቅሙ ጉዳቱ እንደሚያመዝን በመረዳት ባዶ ቦታ ተብሎ የተያዘው መሬት በሙሉ ባዶ መሬት እንዳልነበረ፣ሰው ሰፍሮበት የቆዬና በችግርና በጦርነት ምክንያት ሕዝብ ተገዶ የለቀቀው መሆኑ ታመነበት።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮና ህይወቱ ከመሬት ጋር የተያያዘ ስለሆነ ያንን መንካት መድፈርና ማሳጣት በጣሊያኑ አስተዳደር ላይ ትልቅ ጠላትነትና ችግር ለመፍጠር ቻለ።ይህ በጣሊያኖች የተወሰደው እርምጃ የኢትዮጵያኑን ልብ ሙሉ ለሙሉ ወደ አገራቸው መለሰው።ምንም እንኳን በአገራችን፣በራሳችን መንግስት ፍትህ ቢጓደልም፣ ብንበደልም ከፍተኛ ግብር እንድንከፍል ብንገደድም ከመሬታችን የሚነቅለን ህግና ባለስልጣን የለም።በኤርትራ የሰፈነው የጣሊያን መንግስት አካል ግን መሬታችንን ነጥቆ ማንነታችንን ገፎ ለመኖር ሞከረ።እኛ ግን ተመልሰን እንደ ዱሮው ለመኖር ወስነናል በማለት የጣሊያኖቹን የቅኝ ግዛት የከፋፍለህ መመሪያ ውድቅ አደረጉ።

ማርቲኒ የተባለው የኤርትራ የቀድሞ አስተዳዳሪ ይህንኑ ሲያረጋግጥ ፤የተወሰደው የመሬት ቅሚያና የጣሊያን መመሪያ ደንብ ሕዝቡን ከአጼ ምንሊክ ጋር እንዲሰለፍ አድርጎታል።በአዲ ቋላ በተለይም በደብረ ማርቆሪዮስ

ገዳም ውስጥ የነበሩት መቶ ሃምሳ/150/ የሚሆኑ መነኮሳት ለጣሊያኑ አገዛዝ የእግር ውስጥ እሳት ሆነውበት ነበር ሲል የእምነት ቃሉን ሰጥቶበታል።

በኤርትራና በትግራይ ብቻ ሳይሆን ሱዳን ውስጥም የሚኖሩ የከባቢው ተወላጆች በአመጹ ውስጥ ተካፍለው እንደነበር ጨምሮበታል።የባህታ ሃጎስ አመጽና ከራስ መንገሻ ጋር የተካሄደው ውጊያ ጣሊያኑን አዳክሞ የኩዶፈላሲን ሰፈራ በጠበጠው።በዛም ሳይቆም ጣልያኖች ከመቀሌ ለቀው ወጡ።በዓመቱ መጨረሻ ወር በ1895 ላይ የሰፈሩት ሁሉም መጤ የጣሊያን ዜጎች ተርበተበቱ።ሰፈራቸውን እየለቀቁ ወደ ወደብ ገሰገሱ።የተወጠነው የሰፈራ ህልም እንዳያገግም ሆኖ ከፍተኛ ውድቀት ደረሰበት።ለአደዋ ጦርነት ድል ይህ ፖሊሲ የቀሰቀሰው ተቃውሞ አስተዋጽኦ እንዳደረገ ታምኖበት የመሬት መውረሱና መያዙ ፣መቀራመቱ መመሪያ/ፖሊሲ/ ውድቅ ሆኖ ተሰረዘ።

ጣልያኖች በአድዋ ጦርነት ከደረሰባቸው ውድቀት በመማር ሌላ የተለዬ የመሬት ይዞታ መመሪያ ይዘው ብቅ አሉ።በጦርነት ላልተሳተፉትና ላላመጹት የቀድሞ ባለመሬቶች ማካካሻ/ካሳ/ለመስጠት የጣሊያኑን ህግና መመሪያ የማይቀበለውን ደግሞ ከእርስተ ጉልቱ ለመንቀል የሚያስችል አዋጅ ወጣ።

የጣሊያኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የነበረው ቶማሶ ተቶኒ በግንቦት ወር/በ16-05-1907 እ.አ.አ/ ለፓርላማው በሰጠው መግለጫ እንደገና የሰፈራው ሂደት እንዲያንሰራራ ቅስቀሳ አካሄደ።ከአለፈው ውድቀትና ስህተት በመማር አዲስ የማያስነቃ ዘዴ መጠቀም እንደሚገባ ጨምሮ አሳሰበ።ያልተያዘውን ባዶ ለም መሬት በቀጥታ ለመያዝ ፣በተወላጁ የተያዘውን መሬት ደግሞ ካሳና የኪራይ ገንዘብ እየሰጡ መልከኛውን/ነዋሪውን /መንቀልና መሬቱን መውሰድ የሚለው አማራጭ ፖሊሲ ተነድፎ በተግባር ላይ መዋል ጀመረ።

## የጣሊያኖች በምዕራቡ የኤርትራ ክፍል የነበራቸው የተለዬ መመሪያ/ፖሊሲ

በምዕራቡ ቆላማ ክፍል ከቀረው ደጋማ ክፍል የተለዬ በመሆኑ ችግር ፈጥሮባቸው ነበር።ትግርኛ ተናጋሪ በሆነው የከረንና የአቆርዳት ሕዝብ መካከል ለረጂም ጊዜ የነበረው የርስ በርስ ግጭትና የሻከረ ግንኙነት ሁለት የማይጣጣሙ ማህበረሰቦችን ለመፍጠር በቅቷል።

ይህ አስጋዳና ትግሬ በመባል የፊተኛው መሳፍንት የኋለኛው ደግሞ ገባርና የበታች ሆኖ እንዲያድር የሚያስገድድ ልማድ የሚንጸባረቅበት ከባቢ ከሌላው የኤርትራ መሬት የተለዬ የውስጥ ችግር ነበረበት።

የአስጋዳ ወገን ከፍተኛ ስልጣንና ሃይል ስለነበረው ትግሬውን እረግጦ የማሳደር ሲያሻውም ባሪያ ብሎ ሰይሞ የፈለገውን ሊያደርገው የሚያስችል ጉልበትና ባህላዊ መብት ነበረው።ትግራዩ ከዚህ የበታችነት ወይም የባርነት ሰንሰለት የሚወጣው ወንዱ ሃያ ማሪያ ተሬዛ/የድንጋይ ወይም ጠገራ ብር/ሴቷ ደግሞ ሰላሳ ጠገራ ብር ከከፈሉ ብቻ ነበር።

ጣልያኖቹ ምንም እንኳን የተሻለ አስተዳደር ባያመጡም በመጀመሪያው ወቅት ላይ ይህን አይነት ኢሰብአዊ የሆነ ልማድና ግንኙነት በማየታቸው ለመጀመሪያ ጊዜ በጣም ደንግጠው ነበር።የኋላኋላ ግን እነሱ ብሰው ቁጭ አሉ።

ይህንኑ ኢሰብአዊ አድራጎት የታዘበው ጣሊያናዊ ምሁር የጨቋኙን የአስጋዳን ወገን "ጥቂቶች ኢሰብአውያን በብዙሃኑ/በትግሬው ላይ እንደ መዥገር ተጣብቀው የሚመጠምጡ የሰው ትሎች" ሲል ሰይሚቸዋል።ሆኖም ግን የጣሊያኖቹ አስተዳደር በጣም አስከፊውን ገጽ ከማሻሻል አልፈው ሙሉ ለሙሉ ለመቀየር አልቻሉም።ወይም ፈቃደኞች አልሆኑም ነበር። ትግሬዎች መንግስት በደላቸውን እንዲመለከትላቸው ቢጠይቁም ሙሉ ለሙሉ እነሱን ከአስጋዳን ጓዳ/መዳፍ/ ስር ማላቀቁ የጠብና

የአምባጓሮ መቀስቀሻ ምክንያት ሊሆን ይችላል በሚል ስጋትና የዘመናት በሽታ ስለሆነም ለመለወጥ ዘመናት ይፈጃል ብለው በመገመት ችላ ብለውታል።

እነዚህ በሁለት ማህበረሰብ ተከፍለው እርስ በርስ ፣የበላይና የበታች፣ጌታና ባሪያ ሆነው የኖሩ ያንድ አገር ልጆች ከየት መጡ?እንዴትስ ኖሩ? ብሎ መጠየቅና ማወቅ ተገቢ ነው።

ኤርትራ እራሱን የቻለ አንድ ማህበረሰብ የሚኖርበት ክልል ሳይሆን የትግሬ፣የኩናማ፣የናራ፣የቢለን፣የትግረ፣የሳሆ፣የአፋር፣የቤጃ፣የቢነአምርና የራሻይዳ ማህበረሰብ የሚኖርበት እንደተቀረው የኢትዮጵያ የክርስቲያንና የእስላም ሃይማኖት የሚስተናገዱበት ህብረ ምድር ነው።አንድ ወጥ ቋንቋ የሚነገርበትና አንድ ሃይማኖት የሚከተል ሕዝብ ሚኖርበት አገር አይደለም።

በአክሱማውያን ዘመን ፍጻሜ በዛሬው የኤርትራና የትግራይ ኩታ ገጠም ክልል የተካሄደው ታላቁ የቤጃ ሕዝብ ፈለሳና ሰፈራ ሂደት የሚታወስ ነው።በኤርትራ ትግረና ሳሆ በመሳሰሉት ነባር ሕዝቦች ላይ ለዘመናት የጉልተኛ ስልጣንና ስርዓት የመሰረቱ የበለውና የቤንዓሚር ባላባታዊ ካስቶች የተጠቀሰው የቤጃ ሕዝብ ፍልሰትና ሰፈራ ውጤቶች ናቸው።

ከዘጠነኛው መቶ ዓመት መጨረሻ እስከ አስራ ሶስተኛው መቶ ዓመት ድረስ በመሃል ሰሜኑ ደጋማ ክልል በአክሱማውያን፣በፈላሻ፣በአገውና በአማራ መሳፍንቶችና የጦር አበጋዞች መካከል እረጅም የስልጣን፣ የግዛትና የጎሳ ጦርነት በተካሄደበት ዘመን ከላስታ አካባቢ የአገው ክርስቲያናዊ ሰደተኞች በኤርትራ በትግረና በናራ ነባርና አጎራባች ሕዝቦች ክልል ላይ ሰፍረው ለዛሬው ኩሻዊ የቢለን ማህበረሰብ መነሻ ሆኑ።

በአስራ አምስተኛው መቶ ዓ.ም ገደማ ከትግራይ አንድ አስገዴ የሚባል ክርስቲያናዊ ሹምና አለቃ ከተከታዮቹ ጋር በባርካ ቆላማ ክልል በትግረና በቤጃ ሕዝቦች መካከል ሰፈረ።እሱም "ቤተ አስገዴ"ተብለው ለሚጠሩና የሃባብ፣የአዲ ተክለና የአዲ ማርያም ባላባታዊ ማህበረሰቦች ብሎም በትግረ ገባሮች ምርትና ጉልበት ለሚኖሩት "ሽማግሌ"ተብለው ለሚታወቁ ጉልተኞች የጎሳ አባት ነው።

የአስገዴው ባላባታዊ ስርዓት ተንሰራፍቶ በነባሩ ሕዝብ ላይ የባርነት ሰንሰለቱን ዘረጋ።

በሁለቱ ማህበረሰቦች ማለትም በአስገዴውና በትገረው ወገን መካከል ሲሰራበት የነበረው ኢሰብአዊ ግንኙነትና ግዴታ መካከል ዋናዎቹ ከዚህ የሚከተሉት አራቱ ነበሩ።

1ኛ.-ወጥጸሃይ/የጸሃይ ላም/(cow of the sun) ግጦሽ በማይኖርበትና ላሞች በሚነጥፉበት በበጋው ወቅት ከብት ያለው ትግሬ ለአስጋዳው ለእርድ የሚሆን አንዱን የመስጠት ግዴታ፤እንዲቀበል፣-

2ኛ.-ወጥመካን የትግረው የሆኑትን መካን ላሞች አስጋዳው እኩል የመካፈል መብት የሚያረጋግጥ፤

3ኛ.-ነጋለት እለፍ (goat of syphilis)የቂጥኝ ፍየል፣አስጋዳውን ቂጥኝ ወይም ጨብጥ ሲይዘው እስኪድን ድረስ የትግረውን ፍየል እያረደ መመገብ የሚያስችለው መብት፤

4ኛ.-መስቃንገል አንድ አስጋዳ በሱ ስር ያለውን ትግረ ባገኘ ቁጥር አንድ ጠገራ ብር ለማስገበር የሚችልበት ግዳጅ፤

እነዚህ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ሲሰራባቸው የኖሩ ግዳጆች በጣልያኖቹ ትእዛዝ ተወግደው ሌላ ዘጠኝ ግዳጆች በትግረው ትከሻ ላይ ተንጠልጥለው ቀሩ።እነሱም፣-

1ኛ.-መዳኒት፣-ትግረው ለአስጋዳው እንዳለው የከብት ብዛት መጠን ቅቤ ወይም ለመንጋ ከብት በገንዘብ አራት ጠገራ ብር ፣ለመንጋ ፍየል ሁለት ጠገራ ብር የመክፈል ግዴታ፤

2ኛ.-ወጥ ሃሊብ(የወተት ላም)/milk cow/ትግረው ለአስጋዳው በክረምት አንድ በበጋ ወር ሌላ አንድ የሚታለብ ላም ማቅረብና ሲነጥፉ መልሶ እንዲወስድ የሚያስገድድ

3ኛ.-ታሊት ሃሊብ (የወተት ፍየል)/milk goat/እንደ ወጥ ሃሊብ ሆኖ በላም ፋንታ የፍየል ነው።

4ኛ.-ሺመት ጊልሳ/gift of cover/ትግረው ለአስጋዳው በክረምት ጊዜ ለብርድ መከላከያ እንዲሆነው የሱፍ ብርድ ልብስ ወይም ፍየል፣ወይም ብር መስጠት ይኖርበታል፤

5ኛ.-ጃመል ዛን(የመጓጓዣ ግመል)ትግረው አስጋዳው በዓመት ሁለት ጊዜ ለሚያደርገው ጉዞና መንቀሳቀስ ግመል ማበርከት ይኖርበታል፤

6ኛ ዙም ባላት (ለጋብቻ ስጦታ)/marriage present or gift/አስጋዳው ሲያገባ ወይም ሲድር ትግረው ስጦታ ማቅረብ ይኖርበታል፤

7ኛ.-ሮጋዝ /funeral/አንድ አስጋዳ ሲሞት ለቀሪ ዘመድ ወይም ልጅ ትግረው ማስተዛዘኛ አንድ ላም ወይም ፍየል መስጠት ይኖርበታል፤

8ኛ.-ታሊት ሃጂ/goat of the haj/አስጋዳው ለዝየራ ወደ መካ ሲሄድ ትግረው አንድ ፍየል መስጠት ይኖርበታል፤

9ኛ.-ጽዮን/hospitality/አስጋዳው የመንጋና የከብት ይዞታውን ለመጎብኘት በወጣ ጊዜ ትግረው በቀን ሁለት ጊዜ የሚጠጣ ወተት ማቅረብ ግዴታው ነው። ጣልያኖች ይህንን ብቻ አለሳልሰው አስጋዳው ብዙ ቀን እንዳይቀመጥ /እንዳይቆይ/ትእዛዝ አስተላልፈው ነበር።

ምንም እንኳን አንዳንድ የጥገና ለውጦች ቢደረጉም ልማዱን "የመሳፍንቱ"የአስጋዳዎቹ ጥቅምና ስልጣን እንደተጠበቀ ቆዬ።በዚህም ዘዴ ጣሊያኖች ከአስጋዳው በኩል ሊቀሰቀስባቸው የነበረው ግንኙነት ቀርቶ ወደ መረዳዳቱ አመዘነ።

በ1947 በተደረገው የአራቱ ሃያላን አገሮች ኮሚሽን ጉብኝት ላይ የጣሊያኑ ተወካይ እንደገለጸው ይህን አጉል የቆዬ ልማድ ሙሉ ለሙሉ ማንሳትና ማሶገድ ጭራሽ ብጥብጥና ሽብር መቀስቀስ ነው ብሏል። ስለዚህም ጣሊያኖች ለቀው ከወጡም በኋላ በእንግሊዞች ጊዜም ይህ ኢሰብአዊ የሕዝብ ግንኙነት የሆነው የትግረዎች ለአስገዴዎች ማሟላት የሚኖርባቸው የባርነት ግዴታ ተከብሮ ቆይቷል።

የተርጓሚው አስተያየት- ይህን ከዚህ በላይ የተገለጠውን በኤርትራ ምድር ውስጥ ሲከናወን የኖረ የውስጥ ኢሰብአዊ ልማድና የሕዝብ ግንኙነት ስናይ አማራው እንዲህ አደረገን፣ ኢትዮጵያዊነት ማለት መከራና ስቃይ ማለት ነው ብለው ለመገንጠል የፈለጉትና ጥረት ያደረጉትን ሁሉ እራሳቸውንና ታሪካቸውን ያለፉበትን ጎዳና ዘወር አድርገው እንዲመለከቱና ከነበራቸው የተሳሳተ አቋምና ጥላቻ ወደ መከባበርና መቀራረብ ሊመልሳቸው ይችላል የሚል ግምት አለኝ።ከአማራው ይልቅ በራሳቸው፣አብሯቸው በኖረው ጎሳ እርስ በርስ ሲዋቀጡ መኖራቸውን ልብ እንዲሉት ያሻል።በሌላውም ከባቢ በዚሁ መከረኛ አማራ ማህበረ ሰብ ላይ የሚወርደው ውርጅብኝ ከዚህ የተለይ አይደለም።

ግራም ነፈስ ቀኝ በዚህ ያገሪቱ ዜጋ፣በአማራው ላይ የሚወርደው የስም ማጥፋትና ውንጀላ ዋና ምክንያት የሆነው ለአገሪቱ አንድነት ግንባር ቀደም ሆኖ ከሌሎች ወገኖቹ ጋር አብሮ በመቆሙና ለውጭ ወራሪ ሃይሎች ውጋትና የቋያ እሳት፣የማይበገርና የማይደለል፣ለቅኝ ገዥዎች የማይመች አገሩን የሚወድ ዜጋ በመሆኑ ነው።

ኢትዮጵያን ከውጭ ሃይሎች የተከላከለና ነጻነቷን ያስከበረ የአማራው ማህበረሰብ ብቻ አይደለም፤የሁሉም ማህበረሰብ ተወላጅ የድርሻውን አበርክቷል።ከነጻነትም በኂላ በኤኮኖሚውና በማህበረሰብ እንቅስቃሴዎች የሁሉም ተሳትፎ አለበት፡፤በእርሻው፣በንግዱ፣በትምህርቱ፣በጤናው፣በግንባታው ስራ ሁሉ ኤርትራዊው፣ኦሮሞው ትግሬው፣አማራው፣ጉራጌው፣አፋሩ፣ሃድያው ወላይታው፣...ወዘተ በሙሉ ተሳትፏል።ሁሉም የአገሪቱ ጥቅምና ጉዳት ተካፋይ ነው።

በወያኔና በሻእቢያ የጥቅም ግጭት የተነሳየኤርትራ ህዝብ ከወገኑ ተለያይቶ እንዲኖር ተፈረደበት።ተገንጥሎ መኖሩ ግን የተሰጠውን የተስፋ ዳቦ በእውን የገመጠበት ሳይሆን በራሱ ቋንቋ ተናጋሪዎች የመከራ መዳፍ ውስጥ ገብቶ መሰቃየት,መሞት,መሰደድ ሆኗል።ለዘላቂ ሰላምና አንድነት የእርቅና የመግባባት ስራ አሁን መጀመር አለበት።

መቸስ ምን ይደረግ!በውድም ሆነ በግድ ኤርትራ አንድ ጊዜ ነጻ አገር ሆናለችና ተቀብሎ በጎረቤትነት መኖር ነው የሚል አስተሳሰብ በስፋት ይሰማል።የእኔ አቋም ግን ከዚህ የተለዩ ነው።ምንም እንኳን በአሻጥርና በጉልበት ብትገነጠልም፣ሕዝቡ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣በታሪኩ፣በእምነቱ፣በመልኩ፣በስሙ፣የሚመሳሰል፣ተጋብቶ የተዋለደ፣ባህርና ውቅያኖስ የማይለየው የአንድ ወጥ መሬት ተወላጅ፣ በመሆኑ መነጣጠል የለበትም የሚል ነው።እንግሊዞች ባሕር ተሻግረው የሌላ አገር መሬት ጅብራልታርንና፣ከ15000 ኪሎሜትር እርቆ የሚገኘውን የአርጀንቲናን ክልል ያገባኛል የኔነው ብላ ጦርነት ስትገጥም፣ቻይና ከ70 ዓመት በፊት የተገነጠለችባትን የታይዋንን ደሴት ይገባኛል ፣ የኔ ነው ብላ ስትከራከርና በአሁኑ ጊዜ የመዋሃዱ ዕድል ሲያመዝን፣ ይችው ቻይና ለመቶ አርባ ስድስት ዓመት በእንግሊዝ ቅኝ ስር ወድቃ የቆየችውን የሆንግኮንግ ግዛቷን ስታስመልስ ታሪካዊ መብት ያላት ኢትዮጵያ ኤርትራን የማታስመልስበትና የተነጣጠለው ሕዝቧ እንደገና የማይዋሃድበት ምክንያት አይኖርም።ለዚህ ጦርነት መማዘዝ ያስፈልጋል ማለት ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ የኤርትራም ጭምር ድምጽ ሊሰጥበት ይገባል።የአንድነትና የነጻነት ደጋፊዎች ካለምንም ተጽእኖ፣በነጻ ተንቀሳቅሰው፣ሕዝቡን አሳምነው የሚደረስበትን ሕዝበ ውሳኔ አክብሮ መቀበል ይገባል።ያ እስኪሆን ድረስ ግን ኤርትራን ነጻ አገር አድርጎ መቀበልና ኢትዮጵያ የኔ ግዛት ነው ማለት አትችልም ብሎ መፍረድ ትክክል አይደለም።ሌባ ሰርቆ ስላመለጠ የሰረቀው ንብረት ይርጋለት፣የተሰረቀው ባለቤት ለማስመለስና የኔ ነው ለማለት መብት የለውም እንደማለት ነው።በግርግር ፣ኢትዮጵያ በተዳከመችበትና መሪ ባጣችበት ጊዜ የተደረገ ደባ ሕጋዊነት አለው ብዬ አላምንም።

ስለ ኦሮሞ ሕዝብ ታሪክ

በሌላው አቅጣጫ አገሪቱን ቀስፎ የያዘውና ለአንድነቷ አደጋ በመሆን የሕዝቡን ሰላማዊ ኑሮ የሚፈታተነው በአንዳንድ የኦሮሞ ተወላጅ በሆኑ ምሁራን የተጠነሰሰውና የሚራመደው ጸረ ኢትዮጵያዊነት የሆነው አዝማሚያ ነው።

እነዚህ ምሁራን እንደሚሉት የኦሮሞ ሕዝብ ኢትዮጵያዊ ያልሆነ፣እራሱን ችሎ በዲሞክራሲ ስርዓት ሲተዳደር የኖረና ከመቶ ዓመት ወዲህ በተፈጠረችው ኢትዮጵያ በምትባል አገር በሚኖር በአማራ ብሔር ነጻነቱን ተገፎ በቅኝ ግዛት ስር የሚተዳደር አገርና ሕዝብ ነው ይላሉ።

የዚህን የፈጠራ ታሪክ ባዶነት በሚቀጥለው የታሪክ ዘገባ ውድቅ ማድረግ ተገቢ መሆኑን በማመን በአጭሩ ለማቅረብ ተገድጃለሁ።

የኦሮሞ ሕዝብ እንግዳና ባዳ ሳይሆን ከአገሪቱና ከቀረው ሕዝብ ተቀላቅሎ፣በስርዓቱና በአስተዳደሩ ተካፍሎ የኖረ፣ ለኢትዮጵያ ነጻነት ከውጭ ወራሪዎች ጋር በተደረገው ተደጋጋሚ ጦርነትና ውጊያ ከሌሎቹ ወገኖቹ ጋር ተባብሮ የህይወት ዋጋ የከፈለ ሕዝብ ነው።

የኦሮሞ ሕዝብ ኢትዮጵያዊ መሆኑን የሚያረጋግጡና የሚመሰከሩ የታሪክ መረጃዎች አያሌ ናቸው። ኢትዮጵያን ከኦሮሞ፣ኦሮሞን ከኢትዮጵያ ነጣጥሎ ማየት ቀርቶ ማሰብ አይቻልም።በባህልና በቋንቋ ውርርስ፣ በሃይማኖት ፣ በፖለቲካ፣በኤኮኖሚ ከዛም በላይ በትውልድ ሃረግ የተሳሰሩ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጾች ናቸው። የኢትዮጵያ ሕዝብ የተቀላቀለ ሕዝብ ነው።በኋላ የመጣው በፊት ከመጣው ጋር ተቀላቅሏል።አንዱን ካንዱ መለየት አይቻልም።እንኳንስ በአሁኑ በሰለጠነውና ህዝብ ከአንዱ ከባቢ ወደ ሌላው በቀላሉ መጓዝ በሚችልበት ጊዜ ቀርቶ በጥንቱም ጊዜ እንኳንስ ተራው ሕዝብ በስልጣን ላይ የነበሩትም ነገስታት ከሌላው ብሄረሰብ ጋር ተጋብተው ፣ተዋልደው ስልጣኑን እየተቀባበሉ ኑረዋል።የአንዱ እምነት ለሌላው እምነቱ፣የአንዱ ቋንቋ ለሌላው ቋንቋው፣የአንዱ ከባቢ የሌላው ከባቢውና የመኖሪያ ቤቱ እየሆነ እየተወራረሰ መጥቷል።

ለመጥቀስ ያህል የሌሎቹን የብዙዎቹን ትተን የአንዱን ብቻ ብናነሳ፣–

አጼ ሰርጸ ድንግል ከጎንደር ተነስተው በጎጃም በኩል ወለጋ፣ሊሙ፣ ጅማ፣ ከምባታ እየተበታተነ የሸፈተውንና አገር እያጠፋ ህዝብ እየዘረፈ ያስቸገረውን ሽፍታ ሁሉ ወታደር እየላኩ ከቀጡ በኋላ በኦሮሞው ግዛታቸው ሲደርሱ፣ከዚህ በፊት በመልካም ክብር የተቀበላቸው ባላባት ሞቶ ዳንቾ የተባለው ልጁ ተተክቶ ነበርና እርሱም በተራው እንዳባቱ በክብር ተቀበላቸው።ንጉሱን ተከትለው የሄዱት ቀሳውስት ስለክርስትና አስተምረውና አሳምነው ዳንቾንና ተከታይ ሹማምንቶቹን ክርስትና አነሱ።ዳንቾም የንጉሱ ክርስትና ልጅ ሆነ፤ስሙም ዘማርያም ተብሎ የወርቅ መስቀል ንጉሱ አጠለቁለት።የዳንቾንም ሚስት የንጉሱ አክስት እቴ ወለቴ ክርስትና አነሱ፣ሕዝቡ እራሱ በገዛ ፈቃዱ ውሃ ውስጥ እየገባ ተጠመቀ።ንጉሱም ለሕዝቡ የሚከፍለውን ግብር መጠን ቀነሱለት።በጉራጌም ግዛታቸው እንዲሁ ቦሾ የሚባለው ሹም ክርስትና ተነሳና የንጉሱ ክርስትና ልጅ ሆነ።ስሙም በተነሳበት ቀን ጊዮርጊስ ተባለ።የኘሁ ንጉስ የአጼ ሰርጸ ድንግል የእህት ልጅ፣መና እስራኤል የምትባለዋ ላሎ ከሚባል የኦሮሞ ባላባት ሰባት ልጆች ወልዳለች።ስማቸውም፣ ከረዩ፣ሜጫ፣ቱሉማ፣ወሎ፣አልኮ፣ዱረቲ፣ኢያንቱ ይባላል።የነዚህም ዘር ስርጭት የአንዳንድ ቦታዎች መጠሪያ ስም ሆኗል።በሌላም ከባቢ ወረሞ የሚባሉት የቤተሰብ ተወላጆች እየበረከቱ በመምጣታቸው በአሁኑ ጊዜ ለማህበረሰቡ መጠሪያ ለመሆን በቅቷል።እዚህ ላይ መገንዘብ የሚኖርብን ነገር ቢኖረ የየጎሳው በጋብቻም ሆነ በእምነት የማስተሳሰሩ ሂደት ወደ እኩልነትና ቤተሰብነት ወደ አመራ ግንኙነት የረዳ ብልሃት እንጂ በአንዳንድ ሰዎች እንደሚቀርበው ነጮች የጥቁርንና የሌላውን የተለዩ ሕዝብ አገር ሲወሩና ሕዝቡን በባርነት ሲገዙ በወሰዱት ዘረኛ መልክ አንዳልሆነ፣ለይቶ ማወቅ የሚገባና ትክክለኛ ሚዛናዊ የሆነ የታሪክ አቀራረብ አላፊነትን የሚጠይቅ ስራ መሆኑን ነው።

የተርርጓሚው አስተያየት-በጣም የሚገርመውና የሚያሳዝነው ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ የደቡቡ ሕዝብ በሰሜኑና በመሃል አገሩ ሕዝብ ተወሮ ሃይማኖቱንና ማንነቱን እንዲያጣ ተደርጓል እያሉ የአዞ እምባ የሚረጩት የስልጣን እብድ ምሁራን እነሱ እራሳቸው በውጭ አገር ሚሲዮኖች መጠመቃቸውን ስማቸው ሳይቀር መለወጡን እንደ ትልቅ ክብርና ስልጣኔ ሲቆጥሩ መሰል ያገር ልጅ ወገናቸው የአገሩን ዳር ድንበርና የሕዝቦች አንድነት ለማስከበርና ለመጠበቅ የወሰደውን እርምጃ ማውገዛቸውና እንደ ወንጀል መቁጠራቸው ነው።የውጭ ሚሲዮናዊ ስራ በሃይማኖትና በሰብአዊ ስራ ምክንያት እየገባ ተቆርቋሪና አሳቢ መስሎ የህዝብን ህብረት ንዶና አዳክሞ የላከው አገርና መንግስት ጥቅም የሚጠበቅበትን መንገድ ማዘጋጀት ነው።በአለፈው የቅኝ ገዥዎች የመስፋፋት ዓላማ በዚህ አይነቱ ስልት ነበር ለመሳካት የቻለው።የአንድን አገር የተፈጥሮ ሃብት በቁጥጥር ስር ለማዋል የግድ የሚገቡበት ቀዳዳ መፍጠር ያስፈልጋል።በሃይማኖትና በእርዳታ ስም መግባት ቀላሉና ርካሹ ዘዴ ነው።ከገቡ በኋላ ደግሞ በሃይማኖት የተሳሰረን ሕዝብ ሌላ አዲስ ሃይማኖት እንዲከተል በማድረግ መነጣጠል፤የጋራ ታሪኩን እንዲጠላ፣ ማንነቱን ክዶ ሌላ እንዲሆን ማድረግ፣ የህዝቡን አንድነት አፍርሶ፣እርስ በራሱ እያናከሱ ወረራቸውን

የሚቋቋም ተከላካይ ሃይል ማዳከምና ማሳጣት ተከታዩ ዓላማ ይሆናል። ይህም በአገር በቀሉ ባንዳ ተሳትፎ ድጋፍና እርዳታ እንዲጠናቀቅ ማድረግ መሆኑ የተሰወረ አይደለም። በኤርትራ፣በትግራይ፣በወለጋ፣በኦጋዴንና በደቡብ ከፈላተ ሃገራት በሚኖሩት ኢትዮጵያውያን ዘንድ በዲሞክራሲ መብት ስም ከኢትዮጵያ የመገንጠል እንቅስቃሴ የጀመሩትና እስከ አሁንም የሚያራምዱት ምሁራን በውጭ አገር ሚሲዎኖች በተደራጁና በሚረዱ ትምህርት ቤቶች በተማሩና የነዚሁ የሚሲዮን፣የካቶሊክ፣ የፕሮቴስታንት፣ የአድቬንቲስት፣የሉትራን…ወዘተ ሃይማኖቶች ተከታዮች በሆኑ የጥቁር ነጮች ነው።ይህን ዜግነትን የሚያስከድ፣አንድነትን የሚንድ አመለካከት መዋጋት ማለት አገርን ከእጅ አዙር ቅኝ ግዛት ወረራ መከላከል ማለት ሲሆን በእኩልነትና በዲሞክራሲ ስም እያዩ በቸልታ ማሳለፍ አገርና ሕዝብን ከበለጠ መቀመቅ ውስጥ ለመክተት ፈቃደኛ መሆን ነው።እዚህ ላይ በጣም መጠንቀቅ ያለብን ጉዳይ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እምነት ውጭ የሚከተል ኢትዮጵያዊ ሁሉም የውጭ አገር መሳሪያና ለአገሪቱ አንድነት አደገኛ ነው ማለት አይደለም።ያመኑትን እያመኑ አገራዊ የዜጋ ግዴታቸውን የተወጡና የሚወጡ፣መስዋእት የሆኑ ብዙዎች ናቸው። እስላም ክርስቲያን ሳይባል ለአገሪቱ መቆየት ድርሻውን አበርክቷል።ለማለት የተፈለገው ሕዝብ ተወላጆች የሆኑ የአገሪቱ ዜጎች አቅማቸው እስከ ፈቀደ ድረስ እየተቀባበሉ ያስተዳደሩባት አገር ነች።የስልጣን ምንጩ ጉልበትና ሃይል በሆነበት አገር የስልጣኑ ባለቤቶች ብዙ ወታደርና ጭፍራ ተከታይ የነበራቸው ናቸው።በየጊዜው የተነሱት የየጎሳውና ማህበረሰቡ መሪዎች ከከባቢያቸው አልፈው ሄደው ይገዙና ያስገብሩ ነበር።ይህ በአማራው፣ ማህበረሰብ ብቻ የተከናወነ ድርጊት ሳይሆን በትግራዩ፣በኦሮሞውና በሌላውም የአገሪቱ ማህበረሰብ ተወላጆች የተከናወነ የወል ድርጊት ነው።የሃይማኖቱም የቋንቋውም ስርጭት እንዲሁ ከስልጣንና ከሃይል ጋር የተያያዘ ነው።በግራኝ አህመድ መነሳትና መስፋፋት ጋር የተያያዘው የኦሮሞ ሕዝብ የሃይማኖትና የስልጣን ለውጥ ከግራኝ በኋላ የተነሱትን የሰሜን ነገስታቶች እረፍትና ሰላም የነሳ ነበር። በዚህ ብቻም ሳይወሰን በወሎ የሚኖረው የኦሮሞ ማህበረሰብ ተወላጆች ስልጣኑን ነጥቀው ለረጂም ጊዜ በጎንደር ቤተመንግስት ተቀምጠው አገሪቱን ያስተዳድሩ ነበር።

በግምት በ1730 ዓ ም አካባቢ ጀምሮ በሰሜን ኢትዮጵያ የጎንደር ነገስታት ሃይልና ስልጣን በቤተመንግስትም በክፍለ ሃገርም ፣በጦር ድርጅትም እየቀነሰና እየተዳከመ ሄደ።በሌላ በኩል የኦሮሞ፣የአማራና የትግሬ የአካባቢ ባላንጣ መሳፍንቶችና የጦር አበጋዞች ሃብትና ሃይል በየከባቢአቸው በጣም እያደገና እየተስፋፋ ሄደ።በሌላ ቃል "ዘመነ መሳፍንት"ተብሎ የሚታወቀው የጦር አበጋዞች ስርዓት ተፈጠረ።

በሌላ አነጋገር የተለያዩ ኦሮሞ ማህበረሰቦች በጥንታዊው የገዳ ባህላዊ ስርዓት ፈንታ በመደባዊ የባላባት የጉልተኛ ስርዓትና ሕግ መተዳደር ጀመሩ።የከባቢ ኦሮሞ ባላባቶች እየታወቁና እየገነኑ ሲሄዱ ከመካከለኛው መንግስት መሪዎች ጋር የጥቅም ግንኙነት እያስተሳሰራቸው ፣ግንኙነቱ በቤተሰብ ደረጃ እየተለወጠና እያደገ መጣ።

በሰላም ጊዜ አብሮ መብላት በጦርነትም ጊዜ አብሮ መዝመትና መመከት የጋራ ተግባራቸው ሆነ።በዚህ አኳያ አጼ በካፋ በ1720-1730 የነበረው የጎንደር ንጉስ በቤተ መንግስቱ አካባቢ የተነሱትን የስልጣን ባላንጣዎቹን ለመምታት ከወሎ-የጁ ተዛማጅ የኦሮሞ ማህበረሰቦች የተውጣጣ አንድሽህ ወታደሮችን የያዘ የክብር ዘብ አዘጋጅቶ ነበር።

በ1730 አጼ በካፋ ከሞተ በኋላ ሚስቱና የልጁ የአጼ ዳግማዊ እያሱ እናት እቴጌ ምንትዋብ የሚቹን የባሏን የንጉስ በካፋን ከኦሮሞ ባላባቶች ጋር የነበረውን ግንኙነት በማጠናከር የኦሮሞ ምርጥ የጦርና የአስተዳደር ሰዎች በስልጣንና በአመራር ቦታዎች ላይ ሾመች።በተጨማሪም ግንኙነቱን ለማጥበቅ ለልጇ ለአጼ እያሱ የየጁ ኦሮሞ ባላባት ልጅ የነበረችውን ወይዘሮ ውቢትን ክርስትና አስነስታ ዳረችለት።የዳግማዊ እያሱ ልጅ አጼ ኢዩአስ በ1755-1769 የመንግስትና የጦር ከፍተኛ ባለስልጣኖችና ሹማምንቶች አብዛኛው ከኦሮሞ ከሆኑት የእናቱ ዘመዶች የተውጣጡ ነበሩ።በመሆኑም በዘመኑ ለተወሰነ ጊዜ ኦሮምኛ ቋንቋ በጎንደር ቤተ መንግስት ውስጥ የሚነገር ልሳነ አጼ ከመሆን ደረጃ ላይ ደረሰ።

የራስ አሊ ጉዋንጉል፣ቤተሰብ፣እነጉግሳ መርሳ፣የነአሊጋዝ ከዚያም ትንሹ ራስ አሊ ከ1760-1852 ድረስ በያዙት መቶ ዓመት የሚጠጋ የስልጣን ዘመን ከጎንደር ቤተመንግስት ውጭ ባለው ከባቢ ኦሮሞኛ ቋንቋ በሰፊው

በመነገሩ ወደ ብሄራዊ ቋንቋ ደረጃ ለመድረስ አቅጣጫ ይዞ ነበር፤ ግን በስልጣን ልውውጡና ከመሳፍንቶች ውድቀት ጋር ተያይዞ ባለበት ቀረ። በዚህ በዘመነ መሳፍንትና ከዚያም በኋላ የተነሱት የትግራዩ፣የአማራው፣ የኦሮሞው መሪዎች የዘር ግንዳቸውን በዚህም በዚያም በኩል ከሰለሞናዊው ትውልድ ጋር እያስተሳሰሩ ታሪካቸው እንዲጻፍና ሕዝብ እንዲቀበላቸው ያደርጉ ነበር።ከነዚህ ታላላቅ ያገሪቱ ማህበረሰብ ጋር እርስ በርሱ ያልተጋባና ያልተዛመደ የለም።

የአጼ ምኒሊክ ሚስት እቴጌ ጣይቱ ብጡልም ከየጁ ኦሮሞ ማህበረሰብ የተወለዱ ናቸው።ልጅ እያሱም በወሎ ውስጥ ወረሂመኖ በሚባለው ቦታ ባላባት ከነበሩት ከይማም አሊ አባ ቡላና ከወ/ጌጤ ከተባሉት ከግንደበረት ከመጡት የቤት አገልጋይ ከተወለዱት ሙሃመድ አሊ በኋላ ንጉስ ሚካኤል ከተባሉት ኦሮሞ ሙስሊም ባላባት የተወለዱ ናቸው።የአጼ ሃይለስላሴ አያት ፣ያባታቸው የራስ መኮንን አባትም ጉዲና የተባሉ ኦሮሞ እንደነበሩ ልብ ማለት ያስፈልጋል።

የተርጓሚው አስተያየት-እንግዲህ ኦሮሞነት ባዳና እንግዳ ያልሆነ እንደ አማራውና ትግሬው እንደቀሩትም ማህበረሰቦች፣እንደሙስሊምና እንደክርስትና እምነቱ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አካልና ገጽ ሆኖ የኖረና የሚኖር በቅደም ተራ አገሪቱን ሲያስተዳድሩና ሲገዙ ከነበሩት እኩል ደረጃ ኖሮት ሲመራ የነበረ ማህበረሰብ እንጂ ተረግጦና ተዘርፎ ተንቆ፣እንደውጭ ዜጋ ተቆጥሮ የኖረ ባዳ አይደለም።ለአገሪቱ አንድነት መስዋዕት የሆነ የሚያኮራ ዜጋ ነው።

ከላይ የተዘረዘረውን የታሪክ ዘገባ ስንመለከት ኢትዮጵያ አንድ ነጠላማህበረሰብ ሲገዛባት፣አንድ ነጠላ ቋንቋ ብቻ ሲነገርባት፣የአንድ ማህበረሰብ ባህልና እምነት ሲንጸባረቅባት ያልኖረች አገር መሆኗን እንረዳለን።

ኢትዮጵያ የተመሰረተችውና የቆመችው በአማራው ማህበረሰብ ብቻ ሳይሆን ሌላውም በመሬቷ ውስጥ የሚኖረው ዜጋ በጋራ በከፈለው የህይወት ዋጋ ነው።አገሪቱን በአገር ደረጃ አሰባስቦ ለመፍጠር ሁሉም የድርሻውን አበርክቷል።አገር ለማዋሃድ ከተነሱ መሪዎች ጎን ተሰልፎ ሲያስፈልግ በሃይል፣አለበለዚያም በዘዴና በመስማማት በአንድ መንግስት አስተዳደር ስር እንዲዋቀር በተደረገው ሂደት አንድነትን የሚወድና የሚቀበል ሁሉ በሚችለው ሁሉ ተባብሯል።አማራ፣ኦሮሞ ትግሬ ጉራጌ፣ሃድያ፣ አፋር፣ሲዳማ፣ሶማሌ፣...ወዘተ ሳይባል

የውጭ ወራሪ ሃይል ሲነሳ፣እርግጥ አንዳንድ ተባባሪዎችና ባንዳዎች መኖራቸው ባይካድም የኔ የሱ ሳይል የኛ ብሎ ያገሩን ዳር ድንበርና አገራዊ  ነጻነቱን ለማስከበር ከዳር እስከዳር ተነስቶ የሚጠበቅበትን የህይወት ድርሻ ከፍሏል።በዚያም ትግሉ ኢትዮጵያን ለተተኪው ለእኛ ትውልድ አስረክቦ አልፏል፤ይህም ትውልድ ለተተኪው የማስረከብ አደራ አለበት።

በአሁኑ ጊዜ ፈጦ የሚታየው ችግር ከኢትዮጵያ ቤተሰብነት እራስን ነጥሎ ማውጣትና የዘመናት ዝምድናን፣ ትስስርን፣ቤተሰብነትን ክዶ ለብቻ አፈንግጦ ለመኖር የሚደረገው ውድድር ነው።መታወቅ የሚኖርበት ጉዳይ እንኳንስ በዘር የተቆላለፈ ፣ለመለየት የሚያስቸግር ፣ በመልክ፣በምነት፣በመልከአ ምድር፣በባህልና በታሪክ የተሳሰረ ሕዝብ ቀርቶ ውቅያኖስ የሚለየውም ሕዝብ እንኳን ተነጣጥሎ ለመኖር ያዳግተዋል። ኢትዮጵያውያን የድንበር ልዩነቱ በማይለየው ምድር ላይ እየኖርን ከመካከላችን በወጡ  የሰፈር ልጆችና የጎሳችንን ቋንቋ በሚናገሩ የስልጣን እብዶችና የውጭ ጠላት ተወካዮች  በሆኑ እየተታለቅን ለመለያየት አመቺ ስንሆን በሌላው ቦታ በባህርና በውቅያኖስ በተነጣጠሉ ደሴቶች የሚኖር የተለያዩ ሕዝብ በአንድነት እየኖረ፣በአንድ መንግስት ስር የሚገጥመውን ችግር በጋራ ሲወጣ እንመለከታለን።ለመገነጣጠል ሌት ተቀን ስንሰራ መሳቂያ ከመሆን በላይ የሚያሳፍረንና ትውልድ ይቅርታ የማያደርገውን ጥፋት መስራታችንን ከወዲሁ ልንረዳ ይገባል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የተቀላቀለ ሕዝብ ነው።በኋላ የመጣው በፊት ከመጣው ጋር ተቀላቅሏል።አንዱን ካንዱ መለየት አይቻልም።እንኳንስ በአሁኑ በሰለጠነውና ህዝብ ከአንዱ ከባቢ ወደ ሌላው በቀላሉ መጓዝ በሚችልበት ጊዜ ቀርቶ በጥንቱም ጊዜ እንኳንስ  ተራው ሕዝብ በስልጣን ላይ የነበሩትም ነገስታት ከሌላው ብሄረሰብ ጋር ተጋብተው ፣ተዋልደው ስልጣኑን እየተቀባበሉ ኑረዋል።የአንዱ እምነት ለሌላው እምነቱ፣የአንዱ ቋንቋ ለሌላው ቋንቋው፣የአንዱ ከባቢ የሌላው ከባቢውና የመኖሪያ ቤቱ እየሆነ እየተወራረሰ መጥቷል።

በአንድ አገር ውስጥ በሚኖሩ፣በታሪክና በዘር በተሳሰሩ ሕዝቦች መሃል የሚፈጠረው የሃይማኖትም ሆነ የቦታ መወራረስ ፤የኖረ ያለና የሚኖር እውነታ መሆኑን መቀበል ያሻል።ሊያቆሙትና ሊከላከሉት የማይችሉት የሕዝብ ግንኙነት ፣የዜጋ ትስስር ነው።የኢትዮጵያ ሕዝብ በቀላሉ ሊበጠስ በማይችል የቤተሰብ ድር ተሳስሯል።

በሌላውም ገጹ ብናስተውል፤በስልጣን ላይ የተቀመጠው መንግስት መመሪያና መርሆው በዘር ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ኢትዮጵያዊ ከዜግነቱ ይልቅ በሚኖርበት ክልል፣ በሰፈሩ፣በቋንቋው፣በጎሳና በሃይማኖቱ የሚለይበት፣ ስርዓት ውስጥ ገብተን በመዋተት ላይ ነን።በተጨማሪም ከአገር ክብርና ጥቅም ይልቅ ገንዘብና የግል ጥቅም ከፍተኛውን ቦታ ስለያዘ አብዛኛው ዜጋ በዚያው መንገድ በራስ ወዳድነት ተጠምዶ ብሄራዊ ስሜቱና የቤተሰብ ፍቅሩን አጥቶ ሲባዝን፣ሲያጭበረብርና ሲክድ፣በሙስና ሲጨማለቅ ከምናይበት ወቅት ላይ ደርሰናል።የአገሪቱ መሪዎች ሃብት እያግበሰበሱ ፣የበለጠ ጥቅም ለሚሰጣቸው ያገር ውስጥና የውጭ አገር ከበርቴና ኩባንያዎች ያገሪቱን መሬትና አንጡራ ሃብት በመቸብቸብ ላይ ናቸው።ልማት ወይም ኢንቨስትመንት በሚል ስምና ሽፋን አገር በቀላሉ የምትቦጠቦጥበት መመሪያ ተነድፎ ገንዘብ ያለው የውጭ አገር መንግስታዊና የግል ባለሃብት ኩባንያ የፈለገውን በማድረግ ላይ ነው።በየከባቢው በስልጣን ላይ የተቀመጡትም እንዲሁ እንደአለቆቻቸው እድሉን በመጠቀም«ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል»በሚል ፈሊጥ ደሃውን ህዝብ በሙስና የአገር ንብረት የሆነውን መሬትና የተፈጥሮ ሃብት እየቸበቸቡ በውጭ አገር የባንክ ቁጥር በማስቀመጥና በየቤተሰቡ ስም ንብረት በመግዛትና በመያዝ ውድድር ውስጥ ገብተዋል።ሌላውም ተራ ዜጋ ያባትህ ቤት ሲበዘበዝ አብረህ በዝብዝ በሚለው እኩይ ምግባር፣በስርቆት፣በሙስና፣ ሙያ ላይ ተሰማርቶ ይገኛል። አገርና ሕዝብ እንደመሪውና እንደ ስርዓቱ መሆኑን በጥቂቱም ቢሆን በዚህ ልንገነዘብ እንችላለን።

በአሁኑ ጊዜ ፈጦ የሚታየው ችግር ከኢትዮጵያ ቤተሰብነት እራስን ነጥሎ ማውጣትና የዘመናት ዝምድናን፣ ትስስርን፣ቤተሰብነትን ክዶ ለብቻ አፈንግጦ ለመኖር የሚደረገው ውድድር ነው።እኛ ኢትዮጵያውያን ከመካከላችን በወጡ  የሰፈር ልጆችና የጎሳችንን ቋንቋ በሚናገሩ የስልጣን እብዶችና የውጭ ጠላት መሳሪያ በሆኑ እየተታለቅን ለመለያየት አመቺ ስንሆን በሌላው ቦታ በባህርና በውቅያኖስ በተነጣጠሉ ደሴቶች የሚኖር የተለያዬ ሕዝብ በአንድነት እየኖረ፣በአንድ መንግስት ስር የሚገጥመውን ችግር በጋራ ሲወጣ እኛ በአንድ ኩታ ገጠም በሆነ አገር ውስጥ የምንኖር፣በባህል፣ በታሪክ፣በእምነት፣በጋብቻ የተሳሰርን እርስ በርስ ስንባላና  የጋራ ሰንደቅ ዓላማችንን በመቅደድና የጎሳ ባንዲራ ሰፍተን ስንራኮት፣ለመገነጣጠል ሌት ተቀን ስንሰራ መሳቂያ ከመሆን በላይ የሚያሳፍረንና ትውልድ ይቅርታ የማያደርገውን ጥፋት መስራታችንን ከወዲሁ ልንረዳ ይገባል።

የፕሮፌሶር ሪቻርድ ፓንክረስትን ነፍስ ይማር!ስማቸው በኢትዮጵያ የምሁራን ታሪክ ውስጥ ዘላለም ጎልቶ ይኖራል!!!

አገሬ አዲስ

26-04-2017